61_1999.pdf

62_1999.pdf

63_1999.pdf

64_1999.pdf

65_1999.pdf

66_1999.pdf

67_1999.pdf

68_1999 court.pdf

69_1999.pdf

70_1999.pdf

71_1999.pdf

72_1999.pdf

73_1999.pdf

74_2000.pdf

75_2000.pdf

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| 11ኛ አመት ቁጥር 10<br>11th year No 10 | | ሐረር ጥቅምት 8 ቀን 1999 ዓ.ም |
| ያንዱ ዋጋ ሣንቲም 0.50<br>Unit Price Cents 0.50 | በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272<br>P.o .Box 272 |

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 61/1999 ዓ.ም
የሸዋል ኢድ ቀንን በክልሉ በዓል እንዲሆን የወጣ አዋጅ......ገጽ 481

## አዋጅ ቁጥር 61/1999 ዓ.ም
## «ሸዋል ኢድ» ቀንን በክልሉ በዓል እንዲሆን ስለማወጅ

ብሔር ብሔረሰቦች ባህላቸውን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት መብት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 2 በመረጋገጡ፤

የሐረሪ ብሔረሰብ ባህሉን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት መብት በክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 39(1) መረጋገጡንና ይህንን የባህል መብት መንግስት የመንከባከብ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በህገ መንግስቱ አንቀጽ 41(8) ላይ የተደነገገ መሆኑን በመገንዘብ፤

የሐረሪ ብሔረሰብ ለረጅም ዘመናት በየ ዓመቱ የሸዋል ኢድ በአልን እንደ ልዩ ባህሉና ታሪካዊ መገለጫ እለት በማድረግ ሲዘክርና ሲያከብር የቆየ ቢሆንም ለባህሉ እድገትና አከባበር ማነቆ የሆኑትን የተለያዩ ችግሮች መቅረፍ አስፈላጊ በመሆኑ፤ እንዲሁም ባህሉን በዘላቂነት ለመንከባከብና ለመጠበቅ፤ ይህ እለት በደመቀ ሥነ-ሥርዓት እንዲከበርና ለትውልድ እሴቱን ጠብቆ ለማስተላለፍ እንዲቻል በዝርዝር ህግ ዋስትና መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሐረሪ ብ/ጉባዔ የሐረሪን ብሔረሰብ ባህልና ታሪክን እንዲጠብቅና እንዲንከባከብ ከፍተኛ ኃላፊነት የተጣለበት በመሆኑና ''ሸዋል ኢድ'' የሐረሪዎች ልዩ ባህላዊና ታሪካዊ መገለጫ እለት መሆኑን በመገንዘብ፤

የሐረሪ ብሄራዊ ጉባዔ በተሻሻለው የሐረሪ ህዝብ ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚከተለውን አውጇል።

www.chilot.me

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "«ሸዋል ኢድ» ቀንን በክልሉ በዓል እንዲሆን ለማድረግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 61/1999 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

ቃሉ በአግባቡ ሌላ ትርጉም እንዲሰጥ ካልተደረገ በስተቀር በዚህ አዋጅ፦

1. «ሸዋል ኢድ» ማለት ከኢድ አልፈጥር በዓል ቀጥሎ ስባተኛ ቀን ላይ የሚውለው ዕለት ነው።
2. «ክልል» ወይም «ክልሉ» ማለት የሐረሪ ህዝብ ብሄራዊ ክልል ነው።
3. «ቢሮ» ማለት በሐረሪ ህ/ክ/መንግስት የህዝብ አደረጃጀት፣ ባህልና ማሕበራዊ ጉዳይ ቢሮ ነው።

## 3. «ሸዋል ኢድን» የክልሉ በዓል ስለማድረግ

ሸዋል ኢድ በሐረሪ ህዝብ ክልል የሚከበር ክልላዊ የበዓል ቀን እንዲሆን ተደርጓል።

## 4. አዋጁን የማስፈጸም ሥልጣን

ቢሮው የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በሚያወጣው የአዋጁ ማስፈፀሚያ ዝርዝር ደንብ መስረት የሸዋል ኢድ ማክበሪያ ስፍራና የአከባበሩን ስነ-ሥርአት መሰረት በማድረግ በአሉን የማስፈፀም ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

## 5. የአዋጁ ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ሥር በተቋቋመው የመንግስት መ/ቤቶች በሙሉ ተፈፃሚ ይሆናል።

## 6. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ህግ፣ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ለተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 7. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ደንብ ሊያወጣ ይችላል። እንዲሁም ለዚህ አዋጅና ደንብ ዝርዝር ማስፈፀሚያ ቢሮው መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## 8. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥቅምት 8 ቀን 1999 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ጥቅምት 8 ቀን 1999 ዓ.ም

ሐ ረ ር

ሙራድ አብዱልሃዲ

የሐረሪ ህ/ብ/ክ/መንግስት ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA
OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | |
|---|---|
| 11ኛ አመት ቁጥር 11<br>11th year No. 11 | ሐረር ህዳር 6 ቀን 1999<br>HARAR, Nov.15/2006 |

| | | |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ ብር 5:60<br>Unit Price Bir. 5:60 | በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት<br>ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 952<br>P.o .Box 952 |

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር 62/1999 ዓ.ም
የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኮንዶሚየም ባለቤትነት አዋጅ ...................... ገጽ483

## አዋጅ ቁጥር 62/1999
## የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
## የኮንዶሚኒየም ባለቤትነት አዋጅ

በሐረር ከተማ ያለውን የቤት አቅርቦትና የቤት ፍላጎት አለመጣጣም ለመቀነስ የከተማ ቦታን በግል ከመሸንሸን በተጨማሪ ሌሎች የከተማ ቦታ አጠቃቀም አማራጮችን ጎን ለጎን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

የከተማ ቦታን ወደ ላይ ወይም ጎን ለጎን የተሰሩ ቤቶችን ለሚይዝ የጋራ የህንፃ ግንባታ መዋል አስተኛ የከተማ ቦታ የብዙ ሰዎች የጋራ ይዞታ እና መጠቃቀሚያ እንዲሆን በማድረግ የከተማ ቦታ አጠቃቀምና የቤት አቅርቦትን በማሻሻል እንዲሁም የከተማዋን ውበት በመጠበቅ ረገድ የሚኖረውን ድርሻ በመረዳት፤

የግል አልሚዎችና ማህበራት በኮንዶሚኒየም ግንባታ ለሚኖራቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ እና ኮንዶሚኒየም ለሚገዙ ወይም ለሌሎች በኮንዶሚኒየም ላይ ባለመብት ለሆኑ ሰዎች ምቹ ሁኔታ መፍጠር ለጋራ ህንፃ ግንባታ ወሳኝ በመሆኑ፤

በተሻሻለው የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ህገ-መንግስት አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) በተደነገገው መሰረት በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት ከዚህ የሚከተለው ተውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት የኮንዶሚኒየም ባለቤትነት አዋጅ ቁጥር 62/1999" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ኮንዶሚኒየም" ማለት ከመሬት ወደ ላይ ወይም ጎን ለጎን የተሰሩ በተናጠል የሚያዙ አምስትና ከአምስት በላይ ቤቶች እና በጋራ ባለቤትነት የሚያዙ የጋራ መጠቀሚያዎች ያሉት ለመኖሪያ ወይም ለአገልግሎት የሚውል ግንባታ ሲሆን ኮንዶሚኒየም ያረፈበትን የቦታ ይዞታ ይጨምራል፡፡

www.chilot.me

2. **"የጋራ መጠቀሚያ"** ማለት በተናጠል ከተያዙት ቤቶች ውጭ ያለ ማናቸውም የኮንዶሚኒየሙ አካል ነው።
3. **"የጋራ ወጪ"** ማለት የቤት ባለቤቶች ማህበርን አላማ እና ግዴታ ለማስፈጸም የሚደረግ ማናቸውም ወጪ እና በዚህ አዋጅ በኮንዶሚኒየሙ ማሳወቂያ የጋራ ወጪ ተብሎ የተደነገገው ነው።
4. **"የጋራ ትርፍ"** ማለት የቤት የባለቤቶች ማህበር ከሚሰበሰበው ገቢ ወጪው ተቀንሶ የሚገኘው ውጤት ነው።
5. **"አስመዝጋቢ"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 መሰረት ኮንዶሚኒየም ያስመዘገበ ነው።
6. **"የህንፃ ማሳወቂያ"** ማለት የቤት ባለቤቶች ማህበርን እና የእያንዳንዱን የቤት ባለቤት መብትና ግዴታዎች የሚወስን ሰነድ ሲሆን ማንኛውንም የኮንዶሚኒየም ማሳወቂያ ማሻሻያ ይጨምራል።
7. **"የኮንዶሚኒየም መግለጫ"** ማለት የኮንዶሚኒየምን ስምና አድራሻ፣ የቤቶችንና የጋራ መጠቀሚያዎችን፣ ወሰኖችን፣ እንደዚሁም ከኮንዶሚኒየም አንፃር የጋራ መጠቀሚያዎች እና የእያንዳንዱ ቤት የሚገኝበት ትክክለኛ ቦታ የሚያሳይ ሰነድ ሲሆን ማንኛውም የኮንዶሚኒየም መግለጫ ማሻሻያ ይጨምራል።
8. **"ለተወሰነ ቤት የተመደበ የጋራ መጠቀሚያ"** ማለት ከጋራ መጠቀሚያ ውስጥ ለአንድ ወይም ለተወሰነ ቤቶች አገልግሎት ብቻ የተመደበ የኮንዶሚኒየም አካል ነው።
9. **"የቤት ባለቤቶች ማህበር"** ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የተቋቋመ የኮንዶሚኒየም ባለቤቶች ማህበር ነው።
10. **"መዝጋቢ አካል"** ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የኮንደሚኒየም ባለ ቤትና "የኮንደሚኒየም ባለቤቶች ማህበርን የምዝገባ ተግባር ለማከናወን በመስተዳደር ም/ቤቱ በሚወጣው ደምብ መሰረት የሚሰየመው አካል ነው።
11. **"ቤት"** ማለት በኮንዶሚኒየም ማሳወቂያና መግለጫ ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት የተመደበ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ክፍሎች ያሉት የኮንዶሚኒየም አካል ነው።

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሚገኙ የከተማ አገልግሎት ጽ/ቤቶች፣
የመንግስት የቤት ልማት ድርጅቶች፣ በግል ባለሀብትና በቤት ባለቤቶች ማህበራት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## የኮንዶሚኒየም ምዝግባና የምስክር ወረቀት

### 4. የኮንደሚኒየም ምዝገባ

1. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የኮንዶሚኒም ባለቤት ወይም ወኪሉ ኮንዶሚኒየሙ በዚህ አዋጅ እንዲገዛ ፍላጎቱን በጽሁፍ ለመመዝገብ ብቁ የሚያደርጉትን የኮንዶሚኒየም ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ ውስጠ ደንብ፣ ሲያቀርብ ኮንዶሚኒየሙ ይመዘግባል።
2. የኮንዶሚኒየም ማሳወቂያና መግለጫ የመተዳደሪያ ደንብ እና ውስጠ ደንብ ይዘት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።
3. የኮንዶሚኒየም ማሳወቂያና መግለጫ መተዳደሪያ ደንቡና ውስጠ ደንቡ በመዝጋቢው አካል መጽደቅና መመዝገብ አለበት።

### 5. የምዝገባ የምስክር ወረቀት

በዚህ አዋጅ መሠረት ኮንዶሚኒየሙ ሲመዘገብ ለአስመዝጋቢው የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

### 6. የምዝገባ ውጤት

1. ኮንዶሚኒየም፤ ኮንዶሚኒየሙ ያረፈበት ቦታና ከዚሁ ጋር የተያያዙ መብቶች ጥቅሞችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ይገዛሉ።
2. በኮንዶሚኒየም መግለጫ ላይ የተገለጸው ህንፃ በቤቶች እና በጋራ መጠቀሚያዎች ይከፋፈላል።
3. የቤት ባለቤቶች ማህበር የሕግ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ ይቋቋማል።

### 7. የኮንዶሚኒየም ማሳወቂያና መግላጫ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ ስለማሻሻል

1. የኮንዶሚኒየም ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ መሻሻ በቤት ባለቤቶች 2/3ኛ ድምጽ መወሰን አለበት።
2. በቤት ባለቤቶች የጸደቀው መተዳደሪያ ደንብ፤ ውስጠ ደንብ እና የመተዳደሪያ ደንቡና ውስጠ ደንቡ ማሻሻያ ተግባራዊ የሚሆነው ለመዝጋቢው አካል ቀርቦ ሲመዘገብና ለዚሁም የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማህበሩ ሲሰጠው ነው።

# ክፍል ሦስት
## ስለ ባለቤትነት

### 8. ስለ ቤት ባለቤትነት

1. በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም የቤት ባለቤት በቤቱ ላይ የባለቤትነት መብት ይኖረዋል።
2. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚተዳደር የኮንዶሚኒየም አካል የሆነ ቤት በተናጠል ማናቸውም ህጋዊ ተግባር የሚከናወንበት ነው።

### 9. ስለ ጋራ መጠቀሚያዎች

1. በዚህ አዋጅ፣ በኮንዶሚኒየም ማሳወቂያ፣ በመተዳደሪያ ደንብና በውስጠ ደንብ የተወሰኑ ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የኮንዶሚኒየም ባለቤት የጋራ መጠቀሚያዎችን አግባብ በሆነ መንገድ የመጠቀም መብት አለው።
2. በጋራ መጠቀሚያዎች የመጠቀም መብት የማይከፋፈል እና ከእያንዳንዱ ቤት የባለቤትነት መብት ጋር የማይነጣጠል ነው።
3. የእያንዳንዱ ቤት ባለቤትነት መብት በጋራ መጠቀሚያ ላይ የሚያስገኘው የማይከፋፈል መብት ድርሻ መቶኛ በኮንዶሚኒየም ማሣወቂያ ይወሠናል።
4. የእያንዳንዱ ቤት የባለቤትነት መብት በጋራ መጠቀሚያ ላይ የሚያስገኘው መብት ድርሻ የእያንዳንዱ ቤት አካል ሆኖ የሚታይና በቤት ላይ የሚፈፀው ማናቸውም ህጋዊ ተግባር የሚከተለው ነው።
5. በዚህ አዋጅ መሰረት ካልሆነ በቀር የጋራ መጠቀሚያዎች ሊከፋፈሉ አይችሉም።

# ክፍል አራት
## ስለ ቤት ባለቤቶች ማህበር

### 10. ስለ ማህበሩ

የቤት ባለቤቶች ማህበር ትርፍ ለማግኘት ወይም ለመከፋፈል ሳይሆን ለአባላቱ የጋራ ጥቅም የተቋቋመ ማህበር ነው።

### 11. ዓላማ

የቤት ባለቤቶች ማህበር የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

1. የቤት ባለቤቶችን በመወከል ኮንዶሚኒየሙን ማስተዳደር፣
2. የኮንዶሚኒየም ነዋሪዎች ሠላምና ደህንነት ማስጠበቅ፣
3. የቤት ባለቤቶች ቤቶችን የያዙ ሰዎች፣ የጋራ መጠቀሚያ ተከራዩች ይህንን አዋጅ፣ የኮንዶሚኒየም ማሳወቂያና መግለጫውን፣ መተዳደሪያ ደንቡንና ውስጠ ደንቡን ማክበራቸውን ማረጋገጥ፣
4. የቤት ባለቤቶችን የጋራ ጥቅም በመወከል አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን መፈፀም።

### 12. የማህበር አባልነት

ማንኛውም የኮንዶሚኒየም ባለቤት የቤት ባለቤቶች ማህበር መሆን አለበት።

### 13. የማህበሩ ስልጣንና ተግባር

የቤት ባለቤቶች ማህበር የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የህንፃ ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብና ውስጥ ደንብ ማውጣት፣ማሻሻል፣
2. በጀት መወሰን፣ማሻሻል፣
3. የጋራ መጠቀሚያዎችን አጠቃቀም መወሰን፣
4. የጋራ መጠቀሚያዎችን ማከራየት፣በዋስትና ማስያዝ ማስተላለፍ፣
5. ቅጣት፣ መዋጮና የአገልግሎት ክፍያዎችን መወሰን፣
6. ሰራተኞች መቅጠር፣ ማስተዳደር ማሰናበት፣
7. የንብረት ባለቤት መሆን በዋስተና ማስያዝ ማስተላለፍ፣
8. ውል መዋዋል፣ መክሰስ፣መከሰስ ናቸው።

### 14. የማህበሩ ጠቅላላ ስብሳባ ስልጣንና ተግባር

የቤት ባለቤቶች ማህበር ጠቅላላ ስብሰባ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. የኮንዶሚኒየም ማሳወቂያና መግለጫ እንዲሁም ማሻሻያ ማፅደቅ፣
2. መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ እንዲሁም ማሻሻያዎቹን ማፅደቅ፣
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን መምረጥ፣ መሻር፣
4. የማህበሩ የስራ ክንውን፣ የሂሳብ ምርመራ ሪፖርቶች መስማትና ውሳኔ መስጠት፣
5. በዚህ አዋጅ መሰረት የቤት ባለቤቶች ማህበር ከሌላ የቤት ባለቤቶች ማህበር ጋር እንዲዋሀድ ወይም ኮንዶሚኒየም በዚህ አዋጅ መሰረት መተዳደሩ እንዲያበቃ መወሰን፣
6. ዓመታዊ የስራ ዕቅድና በጀት ማፅደቅ፣
7. በዳይሬክተሮች ቦርድ በሚቀርብለት ማናቸውም ጉዳይ ላይ ውሳኔ መስጠት።

www.chilot.me

## 15. የቤት ባለ ቤቶች ማህበር ስብሰባና ሥነ ሥርአት

1. የቤት ባለቤቶች ማህበር አመታዊ ጠቅላላ ስብሰባ ይኖረዋል፤
2. የቤት ባለቤቶች ማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚያደርገው ጥሪ መሰረት ሌሎች ስብሰባዎችን ያደርጋል፤
3. 25 ፐርሰንት (ሃያ አመስት በመቶ ) የሆኑትን ቤቶች የያዙ የቤት ባለቤቶች ስብሰባ እንዲደረግ ከጠየቁ የዳይክተሮች ቦርድ የቤት ባለቤቶች ስብሰባ መጥራት አለበት፤
4. በማንኛው ስብሰባ ከጋራ ህንፃው ቤት ባለቤቶች 50 ፐረሰንት ሲደመር 1 (ሃምሳ በመቶ ሲደመር 1) እና በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤
5. የቤት ባለቤቶች በቀጥታ ወይም በወኪል አማካኝነት ድምፅ ሊሰጡ ይችላሉ፤
6. በዚህ አዋጅ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በቀር የቤት ባለቤቶች ማህበር ውሳኔ የሚያስተላልፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል።

## 16. የዳሬክተሮች ቦርድ

1. የዳሬክተሮች ቦርድ የቤት ባለቤቶች ማህበር የአመራር አካል ነው፤
2. የመጀመሪያዎቹ ዳሬክተሮች በአስመዝጋቢው የሚሰየሙ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ዳይሬክተሮች ከቤት ባለቤቶች መካከል በባለቤትነት ይመርጣሉ።

## 17. የመጀመሪያው የዳሬክተሮች ቦርድ

1. ኮንዶሚኒየም በዚህ አዋጅ መሰረት ከተመዘገበ በኂላ አስመዝጋቢው የመጀመሪያውን የዳሬክተሮች ቦርድ መሰየም አለበት፤
2. የቤት ባለቤቶች በአስመዝጋቢው ከተሰየሙት የቦርድ አባላት ተጨማሪ የሚሆኑ አባላት ወይም ተተኪ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊመርጡ ይችላሉ፤
3. በዚህ አንቀጽ መሰረት ምርጫ ስለሚከናወንበት ጊዜ እና በመጀመሪያ የዳሬክተሮች ቦርድ መካከል ስለሚደረገው የስልጣን ሽግግር ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

## 18. የዳሬክተሮች ቦርድ ስልጣንና ተግባር

የዳሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. በዚህ አዋጅ መሰረት የማህበሩን ጠቅላላ ስብሰባ መጥራት፣ የስብሰባውን ቃለ-ጉባኤ በጽሁፍ መያዝ፤
2. የኮንዶሚኒየም ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብና ውስጥ ደንብ ማሻሻያ ማዘጋጀት፣ ሲፀድቅም በስራ ላይ ማዋል፤
3. ዓመታዊ የስራ ዕቅድና በጀት ማዘጋጀት ሲፀድቅም በስራ ላይ ማዋል፤
4. የማህበሩን መዛግብትና ሂሳብ መያዝ፤
5. የቤት ባለቤቶች ማህበር ጠቅላላ ስብሰባ ውሳኔዎችን መፈጸምና ማስፈፀም፤
6. የማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት ለጠቅላላ ስብሰባ ሪፖርት ማቅረብ፤
7. ሌሎች በጠቅላላ ስብሰባ የሚሰጡትን ተግባራት ማከናወን ናቸው።

## 19. ስለ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ

የቤት ባለቤቶች ማህበር መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ ይኖሩታል።

## 20. ስለ ኦዲተር

1. የቤት ባለቤቶች ማህበር ኦዲተር ይኖሩታል፤
2. የኦዲተር አሰያየም፣ ብዛት፣ ተፈላጊ ችሎታ፣ ተግባርና ስንብት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወስናል።

# ክፍል አምስት
# ኮንዶሚኒየምን ስለመሸጥና ማከራየት

## 21. በአስመዝጋቢው የሚደረግ ሽያጭ

1. በዚህ አዋጅ መሰረት ህንፃው ከመመዝገቡም ፊት ወይም ከተመዘገበ በኂላ የኮንዶሚኒየም ሽያጭ ውል ለመዋዋል ይችላል፤
2. ኮንዶሚኒየም ከመመዝገቡ በፊትም ሆነ በኂላ ከአስመዝጋቢው ላይ ኮንዶሚኒየም ለሚገዛ ማንኛውም ሰው አስመዝጋቢው መረጃ መስጠት አለበት፤
3. አስመዝጋቢው ለገገርው መረጃ እስከሚሰጠው ድረስ ገገርው በቤት ሽያጭ ውሉ አይገደድም፤
4. መረጃ ከአስመዝጋቢው ያልደረሰው ገዢ የባለሃብትነት ስም በስሙ ከማዛወሩ በፊት ለአስመዝጋቢው በጽሁፍ የውሉን መሰረዝ መግለጽ ይችላል፤
5. በመረጃ በተገለጹ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ ለውጥ ሲኖር አስመዝጋቢው በተሻሻለ መረጃ ለውጡን ለገገርው መግለጽ አለበት በተሻሻለ መረጃ መሰረታዊ ለውጥ መኖሩ ሲገልጽለት ወይም ገገርው በራሱ መሰራታዊ ለውጥ መኖሩን ተረድቶ አስመዝጋቢው የተሻሻለ መረጃ

www.chilot.me

ለአስመዝጋቢው በጽሁፍ የውሉን መሰረዝ መግለጽ ይችላል፡፡

6. ኮንዶሚኒየሙ ከመመዝገቡ በፊት የቤት ሽያጭ ውል የተዋዋለ አስመዝጋቢ በውሉ የተመለከተውን ህንፃ ግንባታ ሳይዘገይ የማጠናቀቅና ህንፃውን የማስመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡

## 22. ቤቶችን ስለማከራየት

1. ማንኛውም የቤት ባለቤት ሲያከራይ ወይም የቤት ኪራይ ውል ሲያድስ ለቤት ባለቤቶች ማህበር በጽሁፍ መግለጽ እና የኪራይ ውሉን ሰነድ ወይም የኪራይ ውሉን ማደሻ ሰነድ አባሪ አድርጎ መስጠት አለበት፤
2. ማንኛውም የቤት ባለቤት የቤት ኪራይ ውል በማናቸውም ምክንያት ሲቋረጥ የውሉን መቋረጥ የሚያስረዳ ማስረጃ አባሪ በማድረግ የውሉን መቋረጥ ለቤት ባለቤቶች ማህበር መግለጽ አለበት፤
3. ማንኛውም የቤት ባለቤት የቤት ኪራይ ውል ሲዋዋል ለተከራዩ የኮንዶሚኒየምን ማሳወቂያና መግለጫ መተዳደሪያ ደንብና ውስጥ ደንብ ቅጂ መስጠት አለበት፡፡

## 23. አስቀድሞ ወደ ቤት ስለመግባት

የኮንዶሚኒየም ማሳወቂያና መግለጫ ከመመዝገቡና የቤት ባለቤትነት ስም ለገዢው ከመዛወሩ በፊት ገዢው ወደ ገዛው ቤት ስለመግባቱ በዚህም ጊዜ ገዢው ስለሚከፈለው ክፍያ እና ስለ አስመዝጋቢው ግዴታ በቤት ሽያጭ ውል ላይ ስምምነት ሊደረግ ይችላል፡፡

# ክፍል ስድስት

# ስለ ጋራ ወጪዎችና ትርፍ

## 24. በባለቤቶች የሚደረግ መዋጮ

1. የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የቤት ባለቤቶች የጋራ ወጪዎችን ለመሸፈን በጋራ መጠቀሚያዎች ላይ ካላቸው የማይከፋፈል ጥቅም ጋር የሚመጣጠን መዋጮ ይከፍላሉ፤
2. የቤት ባለቤት በጋራ መጠቀሚያዎች ላለመጠቀም የወሰነ ቢሆንም ወይም በቤት ባለቤቶች ማህበር በመተዳደሪያ ደንብ ወይም በውስጥ ደንብ በጋራ መጠቀሚያዎች የመጠቀም መብቱ በከፊል ወይም በሙሉ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 25. የመያዣ መብት

1. የቤት ባለቤት የጋራ መዋጮውን በማይከፍልበት ጊዜ ማህበሩ በባለቤቱ ቤትና በጋራ ጥቅሞች ድርሻው ላይ ባልተከፈለው መዋጮ መጠን የመያዣ መብት ይኖረዋል፡፡ ይህ የገንዘብ መጠን ክፍያው በተወሰነለት ጊዜ ባለመከፈሉ ምክንያት የሚኖረውን ወለድ እና ወጪዎች ይጨምራል፤
2. የቤት ባለቤት መዋጮውን መክፈል ከነበረበት ጊዜ አንስቶ ባለው የሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ማህበሩ በዚህ አዋጅ መሰረት በንብረቱ ላይ አለ የሚለውን የመያዣ መብቱን የሚያረጋግጥለት የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሰረት ያልተመዘገበ እንደሆነ የማህበሩ የመያዣ መብት የሶስት ወር ጊዜው ካለቀ በኃላ ተፈፃሚ አይሆንም፤
4. የማህበሩን የመያዣ መብት ለማረጋገጥ የሚሰጠው የምስክር ወረቀት የቤት ባለቤቶች ያልተከፈለውን የመዋጮ መጠን እና መዋጮውን ለማስከፈል ሲባል ማህበሩ ያወጣቸውን ልዩ ልዩ ወጪዎች ለይቶ ማመልከት ይኖርበታል፤
5. ማህበሩ የመያዣ መብት ከማስመዝገቡ በፊት ለሚመለከታቸው የቤት ባለቤቶች የ15 ቀናት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት፤
6. የቤት ባለቤቱ በዚህ አንቀጽ የሚፈለግበት ክፍያ ከፍሎ ሲያጠናቅቅ ማህበሩ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲመዘገብ በማድረግ ለቤት ባለቤቱ ሊሰጠው ይገባል፤
7. በዚህ አንቀጽ የተመለከተው የማህበሩ የመያዣ መብት ከመንግስት ግብርና ቀረጥ በስተቀር ከሌሎች ከተመዘገቡትም ሆነ ያልተመዘገቡ መያዣዎች ቅድሚያ ይኖረዋል፡፡

## 26. የጋራ ትርፍ

1. ማህበሩ የሚያገኘው ማንኛውም ትርፍ የጋራ ወጪዎችን ለመሸፈን ይውላል ወይም በልዩ ተቀማጭ ሂሳብ ውስጥ ይቀመጣል፤
2. ማህበሩ ካልፈረሰ በስተቀር ይህ ትርፍ በቤት ባለቤቶች መካከል አይከፋፈልም፡፡

## 27. ስለ ጥገናና እድሳት

1. **በአደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን ቤቶች ስለመጠገን፡-**
   - ሀ. በአደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን ቤቶች፣ የጋራ መጠቀሚያዎችን እና የማህበሩ ንብረቶችን ማህበሩ ማስጠገን አለበት፤
   - ለ. በአደጋ ምክንያት የሚደረግ ጥገና ጉዳት የደረሰበትን አካል መጠገን እና በአዲስ መተካትን ይጨምራል። ሆኖም በቤቶች ላይ የተደረገ ተጨማሪ ስራ ላይ የሚደርስ ጉዳትን መጠገንን አይጨምርም፤
   - ሐ. ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም በአንድ ቤት ላይ የተደረገ ተጨማሪ ስራ አይነትና መጠን የሚወሰነው በህንፃ ማሳወቂያ በተቀመጠው የቤቶች ደረጃ ጋር በማወዳደር ይሆናል፤
   - መ. የዚህ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ቢኖርም ህንፃው ከመመዝገቡ በፊት በቤቶች ላይ የተደረገ ተጨማሪ ስራዎች ቢኖሩ ማህበሩ የማስጠገን ኃላፊነት ይኖርበታል።
2. **ስለ እድሳት**
   - ሀ. ማህበሩ የጋራ መጠቀሚያዎችን የማደስ ኃላፊነት አለበት፤
   - ለ. እያንዳንዱን ቤት የማደስ ኃላፊነት የቤቱ ባለቤት ነው፤
   - ሐ. ለተወሰኑ ቤቶች የተመደቡ የጋራ መጠቀሚያዎችን ማደስ የጋራ መጠቀሚያዎቹ የተመደቡላቸው ቤቶች ባለቤቶች ኃላፊነት ነው፤
   - መ. የማደስ ኃላፊነት በመደበኛ የንብረት አጠቃቀም የሚመጣን ማርጀት ወይም አገልግሎት መቀነስ ማስተካከልን ይመለከታል።
3. **በቤት ባለቤቶች የሚደረግ እድሳት**
   - ሀ. የጋራ መጠቀሚያን ወይም ቤትን የማደስ ኃላፊነት የቤት ባለቤቱ ከሆነና በቂ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ይህንን ኃላፊነቱን ባይወጣ ማህበሩ እድሳቱን በራሱ ሊያከናውን ይችላል፤
   - ለ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሰረት ማህበሩ እድሳት ሲያከናውን ወጪው ኃላፊነቱን ያልተወጣው የቤት ባለቤት የጋራ ወጪ ተጨማሪ ድርሻው ሆኖ ይታሰባል።

## 28. ስለ ልዩ ተቀማጭ ገንዘብ

1. ማህበሩ ለጥገናና እድሳት ራሱን የቻለ የተለየ ገንዘብ ማስቀመጥ እና ሲያስፈልግ ወጪ ማድረግ አለበት፤
2. ለዚህ ተቀማጭ ገንዘብ ማህበሩ ከቤት ባለቤቶች መዋጮ ይሰበስባል፤
3. በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ተቀማጭ ገንዘብ የማህበሩ ሀብት ነው። በዚህ አዋጅ መሠረት ካልሆነ በቀር ለቤት ባለቤቶች አይከፋፈልም።

# ክፍል ሰባት
# ስለ ማህበራት ውህደት

## 29. ስለ ምዝገባ

1. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የቤት ባለቤቶች ማህበራት የተዋሀደ የኮንዶሚኒየም ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ ለመዝጋቢው አካል በማስመዝገብ ሊዋሃዱ ይችላሉ፤
2. ውህደቱ ከመመዝገቡ በፊት በእያንዳንዱ ማህበር የቤት ባለቤቶች 80 ፐርሰንት ድምፅ መፅደቁና ማህበራቱን ለመወከል ስልጣን ባላቸው ሰዎች መፈረሙ መረጋገጥ አለበት፤
3. ስለ ውህደቱ በሚጣራ ጠቅላላ ስብሰባ ለሚዋሀደው ማህበር የሚያገለግሉት የኮንዶሚኒየም ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ በውህደቱ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ለሚጠራው ጠቅላላ ስብሰባ ቀርበው መፅደቅ አለባቸው፤
4. የሚዋሀዱት ማህበራት የመጨረሻ አመት የኦዲት ሪፓርት በንዑስ አንቀጽ 3 ላይ በተጠቀሰው ስብሰባ ላይ ለአባላት መግለጽ አለበት።

## 30. ምዝገባው የሚያስከትለው ውጤት

1. ውህደቱን የመሰረቱት ማህበራት በሙሉ ተዋህደው የተዋሀደ አንድ የቤት ባለቤቶች ማህበር ይመሰረታል፤
2. ከውህደት በፊት የነበሩት ቤቶች እና የጋራ መጠቀሚያዎች የተዋሀደው ማህበር ቤቶችና የጋራ መጠቀሚያዎች ሆነው ይቀጥላሉ፤
3. ከውህደቱ በፊት የነበሩት የእያንዳንዱ ማህበር የኮንዶሚኒየም ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ ተፈፃሚነታቸው ይቀራል፤

www.chilot.me

4. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 31 እንደተጠበቀ ሆኖ ከውህደቱ በፊት የነበሩት የእያንዳንዱ ማህበር ዳሬክተሮች በአንድ ላይ የተዋሀደው ማህበር የመጀመሪያ ዳሬክተሮች ይሆናል፤
5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 31 መሰረት ምርጫ እስከሚከናወን የሚያገለግሉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ኦዲተሮች በአባላት ይሰየማሉ፤
6. ውህደቱን የመሠረተው የእያንዳንዱ ማህበር መብትና ግዴታዎች ለተዋሃደው ማህበር ይተላለፋሉ፤

## 31. ዳሬክተሮችንና ኦዲተሮችን ስለመምረጥ

የተዋሀደው ማህበር የኮንዶሚኒየም ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ በተመዘገበ በ90 ቀናት ውስጥ የተዋሀደው ማህበር ቤት ባለቤቶች በጠቅላላ ስብሰባ ለተዋሀደው ማህበር የዳሬክተሮች ቦርድ አባላትና ኦዲተሮች መምረጥ አለባቸው፡፡

# ክፍል ስምንት
# ኮንዶሚኒየም ቢዚህ አዋጅ መሰረት መተዳደሩ ስለሚያበቃበት ሁኔታ

## 32. የቤት ባለቤቶች ፍቃድ

ድምጽ በሚሰጥበት ጊዜ ቢያንስ 80 ፐርሰንት የሆኑት ባለቤቶች የጋራ ህንፃው በዚህ አዋጅ መሰረት መተዳደሩ እንደያበቃ በማለት ድምጽ ከሰጡ ማህበሩ ይህንኑ የሚገልጽ የጽሁፍ ማስታወቂያ ለመዘገቢው አካል ማቅረብ አለበት፡፡

## 33. ከፍተኛ ውድመት

1. ቦርዱ በኮንዶሚኒየም ላይ ከፍተኛ ውድመት ደርሷል ብሎ በሚወስንበት ጊዜ ጉዳዩን ለቤት ባለቤቶች ጠቅላላ ስብሰባ በማቅረብ ስለውደመቱ መጠን እና ከውድመቱ በኋላ ኮንዶሚኒየሙ በዚህ ህግ መገዛቱን ያቆም እንደሆነ ማስወሰን አለበት፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሰረት በሚደረገው የባለቤቶች ሰብሰባ ከ80 ፐርሰንት በላይ የሆኑት ቤቶች ባለቤቶች ኮንዶሚኒየም በዚህ ህግ መገዛቱ እንዲያበቃ ከወሰኑ ቦርዱ ይህንኑ የሚገልጽ የጽሁፍ ማስታወቂያ ለመዝጋቢው አካል ማቅረብ አለበት፤
3. የቤቶች ባለቤቶች በዚህ አንቀጽ በተገለጸው ድምፅ መጠን ኮንዶሚኒየም በዚህ ህግ መገዛቱን እንዲያቆም በማለት ካልወሰኑ ቦርዱ በቂ በሆነ ጊዜ ውስጥ ውድመቱ እንዲጠገን ማድረግ አለበት፡፡

## 34. ስለ ሽያጭ

1. የኮንዶሚኒየም ወይም የተወሰነው የጋራ መጠቀሚያ በሚሸጥበት ጊዜ ይህ ህግ በተሸጠው ኮንዶሚኒየም ወይም የጋራ መጠቀሚያ ላይ ተፈፃሚ መሆኑ ያበቃል፤
2. ማህበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ በተደነገገው መሰረት ሽያጭ ለማከናወን፡-
   ሀ. ድምፅ በተሰጠበት ዕለት 80 ፐርሰንት የሆኑትን የቤት ባለቤቶች አዎንታ ድምፅ እና፤
   ለ. ሽያጩ ለተወሰኑ ቤቶች አገልግሎት ተለይተው በተጨማሪ የጋራ መጠቀሚያ ተለይቶ የተሰጣቸው ቤቶች ባለቤቶችን የእያንዳንዳቸው ፈቃደኝነት በጽሁፍ ማግኘት አለበት፡፡

## 35. ለሕዝብ ጥቅም ንብረት ስለመውሰድ

በህግ መሰረት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የተወሰደ የኮንዶሚኒየም ወይም የጋራ መጠቀሚያ በዚህ ህግ መገዛቱ ያበቃል፡፡

## 36. ከሽያጭና ከንብረት መወሰድ ስለሚገኝ ጥቅም

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 34 ወይም አንቀጽ 35 መሰረት የኮንዶሚኒየሙ ወይም የተወሰነው የጋራ መጠቀሚያ በመሸጡ ወይም በመወሰዱ የሚገኘው ጥቅም በጋራ መጠቀሚያዎች ላይ ባላቸው የመቶኛ ጥቅም ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መጠን ለቤት ባለቤቶች ይከፋፈላል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ቢኖርም የተሸጠው ወይም የተወሰደው ለተወሰኑ ቤቶች መጠቀሚያነት ብቻ ተለይቶ የተተወ የጋራ መጠቀሚያ በሆነ ጊዜ ጥቅሙ የሚከፋፈለው የጋራ መጠቀሚያው ተለይቶ በተሰጣቸው ቤቶች መካከል ብቻ ይሆናል፡፡

## 37. ስለ ምዝገባ

1. መዝጋቢው አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 ወይም 33 መሰረት የሚቀርብለትን ማስታወቂያ መርምሮ በመመዝገብ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
2. የምስክር ወረቀቱ እንደተሰጠ ይህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ሌሎች ህጎች በኮንዶሚኒየሙ ላይ ተፈፃሚነታቸው ያበቃል፡፡

## 38. ስለ ሐብት ክፍፍል

ኮንዶሚኒየሙ በዚህ አዋጅ መገባቱ ስያበቃ፡-

1. የቤት ባለቤቶች ማህበር ሀብት በማህበሩ ላይ የሚነሱ የገንዘብ ጥያቄዎችን ለመክፈል ይውላል፤
2. ቀሪው የማህበሩ ሀብት በጋራ ጥቅማቸው መጠን ለቤት ባለቤቶች ይከፋፈላል።

## ክፍል ዘጠኝ
## ኮንዶሚኒየም ለመስራት ስለሚደራጁት የመኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበራት

## 39. አደረጃጀት

የመኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበራት ኮንዶሚኒየም በመስራት ዓላማ ሊደራጁ ይችላሉ።

## 40. የህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ተፈፃሚነት

1. ኮንዶሚኒየም ለመስራት ለሚደራጁ የህብረት ስራ ማህበራት ስለመኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበራት በአዋጅ ቁጥር 147/91 የተደነገገው ተፈፃሚ ይሆናል፤
2. ሆኖም ህንፃው በዚህ አዋጅ መሠረት ሲመዘገብ ይህ አዋጅ ተፈፃሚ ይሆናል።

## 41. ህንፃ ስለማስመዝገብ

1. ኮንዶሚኒየም ግንባታ ሲጠናቀቅ የህብረት ስራ ማህበሩ የስራ አመራር ኮሚቴ ኮንዶሚኒየምን በዚህ አዋጅ መሰረት ያስመዘግባል፤
2. በዚህ አዋጅ መሰረት ኮንዶሚኒየምን ያስመዘገበው የስራ አመራር ኮሚቴ የባለቤቶች ማህበር የመጀመሪያ ቦርድ በመሆን በዚህ ህግ ለቦርዱ የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤
3. የህብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 147/91 መሰረት የተመረጠው የቁጥጥር ኮሚቴ በዚህ አዋጅ መሰረት ኦዲተር ሆኖ ይሰራል፤
4. ኮንዶሚኒየሙ በተመዘገበ በ90 ቀናት ውስጥ የቤት ባለቤቶች አዲስ የዳይሬክተሮች ቦርድና ኦዲተር ሊመርጡ ይችላሉ።

## ክፍል አስር
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 42. ደንብ ስለማውጣት

የክልል መስተዳድሩ ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዳ ደንብ ለማውጣት ይችላል።

## 43. ስለሌሎች ህጎች ተፈፃሚነት

1. በ1952 ዓ/ም የወጣው የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ህግ ከቁጥር 1281 እስከ ቁጥር 1308 ያሉ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ መሰረት ለሚተዳደር ኮንዶሚኒየም ላይ ተፈፃሚነት አይሆኑም፤
2. ማንኛውም ህግ፣ ልማድ ወይም አሰራር በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፋፃሚነት አይኖረውም።

## 44. አዋጅ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**ሐረር መጋቢት 11 ቀን 1999 ዓ.ም**

**ሙራድ አብዱልሃዲ**

**የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት**

**ፕሬዝዳንት**

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| 11ኛ ዓመት ቁጥር 12<br>11th year No 12 | | ሐረር ህዳር 6/1999<br>Harar , nov 15/2006 |
| ያንዱ ዋጋ ብር 6:30<br>Unit prieoe Bre.6:30 | በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት<br>ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 952<br>P.O.Box 952 |

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 63/1999 ዓ/ም

የሐረሪ ህ/ክ/ መንግስት የቤቶች ል/ፕ/ ጽ/ቤት የሚገነባቸውን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነትና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

—— ገጽ 491

## አዋጅ ቁጥር 63/ 1999

## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤቶች ልማት ፕ/ጽ/ቤት የሚገነባቸውን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነትና አፈፃፀሙን ለመወሰን ያወጣ አዋጅ

የክልሉ መንግስት በግል ባለሀብቶችና አቅም ባላቸው ሌሎች አካላትና ሰዎች በማህበርም ሆነ በተናጠል መኖሪያ ቤቶች እንዲገነቡ አስፈላጊ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የከተማ ነዋሪዎችን ከፍተኛ የመጠለያ ችግር ለመቅረፍ እየሰራ ያለ በመሆኑ፤

ከዚህ ጎን ለጎን የመንግስትም ሆነ የግል ንብረት የሆነና የመሰረተ ልማት አገልግሎት በተሟላ ሁኔታ የማያገኙ ቤቶችን ተክቶ ከተሞችን መልሶ በማልማትና በከተሞች ውስጥ ከድህነት መገለጫዎች መካከል አንዱ የሆነውን የአብዛኛዎቹን የከተማ ነዋሪዎች ከፍተኛ የመጠለያ ችግር ትርጉም ባለው መልኩ በመቅረፍ ከተሞችን ተስማሚ የመኖሪያና የስራ አካባቢ እንዲሆኑ ለማድረግ የክልሉ መንግስት የከተማ ነዋሪዎችን ያኗኗር ደረጃና ፍላጎት ግምት ውስጥ አስገብቶ ባወጣው የቤት ልማት ፕሮግራም መሰረት በከተሞች የቤቶች ግንባታ በማካሄድ ላይ ያለ በመሆኑ፤

ፍትሐዊ፤ ግልጽ ፤ቀልጣፋና ውጣ ውረድ በሌለው ቀላል በሆነ ስነ-ስርአት፤ እንዲሁም የተጠቃሚዎችን የዖታ ተዋጽኦ በሚያረጋግጥና የገቢ አቅም ግምት ውስጥ በሚያስገባ የክፍያ መጠንና የአከፋፈል ሁኔታ የተገነቡ ወይም የሚገነቡ ቤቶች ለከተማ ነዋሪዎች የሚተላለፍበትንና የቤት ባለቤት የሚሆኑበትን አፈፃፀም መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በተሻሻለው የሐረሪ ሕዝብ ክልል ሕገ-መንግስት አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ (2)(ሀ) በተደነገገው መሰረት በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ይህ አዋጅ ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት የቤቶች ልማት ፕ/ጽ/ቤት የሚገነባቸውን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነትና አፈፃፀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 63/1999›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

www.chilot.me

## 2. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

1. "ቤት ፈላጊ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በክልሉ መንግሥት አካላት ቤት ያልተላለፈለት ሰው ሆኖ፤
   ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 በተመለከተው መሰረት ማመልከቻ እስካቀረበበት ቀን ድረስ በክልለ ወይም የክልሉ ተወላጅ ሆነው በተለያየ ምክንያት ከክልሉ ውጪ ስኖሩ ቆይተው የተመለሱ እና በክልሉ የእራሳቸው የሆነ የግል ቤት ወይም መሥሪያ ቦታ የሌለው፤ ወይም
   ለ. የግል መኖሪያ ቤቱ፤ የቤት መስሪያ ቦታ ወይም የተከራየው የመንግሥት ቤት በከተማው የቤት ልማት ፕሮግራም ወይም ለሌላ የልማት ስራ ምክንያት የሚነሳበትና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 መሠረት ቤት ለመግዛት ማመልከቻ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ሲሆን፣ በሥራ ወይም በትምህርት ምክንያት ለጊዜው ይኖሩበት ከነበረው ከተማ ውጪ የሚኖር ሰውን ይጨምራል።
2. «ቤት» ማለት በኮንደሚኒየም ማሳወቂያና መግለጫ ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት የተመደበ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ክፍሎች ያሉት የኮንደሚኒየም አካል ነው።
3. «ኮንደሚኒየም» ማለት ከመሬት ወደ ላይ ወይም ጎን ለጎን የተሰሩ በተናጥል የሚያዙ አምስትና ከአምስት በላይ ቤቶች እና በጋራ ባለቤትነት የሚያዙ የጋራ መጠቀሚያዎች ያሉት ለመኖሪያ ወይም ለአገልግሎት የሚውል ግንባታ ስሆን ኮንደሚኒየም ያረፈበትን የቦታ ይዞታ ይጨምራል።
4. « የጋራ መጠቀሚያ» ማለት በተናጥል ከተያዙት ቤቶች ውጪ ያለ ማናቸውም የኮንደሚኒየም አካል ነው።
5. "ስቱዲዮ" ማለት የግል መፀዳጃ ክፍልና ማዕድ ቤት በውስጡ ወይም ከውጪ እንዲኖረው ተደርጎ የተሰራና የኮንደሚኒየም አካል የሆነ ባለ አንድ ክፍል መኖሪያ ቤት ነው።
6. «ክልል» ማለት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 47 (1)(9) መሰረት የተቋቋመው የሐረሪ ሕዝብ ክልል ማለት ነው።
7. "አዋጅ" ማለት የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት የኮንዶሚኒየም ባለቤትነት አዋጅ ቁጥር 62/1999 ነው።
8. "የመንግሥት ቤት" ማለት በክልሉ ማንኛውም አካል ወይም በኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት /በቤቶች ልማት ድርጅት/ ለቤት ፈላጊ የተከራየ በከተሞች ውስጥ የሚገኝ ቤት ነው።
9. "የግንባታ ወጪ" ማለት የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ለእያንዳንዱ ተጠቃሚ የሚያገለግለውን ቤት ለመገንባት ብቻ ያወጣው ወይም የሚያወጣው ወጪ ነው።
10. « ጽሕፈት ቤት » ማለት የክልሉ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ነው።
11. «ማህበር» ማለት በከተማ አቀፍ ደረጃ የተመሰረተ ቁጠባ ብድር ህብረት ስራ ማህበራት፤ ህብረት ወይም መሰረታዊ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት ወይም በከተማ አቀፍ ደረጃ የተመሠረተ የዕድሮች ህብረት ወይም ማናቸውም ዕድር ነው።
12. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።
13. "ቦርድ" ማለት የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት የበላይ ቦርድ ነው።

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት በሚገነቡ ቤቶች ተጠቃሚዎችና ከቤቶቹ አስተዳደር ጋር ግንኙነት ባላቸው ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## 4. በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

## ክፍል ሁለት

## ቤት ፈላጊዎችን መመዝገብና በክልሉ የቤቶች ል/ፐ/ጽ/ቤት የተገነቡ ቤቶችን የማስተላለፍ አፈፃፀም

5. የቤት ፈላጊዎች ማመልከቻ ቅጽ ይዘትና አቀራረብ

1. ማንኛውም ቤት ፈላጊ፦

ሀ- አባል በሆነበት ማህበር፤ ከጽህፈት ቤቱ /ከማዘጋጃ ቤት/ከተማ አስተዳደር ማመልከቻ በማንባር ቀርቦ በመመዝገብ መኖሪያ ቤት በተከፋፈለ የረጅም ጊዜ ክፍያ ወይም በአንድ ጊዜ ክፍያ ከጽህፈት ቤቱ ለመግዛት እንደሚፈልግ ሊያሳውቅ ይችላል፤

ለ- ንግድ ቤት ለመግዛት ወይም ለመከራየት የሚፈልግ ከሆነ ደግሞ በክልሉ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ህግ እንደተደነገገው በጨረታ ማስታወቂያ በሚገለፀው መሠረት አግባብነት ያለውን የንግድ ቤት ግዢ ወይም የኪራይ ማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ለጽህፈት ቤቱ ማመልከት ይችላል።

2. ቤት ፈላጊ በመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ማመልከቻ ቅጽ የሚከተሉትን ዝርዝሮች መግለጽ ይኖርበታል።

ሀ- ሙሉ ስሙን ከነአያቱ፣ የመኖሪያና የስራ አድራሻውን፤

ለ- ያገባ ከሆነ የትዳር ጓደኛውን ሙሉ ስም ከነአያት፤

ሐ- በዚህ አዋጅ መሠረት ቀደም ብሎ ከጽህፈት ቤት ያልተላለፈለት መሆኑን፤

መ- በሚኖርበት ከተማ ውስጥ የግል መኖሪያ ቤት ወይም የቤት መሥሪያ ቦታ ያለው ወይም የሌለው መሆኑን፤

ሠ- በቤቶች ልማት ፕሮግራም ወይም በሌላ የልማት ሥራ ምክንያት በከተማው ውስጥ የሚገኝ የግል ቤቱን ወይም ቤት መስሪያ ቦታውን የሚለቅ መሆኑን፤

ረ- ማመልከቻ እስካቀረበበት ቀን ድረስ በተከታታይ በሚኖርበት ከተማ ወይም በከተማው ዙሪያ አካባቢ ቢያንስ 2 ዓመት የኖረ መሆኑን፤ ካልኖረ ደግሞ ከክልሉ ውጪ የኖረበትን የሥራ ወይም የትምህርት ሁኔታ እና የትና ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ ወይም እንደሚቆይ፤

ሰ. ለመግዛት የሚፈለገውን የቤት ዓይነትና የክፍል ብዛት፤

ሸ. የወርሃዊ ገቢውን መጠንና ምንጭ፤

ቀ- የቤቱን ዋጋ በአንድ ጊዜ ወይም በተከፋፈለ ረጅም ጊዜ ክፍያ የሚከፍል መሆኑን፤ እንዲሁም፤ የተከፋፈለ ክፍያ የሚከፈል መሆኑን፤ እንዲሁም የተከፈለ የረጅም ጊዜ ክፍያ በሚሆንበት ጊዜ በዚህ አዋጅ መሠረት ቅድሚያ ክፍያ ለመክፈልና የተከፋፈለውን ክፍያ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ክፍሎ ለማጠናቀቅ ፈቃደኛ መሆኑን፤

በ- የቤቱን ዋጋ ክፍያ ከተወሰነው ጊዜ ቀደም ብሎ ቢጠናቀቅም የገዛውን የመኖሪያ ቤት በመጀመሪያዎቹ 5 ዓመታት ውስጥ በሽያጭ ወይም በስጦታ ለሦስተኛ ወገን ላለማስተላለፍ ፈቃደኛ መሆኑን፤

ተ. በአዋጁመሠረት ለመተዳደር ፈቃደኛ መሆኑን ፤

ቸ. የሚኖረው በመንግሥት ቤት ከሆነ ቤቱን ለሚያስተዳድረው አካል የገዛውን ቤት ከመረከቡ ከ30 ቀን በፊት ለማስረከብ ፈቃደኛ መሆኑን፤እና

ኀ- በማመልከቻው ቅጽ የሞላው ዝርዝር ሐሰተኛ ሆኖ ቢገኝ ውሉ ቲቋርጦ የገዛውን ቤት በመልቀቅ ለሻጩ ለማስረከብ ከከፈለው ገንዘብ ላይ ለቤቱ ዕድሳት የሚያስፈልገው ወጪና ለቆየበት ጊዜ በጽህፈት ቤቱ በሚወጣ መመሪያ በሚወሰነው የኪራይ ተመን መሠረት ለቤቱ የሚሰላ የኪራይ ዋጋ ተቀንሶ ቀሪው ብቻ እንዲመለስለት የሚፈቅድ መሆኑን፤

3. ቤት ፈላጊው በማመልከቻ ቅጽ ላይ የሞላው ዝርዝር ዕውነተኛና ትክክለኛ መሆኑን በፊርማው ማረጋገጥ አለበት።

6. ቤት ፈላጊዎችን ማጣራትና መመዝገብ

1. ማንኛውም ቤት ፈላጊ በማመልከቻ ቅጽ የሞላው ዝርዝር በከተማው አስተዳደር /ማዘጋጃ ቤት/ የመረጃ ማዕከል ካለው መረጃ ጋር እንዲገናዘብ በማድረግ፣ የግል መኖሪያ ቤት ወይም የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንደሌለው፣ እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት በአራሱ ስም ወይም በጋብቻ ውስጥ እያለ በትዳር ጓደኛው ስም የተገዛ የመኖሪያ ቤት እንደሌለው ጽህፈት ቤቱ ያጣራል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ መሠረት ከሚደረገው ማጣራት በተጨማሪ ጽህፈት ቤቱ፤

ሀ· አመልካች በሚኖርበትና ማመልከቻ ቅጽ በሞላበት ቀበሌ ነዋሪዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ለ10 ቀናት በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለጥፎ ከሚሰጠው አስተያየት ጋር ማመልከቻውን ያገናዝባል፤

ለ· አመልካች የማመልከቻ ቅጽ በሞላበትና አባል በሆነበት ማህበር ሌሎች አባላት አስተያየት ጥቆማ/ ካላቸው እንዲያቀርቡ ስሙ በማስታወቂያ እንዲወጣ ያደርጋል፤አስተያየቱንም ይመረምራል፤

3. ቤት ፈላጊው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ በተመለከተው መሠረት በሚደረገው ማጣራት በማመልከቻው ቅጽ የሞላው ዝርዝር ትክክለኛ መሆኑን ሲረጋገጥ ጽህፈት ቤቱ በሚወስነው መሠረት በቤት ፈላጊዎች መዝገብ አመልካች ይመዘገባል፤ በጽህፈት ቤቱ ማስታወቂያ ሠሌዳ ስሙ ይፋ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሠረት የመኖሪያ ቤት የመግዛት መብት ያገኛል።

## 7. የቅድሚያ አወሳሰን

ጽህፈት ቤቱ ያሉትን ቤቶች ብዛት መሠረት በማድረግ፤

1. በልማት ምክንያት ለሚነሱ ቤት ፈላጊዎች በከተማ አስተዳደር (ማዘጋጃ ቤት) በሚቀርብ ጥያቄ መነሻ የክልሉ አስተዳደር በሚወስነው መሠረት የተወሰነ የቤቶች ድርሻ በልዩ ሁኔታ ተይዞላቸው ቤቶቹን የመግዛት የቅድሚያ መብት ይኖራቸዋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት በቅድሚያ መብት ተጠቃሚ ከሚሆኑ ቤት ፈላጊዎች መካከል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት ከተመዘገቡት ውስጥ ያሉ ከሆነ ቢያንስ 20% እማወራዎች ይሆናሉ፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ቢኖርም የቤቱን ሽያጭ ጠቅላላ ዋጋ በአንድ ጊዜ ክፍያ ወይም ከተወሰነው የተሻለ ቅድሚያ ክፍያ የሚፈፀም ገዥ አንድና ከአንድ በላይ መኝታ ቤት የመግዛት እንደ አስፈላጊነቱ የቅድሚያ መብት ያገኛል፤
4. ማናቸውም ማህበር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ /1/ እንደተመለከተው ጠቅላላ የሽያጭ ዋጋ ክፍሉ በመግዛት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 በተደነገገው መሠረት ለቤት ፈላጊ አባላቱ የሚያከፋፍላቸው የተወሰኑ ቤቶች ሊመደቡለት ይችላሉ።

## 8. የጽህፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ጽህፈት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 56/1998 የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፤

1. የተገነቡ ወይም በግንባታ ላይ ያሉ የመኖሪያ ቤቶችና የንግድ ቤቶችን ለይቶ በመያዝ ለሽያጭ ያዘጋጃል፤ ወይም በማዘጋጃ ቤቱ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ያስተዋውቃል፤
2. የገነባቸውን ቤቶች በአዋጁ መሠረት ያስመዘግባል ወይም ውክልና በሰጠው ሌላ አካል አማካኝነት አስፈላጊው ተሟልቶ እንዲመዘገቡ ያደርጋል፤ በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ ቤት ፈላጊዎችን ብዛትና ቁጥር ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ያደራጃል፤ ወይም በየቀበሌው እንዲደራጁ ያደርጋል፤
3. በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ ቤት ፈላጊዎችን ብዛትና ቁጥር ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ያደራጃል፤ወይም በየቀበሌው እንዲደራጁ ያደርጋል፤
4. ከመረጃውም በመነሳት የቤት ፈላጊዎችን ብዛትና ክፍፍል እንዲሁም የተጠናቀቁና በመገንባት ላይ ያሉ ቤቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ለቤት ፈላጊዎች ሊከፋፈል ስለሚገባው ድርሻና የመምረጫ መስፈርቶችን አስመልክቶ በቤት ፈላጊዎች ማመልከቻ ቅፆች በሚገኘው መረጃ ላይ በመመስረት የውሳኔ ሃሳብ በየጊዜው እያዘጋጀ ለቦርዱ ያቀርባል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
5. መኖሪያ ቤት ለቤት ፈላጊ የሚተላለፍበት ውል በማዘጋጀት የሚገዛውን ቤት ከለየ ከቤት ገዢ ጋር ውል ይፈራረማል፣ ወይም ለሌላ አግባብ ላለው አካል ውክልና ይሰጣል፣ በሚሰጠው ውክልናም ውል ባፈረሰ ቤት ገዢ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 ንዑስ

አንቀጽ /2/ በተመለከተው መሠረት ተወካዩ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ መፍቀድ ይችላል፣ ተወካዩ ውሉን በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋሉን ያረጋግጣል፤

6. ቤት ገዢዎች በፈረሙት ውል መሠረት እንደየ አግባቡ ቅድሚያ ክፍያ ወይም ጠቅላላ ዋጋ እንዲከፍሉና በመረጡት ህንፃ ውስጥ ለሚገኝ ፎቅና ዓይነት ለእያንዳንዳቸው የሚደርሰው ቤት ተለይቶ ውል እንዲዋዋሉና እንዲረከቡ ያደርጋል፤ ወይም መደረጉን ያረጋግጣል፤

7. የንግድ ቤት ለመግዛት ወይም ለመከራየት በጨረታ ተወዳድሮ ካሸነፈ ማንኛውም ቤት ፈላጊ ጋር እንደየ አግባቡ የቤት ሽያጭ ወይም ኪራይ ውል ይፈራረማል፣ ወይም ሌላ አግባብ ላለው አካል እንዲፈረም ውክልና ይሰጣል፣ የተከራዩ ንግድ ቤቶችንም የክልሉ መንግሥት በሚያወጣው የመንግሥት ቤቶች አስተዳደር አዋጅ በሚደነግገው መሠረት መተዳደራቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

8. ማናቸውም ቤት ገዢ በውሉ መሠረት ክፍያውን ማጠናቀቁ ሲረጋገጥ ለገዛው ቤት የቦታ ይዞታና የማይንቀሳቀስ ንብረት ምስክር ወረቀት እንደየ አግባቡ በከተማው አስተዳደር/በማዘጋጃ ቤት/ እንዲሰጠው ያስተላልፋል፤መሰጠቱንም ይከታተላል፡፡

9. ለነዋሪዎቹ የጋራ አገልግሎት እንዲሰጥ የተሠራ የጋራ መጠቀሚያ ኮንዶሚኒየምን በአዋጁ መሠረት ለተመዘገበ የባለቤቶች ማህበር ወይም ለንግድ ማህበር በሽያጭ ውል መተላለፉንና አገልግሎቱን ሳይለውጥ ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

10.በህጋዊ ደረሰኝ ቅድሚያ ክፍያና ቀሪ ክፍያ እንዲፈፀምና በክልሉ መንግሥት የፋይናንስ አዋጅ ቁጥር 9/1991 መሠረት ገቢ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፣ ይህንንም እንደየ አግባቡ እራሱ ተዋውሎ ለሸጠው ቤት ክፍያ በመቀበል ወይም ገዢዎች ክፍያ የሚፈጽሙበት ባንክ ወይም ሌላ የክፍያ

ጣቢያ በመወከል ያስፈጽማል፤

11. ማናቸውም ቤት ገዢ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 በተደነገገው መሠረት ውል ማፍረሱን ሲያረጋግጥ

ሀ- ውሉን በማቋረጥ ከተረከበው ቤት እንዲለቅ ያደርጋል፤ ወይም ውክልና በመስጠት በሌላ አካል እንዲፈጸም ያደርጋል፣ በውክልናው መሠረት መፈፀሙን ያረጋግጣል፤

ለ- ከከፈለው ገንዘብ ላይ ለቤቱ ዕድሳት የሚያስፈልገው ወጪና ለቆየበት ጊዜ በሚወጣው መመሪያ ላይ በሚወሰነው የኪራይ ተመን መሠረት ለቤቱ የሚሰላ የኪራይ ዋጋ ተቀንሶ ቀሪው ብቻ እንዲመለስለት ያደርጋል፤ ወይም መደረጉን ያረጋግጣል፤

ሐ- በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 በተደነገገው የቅድሚያ አወሳሰን መሰረት ለሌላ ቤት ፈላጊ ውል ፈርሞ እንዲተካ ያደርጋል፤ መደረጉን ያረጋግጣል፡፡

12. ቤት ፈላጊ ለአበዳሪ ተቋም በዋስትና በማስያዝ ቤት ለመግዛት እንደሚፈልግና ጽህፈት ቤቱ ለተቋሙ የቤቱን ግምት እንዲያሳውቅለት በማመልከቻ ሲጠየቅ፤ ተቋሙ ቤቱን በዋስትና ይዞ ለቤት ፈላጊው ገንዘብ ካበደረውና ቤት ፈላጊው የቤቱን ሙሉ ዋጋ መክፈል ከቻለ ጽህፈት ቤቱ ቤት የሚሸጥለት መሆኑን በማረጋገጥ የቤቱ የባለቤትነት ማስረጃ በዋስትና መያዣ ውሉ መሠረት እንዲያዝ ለተቋሙ እንደሚያስተላልፍ ወይም እንዲተላለፍ እንደሚ ያደርግ ገልፆ ለተቋሙና ለገዢው በጽሁፍ ያስታውቃል፡፡

## 9. <u>የከተማ አገልግሎት ጽህፈት ቤት (ማዘጋጃ ቤት) ሥልጣንና ተግባር</u>

የከተማ አገልግሎት ጽህፈት ቤት (ማዘጋጃ ቤት)፡

1. በከተማው አስተዳደር በቤት ልማት ፕሮግራም ምክንያት ከመኖሪያ ቦታቸው የሚነሱ የከተማውን ነዋሪዎች ማህበራዊና ኢኮኖሚ አቋም የሚያመለክቱ መረጃዎችን መዝግቦ ይይዛል፤

2. ምትክ ቦታና የገንዘብ ካሣ፤ ወይም ምትክ ቤት ወይም የገንዘብ ካሣ ብቻ እንዲከፈለው የሚፈልግና ቤት መግዛት የማይፈልግ ማንኛውም ተነሺ ከመኖሪያ ቦታቸው የሚነሱ ሰዎች ማመልከቻ ቅጽ በማስሞላትና ተገቢውን ማጣራት በማድረግ መዝግቦ ዝርዝራቸውን ለጽህፈት ቤቱ ያስተላልፋል፤

www.chilot.me

3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሲጠየቅ ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት ለገዛ ሰው የቦታ ይዞታና የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ ምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ ይሠጣል፤

4. የቤቱ የይዞታና የማይንቀሳቀስ ንብረት ምስክር ወረቀት ለአበዳሪ ተቋማት እንዲተላለፍና በዋስትና እንዲያዝ በጽህፈት ቤቱ ሲጠይቅ ወይም እንደ የሁኔታው ጽህፈት ቤቱ በቤት ፈላጊው ማመልከቻ መነሻ ሲጠይቀው ምስክር ወረቀቱን አዘጋጅቶ ለተቋሙ ያስተላልፋል፤ ቤት ፈላጊው ከተቋሙ ሲበደርም ከተቋሙ ጋር በተፈራረሙት ውል መሠረት የዋስትና መያዣውን ይመዘግባል፤

5. ለገገር በሚሰጠው የይዞታና የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ላይ እስከ አምስት ዓመት በሽያጭ ወይም በስጦታ አይተላለፍም፤ የሚል መግለጫ ይፃፍበታል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የገገሮች መብትና ግዴታ

10. **በመንግሥት ቤት የሚኖር ገገር ግዴታ**

1. ገገሩው በመንግሥት ቤት የሚኖር ከሆነ በሌሎች ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚኖርበትን የመንግሥት ቤት በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (2) በፊደል (ቸ) በተጠቀሰው መሠረት ሲያስረክብ በዚህ አዋጅ መሠረት የገዛውን ቤት ከአንድ ወር በኃላ መረከብ ይችላል፤

2. በመሆኑም፤ ገገሩው ስለሚኖርበት የመንግሥት ቤት ተፈላጊውን መረጃ ለዚሁ ዓላማ በሚዘጋጀው ቅጽ (ሶስት ቅጂ) ቤቱ በሚገኝበት ቀበሌ ጽህፈት ቤት በግንባር ተገኝቶ በመሙላት እና የቀበሌውን ማረጋገጫ በማሟላት፤ እነዚህም ቅጂዎች ለጽህፈት ቤቱ ወይም ቤት ለሸጠለት በጽህፈት ቤቱ ለተወከለ ሌላ አካል፤ ቤቱን ለሚያስተዳድረው የመንግሥት አካል እና የማህበር አባል ከሆነ ደግሞ ለማህበሩ ለእያንዳንዳቸው አንድ ቅጂ ማስረከብ አለበት፡፡

11. **ክፍያ ያጠናቀቀ ገገር መብትና ግዴታ**

1. በተከፋፈለ ተከታታይ ክፍያ ገዝቶ የቤቱን ዋጋ ያጠናቀቀ ገገር የቦታ ይዞታና ቤቱን የባለሃብትነት ምዝገባ ወረቀት ከጽህፈት ቤቱ ወይም ጽህፈት ቤቱ ውክልና ከሚሰጠው የክፍያ ጣቢያ ወይም ማስረጃውን በመያዣነት ከያዘው አካል መውሰድ የሚችልበት ሁኔታ ይመቻቻል፤

2. ገገሩው የቤቱን ጠቅላላ ዋጋ ቢከፍልም ቤቱን ለሦስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ የሚችለው ቤቱን ከገዛ 5 ዓመት ሲሞ ላው ብቻ ይሆናል፡፡ 5 ዓመት መሙላቱን እና ክፍያ ስለማጠናቀቁ በጽህፈት ቤቱ የተሰጠውን ማስረጃ ለሚመለከተው ሁሉ በማቅረብ ማረጋገጥ ይችላል፡፡

12. **የወራሾች መብት**

ወራሹ /ሾቹ/ በህግ መሠረት ተተክተው የመብቱና የግዴታው ባለቤቶች ይሆናሉ፡፡

## ክፍል አራት

## የክፍያ መጠንና የአከፋፈል ሁኔታ፤ እንዲሁም የማገባታ ወጪ ስሌትና አሸፋፈን

13. **የቅድሚያ ክፍያ መጠን፤ እንዲሁም የቀሪ ክፍያና የችሮታ ጊዜ**

1. ማንኛውም አይነት ቤት ገገር ከባንክ ብድር ለማግኘት እና ቤት ለመረከብ የሚያስችል የቅድሚያ ክፍያ የቤቱን ጠቅላላ ዋጋ 20 በመቶ ይከፍላል፤

2. በየጊዜው ለሚገነቡና በዚህ አዋጅ መሠረት ለቤት ፈላጊዎች ለሚተላለፉ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተወሰነው መጠን ሳይወርድ በጽህፈት ቤቱ በሚቀርብ የውሳኔ ሃሳብ መሠረት በክልሉ መንግሥት መስተዳድር ም/ቤት በሚወጣ ደንብ ለየቤቱ ዓይነት የሚከፈለው የቅድሚያ ክፍያ መጠን ሊጨምር ይችላል፤

3. ቅድሚያ ክፍያ ከተከፈለ በኋላ ቀሪው የቤቱ ዋጋ እንደየ ቤቱ ዓይነትና መጠን ገዢው ቤቱን ከተረከበበት ቀን በኋላ የተሰጠው የችሮታ ጊዜ ከሚያበቃበት ቀን የሚቀጥለውን የሥራ ቀን መነሻ በማድረግ በሚከተለው የጊዜ ወሰን መሠረት ይከፈላል፡-

ሀ- ለስቱዲዮ እስከ 20 ዓመት፤

ለ- ለባለአንድ መኝታ ቤት 20 ዓመት፤

ሐ. ለባለሁለት መኝታ ወይም ለባለሶስት ወይንም ለባለ አራት መኝታ ቤት 15 ዓመት፤

4. የቤቱን ዋጋ በተከፋፈለ ተከታታይ ክፍያ በረጅም ጊዜ ለመክፈል የተዋዋለ የስቱዲዮና የባለ አንድ መኝታ ቤት ገዥ እንደየ ቤቱ ዓይነትና መጠን ቤቱን ከተረከበበት ቀን ጀምሮ የሚታሰብ ክፍያ መጀመሪያ የችሮታ ጊዜ በሚከተለው መሠረት ይሰጠዋል፡-

ሀ- ለስቱዲዮ እስከ 6 ወር፤

ለ- ለማናቸውም ባለአንድ መኝታ ቤት እስከ 3 ወር

ሐ- ለንግድ ቤቶች 2 ወር ነው።

14. <u>ስለ ክፍያ አፈፃፀም</u>

1. የቤቱን ጠቅላላ ዋጋ በአንድ ጊዜ በመክፈል ቤት ለመግዛት የተዋዋለ ገዢ ክፍያውን እንደፈፀመ እና ግንባታው እንደተጠናቀቀ በውሉ የተመለከተውን ቤት ከተዋዋለው አካል ይረከባል፤ ገዢው ማህበር በሚሆንበት ጊዜም ማህበሩ 100% ክፍያ ፈጽሞ ለአባላቱ እንዲያከፋፍል ውል የሚፈርም ሲሆን ማህበሩ ለዚህ ግልጋሎቱ በጽህፈት ቤቱ በሚቀርብ የውሳኔ ሃሳብ መሠረት በቦርድ የሚወሰን የአገልግሎት ክፍያ ቤት ከሚገዙ አባላቱ ላይ ሊያስብ ይችላል።

2. በተከፋፈለ ተከታታይ ክፍያ ቤት የገዛ ሰው፡-

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 እንደተመለከተው ጽህፈት ቤቱ ወይም በጽህፈት ቤቱ ለተወከለው አካል ቅድሚያ ክፍያ መክፈሉ ሲታወቅና ግንባታው እንዳለቀ የገዛውን ቤት እንዲረከብ ይደረጋል፤

ለ- ወርሃዊ ክፍያውን በውሉ መሠረት ለጽህፈት ቤቱ ወይም ጽህፈት ቤቱ የሚወክለው ሌላ አካል ጋር በመቅረብ ይፈፅማል፤

ሐ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ /ሀ/ የተመለከተው ቢኖርም፤ገዢ የሚገዛው ቤት ግንባታ ከመጀመሩ ወይም ግንባታው ከመጠናቀቁ በፊት ውል ተዋውሎ ጠቅላላ ዋጋ ወይም ቅድሚያ ክፍያ ሊከፍል ይችላል፤

መ. ለሚገዛው ቤት ጠቅላላ ዋጋ ወይም በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ /1/ ከተወሰነው የተሻለ ቅድሚያ ክፍያ የሚፈጽም ገዢ እንደአስፈላጊነቱ የግዢ ቅድሚያ ሊሰጠው ይችላል፤

3. ገዢው የተላለፈለት መኖሪያ ቤት ወይም ንግድ ቤት የሚገኝበት ህንፃና የጋራ መጠቀሚያ ህንፃ በቤት ባለቤቶች ማህበር በሚገዛበት ጊዜ የሁሉንም ህንፃዎች ግዢ ዋጋና የመድህን ዋስትና በቤቱ ድርሻ መጠን ይከፍላል። እንደዚሁም የጋራ መጠቀሚያ ህንፃውን የቤት ባለቤቶች ማህበር ከጽህፈት ቤቱ ከገዛ የንግድ ማህበር በሚከራይበት ጊዜ በገዛው ቤት ድርሻ መጠን ወርሃዊ የኪራይ ዋጋ ለባለ ንብረቱ ይከፍላል፤

4. ገዢው ከባንክ ብድር ወስዶ የሚከፍል ሲሆን፤ በሚገዛበት ጊዜ የቦታ ይዞታና የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ ምስክር ወረቀት በባንክ ዋስትና እንዲያዝ ፈቃደኛ እንደሆነ በማግለጽ የቤቱ ግምት ተገልፆ ለባንክ እንዲተላለፍለት በማመልከቻ ጽህፈት ቤቱን መጠየቅ ይችላል። ሆኖም ገዢው በማንኛውም መንገድ ዕዳውን መክፈል ቢያቋርጥ በባንክ በመያዣ ስለተያዘ ንብረት በወጣው አዋጅ ቁጥር 97/1990/ እንደተሻሻለ/ ባንኩ በሚያሳውቀው መሠረት ጽህፈት ቤቱ ሌላ ገዢ እንዲተካና የባንኩ መብት እንዲጠበቅ ያደርጋል።

15. <u>የወለድ መጠንና አከፋፈል</u>

1. የመኖሪያ ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት በተከፋፈለ ተከታታይ ክፍያ የገዛ ሰው በቀሪው ክፍያ ላይ የሚታሰብ በወቅቱ ባለው የገበያ ዋጋ መሰረት ወለድ ይከፍላል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም፤ በተከፋፈለ ተከታታይ ክፍያ መኖሪያ ቤት የሚገዛ ሰው የሚከፈለው የወለድ መጠን ባንኩ በገበያ ዋጋ /MARKET RATE/ በሚያወጣው የወለድ መጠን ይተካል።

www.chilot.me

16 **ውል ስለማቋረጥ**

1. ገዢው፡-

ሀ. ወርሃዊ ክፍያ ለ3 ተከታታይ ወራት ያቋረጠና በሚሰጠው የ15 ቀናት ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መሠረት ካልከፈለ፤

ለ- የገዛውን መኖሪያ ቤት5 ዓመት ሣይሞላው በሽያጭ ወይም በስጦታ ካስተላለፈ ወይም፤

ሐ. የግል መኖሪያ ቤት ወይም መኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እያለው የለኝም፤ ወይም ደግሞ ቀደም ሲል በዚህ አዋጅ መሠረት ቤት ከጽህፈት ቤቱ ወይም ከቀበሌ አስተዳደር በእራሱ ስም ሆነ በጋብቻ ውስጥ እያሉ በትዳር ጓደኛው ስም አልገዛሁም ብሎ የቤት ፈላጊዎች ማመልከቻ ቅጽ የሞላው ሐሰት ሆኖ ሲገኝ ወይም፤

መ. በከተማው ወይም በከተማው ዙሪያ አካባቢ ቢያንስ ለ2 ዓመት ኖሬአለሁ ብሎ በማመልከቻ ቅጽ የሞላው ቃል ሐሰተኛ ሆኖ ሲገኝ፤ ውሉን እንዳፈረሰ ይቆጠራል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 /ሀ/ እና /ለ/ በተመለከተው መሠረት ውል ያፈረሰ የመኖሪያ ቤት ገገር ጽህፈት ቤቱ ወይም የወከለው ሌላ አካል ቤቱን የሚለቅበትን ጊዜ በጽሁፍ በሚያስታውቀው መሠረት፡-

ሀ. የገዛውን ቤት ለጽህፈት ቤቱ ወይም ጽህፈት ቤቱ ለወከለው አካል ያስረክባል፤ ካላስረከበም በህግ ተገድዶ ቤቱን እንዲያስረክብ ይደረጋል፤

ለ. ከከፈለው ገንዘብ ላይ ለቤቱ ዕድሳት የሚያስፈልገው ወጪ ለቆየበት ጊዜ በጽህፈት ቤቱ በሚወጣ መመሪያ በሚወሰነው የኪራይ ተመን መሠረት በየወሩ የሚሰላ የኪራይ ዋጋ ተቀንሶ ቀሪው ያለወለድ ይመለስለታል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ1 /ሐ/ እና /መ/ የተመለከተውን ማናቸውንም ሁኔታ የፈፀመ ቤት ገገር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ከተመለከተው በተጨማሪ በወንጀል ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

17. **የወጪ ስሌትና አሸፋፈን**

1. ቤት የሚሸጥበት ዋጋ የሚወሰነው የጽህፈት ቤቱ የግንባታ ወጪና የቤቱና የቤቱ አካባቢ የውስጥ ለውስጥ መሠረተ ልማት ወጪዎችን፤ እንዲሁም የጋራ መገልገያዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡ ሆኖም ዋና የመሠረተ ልማት መስመሮችን ከቤቱና ከአካባቢው የውስጥ ለውስጥ መስመሮች ጋር ለማገናኘት የሚያስፈልጉት የመሠረተ ልማት ወጪዎች በክልሉ መንግስት ወይም በከተማው አስተዳደር /ማዘጋጃ ቤት/ ይሸፈናሉ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም፤ እንደአስፈላጊነቱ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ገዢዎች የተሻለ ገቢ ባላቸው ገዢዎች ለመደጎም በሚያስችል መልኩ የቤቱ አይነት የግንባታ ወጪ እየተሰላ በቦርዱ ፀድቆ ስራ ላይ ይውላል፡፡

3. ለንግድ ቤቶች ግንባታ የወጣ ወጪ የመኖሪያ ቤቶችን ለመደገም በሚያስችል መልኩ እንደየ አካባቢው የመነሻ ዋጋ ተቀምጦለት የንግድ ቤቶቹ በግልጽ ጨረታ እንዲሸጡ ወይም እንዲከራዩ በማድረግ ይሸፈናል፤

4. ልዩ የሆነ የዋጋ መዋዠቅ ሲያጋጥም ወይም አስፈላጊ መሆኑ ሲታመን የተሸጡ ቤቶችን ሣይጨምር ቦርዱ የዋጋ ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል፤

5. በአዋጁ በኮንዶሚኒየም ደንብና መመሪያ የሚደነገጉት የጋራ ወጪዎች በሙሉ በገዢዎች ይሸፈናሉ፡፡

18. **የሊዝ ክፍያ**

1. በቤት ልማት ፕሮግራም አማካኝነት የተገነቡ ወይም የሚገነቡ ቤቶች ገዢዎች በጋራ ይዞታነት የሚጠቀሙበት መሬት የክልሉ መንግስት በሚያወጣው የሊዝ ህግ መሠረት ይተዳደራሉ፤

2. ገቢዎቹ በህግ መሰረት አመታዊ የመኖሪያ ቤት የመሬት ሊዝ ክያፍ የህንፃ ታክስ ይከፍላሉ፡፡

19. **አቤቱታ የማቅረብ መብትና አወሳሰን**

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሠረት በተደረገው ማጣራት በቤት ፈላጊነት እንዳልመዘገብ ተደርጌአለሁ የሚል፤ ወይም በአንቀጽ 7 የተደረገው የቅድሚያ መብት አልተጠበቀልኝም የሚል ወይም ውል ያለአግባብ ፈረሰብኝ የሚል አቤቱታ አቅራቢ ለቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ አቤቱታ ማቅረብና የመጨረሻ ውሳኔ ማግኘት ይችላል፤
2. የቤት ፈላጊዎች ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴው በክልሉ ካቢኔ የሚሰየም ሆኖ ሦስት አባላት ይኖሩታል፤
3. ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴው አቤቱታ በቀረበለት ከ 1 ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፤
4. ኮሚቴው የቀረበለትን አቤቱታ ለማጣራት ማናቸውንም ሰነድ ወይም ምስክር በትዕዛዝ ማስቀረብና መመርመር ይችላል፤
5. ኮሚቴው ውሳኔውን ለአቤቱታ አቅራቢው በውሳኔ ማሳወቂያ ቅጽ መሠረት ያሳውቃል፤
6. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የኮሚቴው የስብሰባ ሥነ- ሥርዓትና ዝርዝር አሠራር ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ ይወሠናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

20. **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡፡

21. **ቅጣት**

ይህን አዋጅ የጣሰ ማንኛውም ሰው በሀገሪቱ የወንጀል ህግ መሠረት ይቀጣል፡፡

22. **ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ህግ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

23. **ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1. የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ይህን አዋጅና በአዋጁ መሰረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈፀም ቢሮዉ መመሪያ ልያወጣ ይችላል፡፡

24. **አዋጅ ስለሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሐረር

ህዳር 6 ቀን1999

ሙራድ አብዱልሃዲ

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HA RARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| 11ኛ ዓመት ቁጥር 13<br>11th Year No. 13 | | ሐረር መጋቢት 11/ 1999<br>Harar March 20/2007 |
| ያንዱ ዋጋ ብር 0.50<br>Unite Price Birr 0.50 | በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 952<br>P.O.Box 952 |

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 64/1999 ዓ.ም

የሐረሪ ሕ/ክልላዊ መንግሥት ለተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የገንዘብ ብድር ዉል ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ገጽ 500

## አዋጅ ቁጥር 64/1999

## በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት ለተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚዉል የክልሉ መንግሥት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር የገንዘብ ብድር ዉል ስምምነትን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የክልሉ መንግሥት የቤቶችን ግንባታ በማካሄድ ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር በርካታ ዜጎች የቤት ባለቤት እንዲሆኑ በማድረግ የቁጠባ ባህል በማዳበር በሥራ ላይ ያልዋለን ተጨማሪ ሀብት ተጨማሪ ሀብት በሥራ ላይ በማዋልና የግንባታ ኢንዱስትሪን በማሳደግ የላቀ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታዎችን ለማረጋገጥ እንደሚቻል በመታመኑ፤

እነዚህን ጠቀሜታዎች ለማረጋገጥ ክልሉ ያለው የፋይናንስ አቅም አናሳ በመሆኑ ችግሩን ለመፍታት ለኢትዮጵያ ንግድ ክ ቦንድ በመሸጥ ብድር በመውሰድ ለቤቶች ግንባታ የሚዉል የፋይናንስ ምንጭ ማግኘትና የቤቶች ተጠቃሚዎችን ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በማስተሳሰር በረጅም ጊዜ ዕዳ እንዲከፍሉ ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤ የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 51/2/ሀ/መሠረት የሚከተለዉን አውጀኂል።

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በሀረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕረግራም ማካሄጃ የክልሉ መንግሥት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር የፈጸመዉን የብድር ስምምነት ዉል ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 64/1999 " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

"የብድር ዉል" ማለት የክልሉን የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም ለማካሄድ የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር መስከረም 26/1999 የተፈረመ የብድር ዉል ፤ " Bond Agreement"፣ የፋይናንስና የቤቶች ማስተላለፍ አፈጻጸም የመግባቢያ ሰነድ እና ማሻሻያዎቻቸዉን ያጠቃልላል።

### 3. የገንዘብ ብድር መጠን

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚሆን ከ1999 ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ለአራት ተከታታይ የበጀት ዓመታት ብር 326,000,000.00 (ሦስት መቶ ሃያ ስድስት ሚሊዮን ብር) ሲሆን በየዓመቱ በሥራ ላይ በሚዉለው መጠን በበጀተ አዋጅ የሚጸድቅ ይሆናል።

### 4. የክልሉ መንግሥት መብትና ግዴታ

የክልሉ መንግሥት ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች በብድር ዉሉ ተስማምተው ያስቀመጡዋቸው እና በክልሉ የቤቶች የማስተላለፍ ሃላፊነትና አፈጻጸም አዋጅ ቁጥር 63/1999 የተደነገጉት መብቶችና ግዴታዎች ይኖሩታል።

### 5. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ዉሉ ከተፈረመበት መስከረም 26/1999 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ሐረር መጋቢት 11 ቀን1999 ዓ.ም

ሙራድ አብዱልሃዲ

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐ ረ ር ነ ጋ ሪ ጋ ዜ ጣ
# HARAR NEGARI GAZETA
OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

11ኛ ዓመት ቁጥር.14
11th year No. 14

ሐረር መጋቢት 11/99
Harar,March 20/2007

ያንድ ዋጋ ብር 1:40
Unit Price Bir. 1:40

በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት
ጠባቂነት የወጣ

ፖስታ ሣጥን ቁጥር 952
P.o .Box 952

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 65/1999 ዓ.ም
የሐረሪ ሕ/ክልላዊ መንግስት ለተለያዩ ልማት ሥራዎች ማስፈጸሚያ የ1999 ዓ.ም የተጨማሪ በጀት አዋጅ ................ .......ገጽ501

## አዋጅ ቁጥር 65/1999

## በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የ1999 የበጀት አመት ለክልሉ መንግስት ለተለያዩ የልማትና የአገልግሎት ሥራዎች ማስፋፀሚያ የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ

የሐረሪ ህዝብ ክልል ም/ቤት በተሻሻለው የሐረሪ ህዝብ ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 2(ነ) እና በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 9/1991 አንቀጽ 21 ላይ በተሠጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለውን ተጨማሪ በጀት አውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “ የ1999 የበጀት አመት ለተለያዩ የክልሉ መንግስት የልማት ሥራዎች ማስፈፀሚያ የተጨማሪ በጀት አዋጅ ቁጥር 65/1999 ዓ.ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ስለ ተጨማሪ በጀትና የገቢ ምንጭ**

ከፌደራል መንግስት ግምጃ ቤት እና ከብድር ምንጭ የተገኘ፤

ሀ. ከፌደራል መንግስት በበጀት ድጎማ ቀመር መሠረት የተገኘ የክልሉ ድርሻ ብር 6,214,500፤

ለ. ከአፍሪካ ልማት ባንክ ከውጪ አገር በብድር የተገኘ ብር 2,824,558.99፤

ሐ. ከአለም ባንክ ለውሃና ሣንቴሽን በብድር የተገኘ ብር 5,753,431.35 እና ለእንጨት አቅርቦት ብር 115,290.00፤

መ. ለተቀናጀ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ግንባታ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ1999 በጀት አመት ከቦንድ ሽያጭ በብድር የተገኘ ብር 38,500,000፡፡

**ጠቅላላ ድምር ብር 53,407,780.34** (ሃምሣ ሦስት ሚሊዮን አራት መቶ ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ሰማንያ ብር ከ34 ሣንቲም) በዚህ አዋጅ መሠረት የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የ1999 ዓ.ም ተጨማሪ በጀት ሆኖ እንዲሰራበት ጸድቋል፡፡

3. **ስለ ወጪ ምደባ**

**ለካፒታል ወጪ**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ላይ የተመለከተው ተጨማሪ በጀት በሚከተሉት ዘርፎች ተደልድሎ የወጪ

www.chilot.me

አመዳደቡ ከዚህ በታች በተለጸው አይነት ይሆናል፡፡

ሀ. ደከር÷ አቦከር ሙጢ÷ እና ሲጊቻ ድሬ ሸሪፍ አንደኛ ደ/ት/ቤቶች ኢኩፐመንት ግዢ ብር 203,000፤

ለ. ደከር÷ አቦከር ሙጢ÷ እና ሲጋቻ ድሬ ሸሪፍ አንደኛ ደ/ት/ቤቶች የትምህርት ፈርንቸር ግዢ ብር 150,000፤

ሐ. ለሶፊ አፈር ደባና ለቡርቃ 1ኛ ደ/ት/ቶች የትምህርት መሳሪያ ግዢ ብር 135,000፤

መ. አዲስ ለሚገነቡ ገልመሽራና ሲጊቻ 1ኛ ደ/ት ቤቶች የትምህርት መሳሪያ ኢኩፐመንት ግዢ ብር 70,000፤

ሠ. ሁለት አዲስ ለሚገነቡት ስጊቻና ገልመሺራ 1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ፈርንቸር ግዢ ብር 50,000፤

ረ. ደከር÷አቦከር ሙጢና ስጊቻ ድሬ ሸሪፍ አንደኛ ደ/ት/ቤቶች ደረጃ ማሳደግ እና የገልመሺራና ሲጊቻ 1ና ደረጃ ት/ቤቶች አዲስ ግንባታ ብር 2,216,558.99፤

ሰ. ለውሃ አቅርቦት ብር 5,753,431.35፤

ሸ. ለእንጨት ኃይል አቅርቦት ብር 115,290.00፤

ቀ. ለተለያዩ የልማት ስራዎች ማስፈጸሚያ ብር መጠባበቂያ በጀት 6,214,500 (ስድስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አሥራ አራት ሺህ አምስት መቶ ብር)፤

በ. በሐረር ከተማ ለሚገነቡ የኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታ አገልግሎት ብቻ የሚውል ብር 38,500,000 ሲሆን ጠቅላላ ድምር ብር 53,407,780.34 (ሃምሣ ሦስት ሚልዮን አራት መቶ ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ሰማንያ ብር ከሰላሳ አራት ሣንቲም) ወጪ ሆኖ እንዲከፈል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል፡፡

## 4. ክፍያን ስለመፈጸም

ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልሉ መንግስት አካላት (መስሪያ ቤቶች) ክፍያ ሲጠይቁ የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ ከላይ ከተጠቀሰው የገንዘብ ምንጭ እንዲከፈል ታዟል፡፡

## 5. አዋጅ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከመጋቢት 11 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ሐረር መጋቢት 11 ቀን1999
ሙራድ አብዱልሃዲ
የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት
ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| 11ኛ ዓመት ቁጥር 16<br>11th year No.16 | | ሐረር መጋቢት 19/99<br>Harar March, 2/2007 |
| ያንዱ ዋጋ ብር 5.60<br>Unite price Birr 5.60 | በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 952<br>P. O. .Box 952 |

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 66/1999 ዓ/ም
የሐረሪ ሕ/ብ/ክልላዊ መንግስት የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደርን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ———— ገጽ 503

## አዋጅ ቁጥር 66/1999
## የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ

የክልሉ ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃውን የጠበቀና በስርዓት የሚመራ እንዲሆን ለማስቻልና የሆስፒታሎችን የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በመከላከል ላይ የተመሰረቱ የጤና አገልግሎቶችና የህዝብ ጤና አጠባበቅን ተግባራዊ ለማድረግ ወጥ የሆነ የአሰራር፣ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት በማስፈለጉ፣

የሐረሪ ህዝብ ክልል ም/ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 51(2)(ሀ) በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለውን አውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ ‹‹ የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 66/1999›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፡-

1. ‹‹የጤና አገልግሎት›› ማለት የበሽታ መከላከልን፣ ቁጥጥርን፣የጤና ማጎልበት ስራን ፣የተላላፊ በሽታዎች ቅኝትን፤ የአካል፣ የላብራቶሪ ፣የራጅና ሌሎች ጤና ነክ ምርመራዎችን፤ የፈውስ ህክምናን፣ የስነ-ልቦናና የአካላዊ ተሃድሶ ጤና አጠባበቅ ትምህርቶችን ያጠቃልላል፡፡
2. ‹‹ነፃ ህክምና›› ማለት ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው መሰረት ወጪው አግባብ ባለው የመንግስት አካል ተሸፍኖ የመክፈል አቅም ለሌላቸው ዜጎች በነፃ የሚሰጥ የጤና አገልግሎት ነው፡፡
3. ‹‹ክፍያ የማይጠየቅበት የጤና አገልግሎት››ማለት የክልሉን ነዋሪ ህብረተሰብ የጤና አጠባበቅ ልምድ ከማሳደግ አንፃር በህዝብ ጤና አጠባበቅ ረገድ ጉልህ ጠቀሜታ ያላቸውን የጤና አገልግሎቶች ከመስጠት ጋር በተያያዘ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ያለ ክፍያ የሚሰጥ አገልግሎት ነው፡፡

4. **‹‹የመንግስት ጤና ተቋም››** ማለት በክልሉ መንግስት ባለቤትነት ስር የሚተዳደር ማናቸውም ሆስፒታል፣ ጤና ጣቢያ ወይም ጤና ኬላ ነው፡፡

5. **‹‹ገቢ››** ማለት የጤና ተቋማት ከሚሰጧቸው ማናቸውም የጤና አገልግሎቶችና ከሚያካሄዱት የመድሐኒትም ሆነ ሌሎች እቃዎች ሽያጭ የሚሰበሰቡ ገቢ እና በአይነትም ሆነ በጥሬ ገንዘብ የሚያገኙት እርዳታ ነው፡፡

6. **‹‹ቢሮ››** ማለት የሐረሪ ህዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የጤና ጥበቃ ቢሮ ነው፡፡

7. **‹‹ ወረርሽኝ››** ማለት በአለም አቀፍ ደረጃ ከተወሰነው መስፈርት ጣሪያ ባለፈ አኳኋን በአንድ የበሽታ አይነት የተጠቁ ሰዎች ቁጥራቸው በዝቶ የሚታይበት ክስተት ነው፡፡

8. **‹‹ተጨማሪ ክፍያ››** ማለት አንድ ሰው በመሰረታዊ ጤና አገልግሎት ተቋም ሊያገኘው የሚችለውንና የሚገባውን አገልግሎት ደረጃው ከዚህ በላይ በሆነ ተቋም ለማግኘት ሲጠየቅ እንዲከፍል የሚጠየቀው ተጨማሪ ክፍያ ነው፡፡

9. **‹‹የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት››** ማለት በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ክስተቶች ምክንያት ህዝብ ለተላላፊ በሽታዎች ሲጋለጥ የሚሰጥ የጤና አገልግሎት ነው፡፡

10. **‹‹ወጪን የሚሸፍን አካል››** ማለት የመክፈል አቅም ለሌላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የሚወጣውን የጤና አገልግሎት ወጪ በጀት በቅድሚያ ይዞ ለመሸፈን የሚስማማ ማናቸውም አካል ነው፡፡

11. **‹‹የግል የጤና ተቋም››** ማለት በጤናው ዘርፍ ከመንግስት መዋቅር ውጪ በግልና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካኝነት የጤና አገልግሎት እንዲሰጡ የሚፈቀድላቸውን ድርጅቶች የሚያጠቃልል ነው፡፡

12. **‹‹የግል ህክምና መስጫ ክፍል››** ማለት ከመደበኛው የህክምና መስጫ ክፍል ውጪ የሆስፒታሉ አንድ አካል ሆኖ የሚቋቋምና ለተመላላሽ ወይም ተኝተው ለሚታከሙ በሽተኞች የህክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ክፍል ነው፡፡

13. **‹‹የቅብብሎሽ ስርዓት››** ማለት ከጤና ኬላ እስከ ልዩ ሆስፒታል ባለው የጤና ተቋማት አደረጃጀት ውስጥ በየደረጃው ለበሽተኞች የሚሰጠው የህክምናና የጤና አጠባበቅ አገልግሎት ከአቅም በላይ ሆኖ ሲገኝ ለተሻለ አገልግሎት ከፍ ወደአሉት ተቋማት የማስተላለፍና የመቀበል አሰራር ነው፡፡

14. **‹‹ድንገተኛ››** ማለት እንደ እራስ መሳት፣ የማያቋርጥ የደም መፍሰስ፣ በእሳት መቃጠል ፣በተለያዩ አራዊት መጠቃትና በመሳሰሉት አደጋዎች ምክንያት ቅስበታዊ እርዳታ የሚያሻው ያልተጠበቀና የከፋ የጤና መታወክ ነው፡፡

15. **‹‹ቤተሰብ››** ማለት ባል ፣ ሚስት፣ እናት፣ አባት ፣ልጅ ፣ ወንድም፣ እህት ወይም በህግ የታወቀ አሳዳጊን የሚያካትት ሲሆን በዚሁ ተቋም ውስጥ የሚተዳደሩ ሌሎች አባላትን ይጨምራል፡፡

16. **‹‹ሰው››** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

17. **‹‹መሰረታዊ የጤና አገልግሎት ተቋም››** ማለት በመንግስት ስር የሚተዳደር ማንኛውም ጤና ጣቢያና ጤና ኬላዎችን የሚያጠቃልል ተቋም ማለት ነው ፡፡

### 3. ዓላማዎች

**አዋጁ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል ፡-**

1. በሽታዎችን በመከላከልና በመሰረተ ጤና አገልግሎት መስፋፋት ላይ ያተኮረውን የአገሪቱ የጤና ፖሊሲ በክልሉ ውስጥ በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ማደራጀት፤
2. የጤና አገልግሎቱን ለህብረተሰቡ በዘላቂነት መስጠት ይቻል ዘንድ የጤናው ዘርፍ በቂ ሐብት የሚያገኝበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤

3. የአገልግሎቱን ሽፋን ለማሳደግና ጥራቱን ለመጠበቅ ይቻል ዘንድ የመንግስትም ሆኑ የግሉ ሴክተር ጤና ተቋማት መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከህብረተሰቡ ጋር ተቀናጅተው የሚሰሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
4. ተጠያቂነትን ለማስፈን ገቢን ለማሳደግና የአሰራር ቅልጥፍናን ለማምጣት ሆስፒታሎች የበለጠ የስራ ነፃነት እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው፡፡

## 4. የጤና አገልግሎት አሰጣጥ መርሆች

1. የጤና ተቋማት የሚሰጡት ማናቸውም የጤና አገልግሎት ተመጣጣኝ ክፍያ የሚጠየቅበት ይሆናል፡፡ የአገልግሎቱ አይነትና የክፍያው መጠን በቢሮው ተጠንቶ በደንብ ይወሰናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም ማናቸውም ሰው የሚከፍለው በማጣቱ ምክንያት ከመንግስት ጤና ተቋማት የጤና አገልግሎት ከማግኘት አይከለከልም ፡፡
3. የጤና ተቋማት በዕቅድ ዝግጅትና በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ጉዳይ የህብረተሰቡን ተሳትፎ ማረጋገጥ አለባቸው ፡፡
4. የመንግስት የጤና ተቋማት አሰራር በሐብት አጠቃቀም ረገድ ወጪ ቆጣቢ፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን የተላበሰ እንዲሁም ውጤትን የሚያስመዘግብ መሆን አለበት ፡፡
5. ማንኛውም የጤና ተቋም ቅድመ ክፍያ ሳይጠይቅ ድንገተኛ የጤና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ሁለት

## የጤና አገልግሎት አሰጣጥ

## 5. የህዝብ ጤና አጠባበቅ

የህዝብ ጤና አጠባበቅ፣ የአካባቢ ደህንነት፣ የምግብና የመጠጥ ውሃ ንጽህና፣ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ የተላላፊ በሽታዎች ክትትልና ቁጥጥር፣ የስራ ነክ ጤና አጠባበቅ፣ በጤና ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ መሳሪያዎች አጠቃቀም እና ተያያዥነት ያላቸው ተግባራት አፈፃፀም የሚመራው ስለነዚሁ ጉዳዮች በተለይ በሚወጣው የሐይጂንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ ደንብ መሰረት ይሆናል፡፡

## 6. የአካል ክፍልን ወይም ደምን ስለ መለገስ

1. ማንኛውም ሰው በ1952 ዓ/ም በወጣው የፍታሐብሄር ህግና በዚህ አዋጅ መሰረት በህይወት ሳለም ሆነ ከሞተ በኃላ የአካሉን ክፍል ወይም ደሙን ለህክምና አገልግሎት እንዲውል በሙሉ ፍላጎት መለገስ ይችላል፡፡ አስቀድሞ ፍቃዱን ሳይሰጥ ከሞተ ከማንኛውም ሰው አስክሬን ማናቸውንም የአካል ክፍል ለህክምና አገልግሎት መውሰድ የሚቻለው የሟቹ ቤተሰቦች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በጽሁፍ ሲስማሙ ብቻ ነው ፡፡
2. ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንብ ይወሰናል ፡፡

## 7. የአስክሬን ምርመራ ስለማድረግና የሞት ማስረጃ ስለመስጠት

1. ለህክምናና ለህግ ጉዳዮች የሚችን የሞት መንስኤ ለመለየት ወይም ለማረጋገጥ ሲባል የአስክሬን ምርመራ ማድረግ ይቻላል፡፡
2. ለሞተ ሰው የሞቱን መንስኤ በሚመለከት ማንኛውም አካል ሲጠይቅ የጤና ተቋማት መርምረው ተገቢውን የጽሁፍ ማስረጃ የመስጠት ግዴታ አለባቸው ፡፡
3. የአስክሬን ምርመራ የሚካሄድበትና የሞት ማስረጃ የሚሰጥበት ዝርዝር የአሰራር ስርአት በደንብ ይወሰናል፡፡

## 8. የታካሚዎችን ፍቃድ ስለማግኘት

1. ህግ በሌላ አኳኋን እንዲፈጸም ካላስገደደ በስተቀር ማንኛውም የህክምና አገልግሎት የሚሰጠው በፍታሐብሄር ህግ ቁጥር 20 እና በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት በታካሚው ፍቃድ ይሆናል ፡፡
2. ፍቃድ መስጠት የማይችሉ ታካሚዎች እርዳታ የሚከናወነው ስለዚሁ ጉዳይ በተወሰነው ህግ ወይም በታወቀ አሰራር መሰረት ይሆናል፡፡

www.chilot.me

9. ፍቃድ ስለ ማግኘት

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ በጤና አገልግሎት ስራ ላይ ለመሰማራት በቅድሚያ የሙያ ምዝገባና የስራ ፍቃድ ሊኖረው ይገባል፡፡
2. የፌዴራሉ መንግስት ሕግጋት እንደተጠበቁ ሆነው በጤና አገልግሎት መስክ ለመሰማራት የሚፈልጉ ማናቸውም ሰው በቅድሚያ ከቢሮው ፍቃድ ማግኘት አለበት፡፡

10. የጤና ባለሙያዎች የሙያ ኃላፊነት

ማንኛውም የጤና ባለሙያ በሙያውና በደረጃው አንፃር ከዚህ በታች የተመለከቱት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1. የህብረተሰቡን ጤና የመጠበቅና የመንከባከብ ፣
2. የጤና አጠባበቅ ትምህርት መስጠት ፣
3. በሳይንሳዊ ምርምሮች የመሳተፍ፣ የበታች የጤና ባለሙያዎችን የማስተማርና እራሱንም በትምህርት የማጎልበት፡፡

11. የሙያ ስነምግባር

ማንኛውም የጤና ባለሙያ ቢሮው የሚያወጣውን የስነ-ምግባር መመሪያ የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

12. ስለ ህክምና አሰጣጥ ቅብብሎሽ ስርዓት

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ወይም ተቋም በደረጃው የሚጠበቅበትን የጤና አገልግሎት መስጠት አለበት ፡፡
2. ህሙማን ከአንድ ጤና ተቋማት ወደ ሌላ ጤና ተቋማት የሚላኩት ለዚሁ የሚሰራበትን የቅብብሎሽ ስርዓት በተከተለ መንገድ ይሆናል፡፡
3. ህሙማን የቅብብሎሽ ስርአቱን ሳይከተሉ የጤና አገልግሎት ለማግኘት ቢፈልጉ የተጨማሪ ክፍያ እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

13. ስለ ግል የህክምና መስጪያ ክፍሎች

1. የመንግስት ጤና ተቋማት እንደሁኔታው ከመደበኛ አገልግሎታቸው ጎን ለጎን ለተመሳሳሽ እና ወይም ተኝተው ለሚታከሙ ሕሙማን ተጨማሪ ክፍያ በማስከፈል የህክምና መስጫ ክፍሎች ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡
2. በመንግስት የጤና ተቋማት ውስጥ የሚደራጁት የግል የህክምና መስጫ ክፍሎች አመራር፣ አስተዳደርና አሰራር ተጠንቶ በደንብ ይወሰናል፡፡

14. አገልግሎቶችን በውል ስለመስጠት

1. የመንግስት ጤና ተቋማት ህክምና ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶችን እንደሁኔታው ብቃት ያለው አገልግሎት መስጠት ለሚችሉ አካላት በውል መስጠት ይችላሉ፡፡
2. የመንግስት ጤና ተቋማት አገልግሎቶችን በውል የሚሰጡበት ዝርዝር ሁኔታ በደንብ ይወሰናል፡፡

15. የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም

1. ቢሮው በህብረተሰቡ የጤና ሁኔታና የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያተኮረ ወቅታዊ መረጃ የሚያዝበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
2. ማንኛውም የጤና ተቋም የሚሰጠውን አገልግሎት በሚመለከት ወቅታዊ መረጃ የመያዝ፣ የማደራጀትና አስፈላጊ ሲሆን አግባብ ላላቸው አካላት የማስተላለፍ ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎትና የድንገተኛ አደጋ ህክምና

16. የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት

1. ቢሮው በወረርሽኝ መልክ የሚከሰቱ የበሽታ ዓይነቶችን ይለያል፣ ተገቢውን መረጃ ያሰባስባል፣ በወቅቱና ቀጣይነት ባለው አኳኋን ለሚመለከታቸው ሁሉ ያሰራጫል፤
2. ቢሮው የጤና አገልግሎት የአመራር አካላትና የጤና ተቋማት አደጋ ከመድረሱ በፊት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የመጠባበቂያ ግብአቶች እንዲሚሉላቸውና የመረጃም ሆነ የሎጀስቲክስ አቅም እንዲገነቡ ያደርጋል፤

3. ቢሮው የህብረተሰቡን ንቁ ተሳትፎ በማረጋገጥና ከሌሎች የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃ ከሚወስዱ አካላት ጋር በመቀናጀት የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎትን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ያስፈጽማል፣ ክትትል ያደርጋል ፤
4. ማንኛውም የጤና ተቋም በወረርሽኝ እና ሌሎች አስቸኳይ የጤና አገልግሎት ስራዎች ላይ የመሳተፍና የመተባበር ግዴታ አለበት፤
5. ማንኛውም የጤና ተቋም ቅድመ ክፍያ ሳይጠይቅ የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

17. የድንገተኛ አደጋ ህክምና አገልግሎት

1. ማንኛውም የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋም የድንገተኛ አደጋ ህክምና መስጫ ክፍል ማደራጀት አለበት፤
2. በየትኛውም የጤና ተቋም ውስጥ የሚገኝ የድንገተኛ አደጋ ህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍል አገልግሎቱን በቀንም ሆነ በማታ የመስጠት ግዴታ አለበት፤
3. ማንኛውም የጤና ተቋም በድንገተኝነት ለሚቀበላቸው ህሙማን የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና መስጠትና ታካሚው ወይም ተጎጂው ቀጣይ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይኖርበታል፤
4. የድንገተኛ አደጋ ህክምና አገልግሎት አደጋው በተከሰተበት ስፍራ ጭምር የሚሰጥባቸውንና ህብረተሰቡ ትምህርት የሚያገኝባቸውን ሁኔታዎች ቢሮው ያመቻቻል፤
5. ማንኛውም የህክምና ባለሙያ በማናቸውም ግዜና ሁኔታ የድንገተኛ አደጋ ህክምና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ ጤና አገልግሎት አደረጃጀትና አስተዳደር

18. ስለ ክልሉ ጤና አገልግሎት አደረጃጀትና አመራር

የክልሉ መንግስት ለህብረተሰቡ የሚያቀርበው የጤና አገልግሎት የሚደራጀውና የሚመራው ከዚህ በታች በተመለከቱት አካላት ይሆናል፡-

ሀ/ የክልሉ ጤና ቢሮ ፣
ለ/ የሆስፒታሎች ስራ አመራር ቦርድ፣
ሐ/ የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ፣
መ/ የቀበሌ አካባቢ መስተዳድሮች ናቸው፡፡

19. ስለ ቢሮው ልዩ ስልጣን

የብሔራዊ ክልሉ መንግስት አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.2/88 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁ.47/97 ላይ የተሰጡት ጠቅላላ ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ቢሮው ከዚህ በታች የተመለከተው ልዩ ስልጣን ይኖረዋል፡-

1. ሐገራዊ ተቀባይነት ያላቸውን መስፈርቶች ግምት ውስጥ በማስገባት የጤና ተቋማት ሊኖራቸው የሚገባውን የሰው ሐይል ብዛት፣ ብቃትና ስብጥር እንዲሁም የህንፃ፣ የህክምና መሳሪያዎችና መገልገያዎችን ደረጃ ይወስናል፤
2. የተገልጋዩን ሕብረተሰብ የመክፈል አቅምና የተቋማቱን ወጪ በማመዛዘን የጤና ተቋማቱ በሚያቀርቡት ሃሳብ መሰረት የመንግስት ጤና ተቋማት ለሚሰጡት የጤና አገልግሎት ሊፈጸም የሚገባውን ክፍያ መጠን የሚወስን መመሪያ ያወጣል፣ሲፈቀድም በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
3. የጤና ተቋማቱ የሰው ሐይል ብቃት፣ የአሰራር ስርአትና ድርጅታዊ አቅም እንዲጠናከር ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፤
4. የጤና ድርጅቶችን ደረጃ ለመለየት የሚያስችል መመዘኛ ያወጣል፣ በዚህ መሰረት ለጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ደረጃ ይሰጣል፤

5. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የግል፣ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ንብረት የሆኑ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ለህብረተሰቡ ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት ለማስፋፋትና ጥራቱን ለማሻሻል የወጡ ልዩ ልዩ ደንቦች፣ መመሪያዎችና መስፈርቶች ተከብረው በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል ፤
6. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ስልጣኑን አግባብ ላለው አካል በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤
7. ቢሮው በማናቸውም የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋም የሚሰሩ ባለሙያዎች ሙያው የሚጠይቀውን የስነ-ምግባር ደረጃ ጠብቀው ስራቸውን ማከናወናቸውንና ተቋማቱም ይህንኑ ማስከበራቸውን በየጊዜው ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

20. **የሆስፒታሎች ስራ አመራር ቦርድ**

1. ማናቸውም የክልሉ መንግስት ሆስፒታል ህጋዊ ሰውነት ያለውና እራሱን የቻለ ሆኖ ይደራጃል፣ በራሱ የስራ አመራር ቦርድና ስራ አስኪያጅ ይመራል ፣ይተዳደራል፤
2. የሆስፒቲሉ ስራ አመራር ቦርድና ስራ አስኪያጆች ዝርዝር የስራ ድርሻና ኃላፊነት በደንብ ይወሰናል ።

21. **የሆስፒታሎች ስልጣንና ተግባር**

እያንዳንዱ ሆስፒታል በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፡-

1. በሽታዎችን በመከላከልና በመቆጣጠር ላይ አተኩሮ ለህሙማን ደረጃው የጠበቀ የህክምና አገልግሎት ያቀርባል ፤
2. በውስጡ የሚገኙ ሙያተኞችና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ተገቢውን ስልጣና እንዲያገኙ ያደርጋል፤
3. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል ፣ ይከሰሳል፤
4. የባንክ ሂሳብ በስሙ ይከፍታል፣ያንቀሳቅሳል፤
5. ሐብቱን በልማት ላይ ያውላል ።

22. **የቀበሌ አካባቢ መስቱዳድር**

የቀበሌ አካባቢ መስተዳድር በተደራጀበት አካባቢ የሚገኙትን መንግስታዊ የመሰረታዊ ጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት አስመልክቶ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 ድንጋጌዎች ለቢሮው የተሰጠውን ስልጣንና ተግባራት እንደ አግባብነታቸው በስራ ላይ ያውላል።

## ክፍል አምስት

## ስለ መንግስት የጤና ተቋማት ፋይናንስ

23. **የጤና ተቋማት የፋይናንስ ምንጭ**

የክልሉ የጤና ተቋማት ፋይናንስ ከሚከተሉት የሚመነጭ ይሆናል፡-

1. በክልሉ መንግስት የሚመደብ ጥቅል በጀት፤
2. ተቋማቱ ከሚሰጡት የጤና አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢ፤
3. ከለጋሽ ድርጅቶችና ግለሰቦች የሚሰጥ የአይነትና የጥሬ ገንዘብ ስጦታ ወይም እርዳታ ፤
4. ሌሎች፡፡

24. **በገቢ ስለመጠቀም**

1. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሆስፒታሎች በመንግስት ተወስኖ ከተመደበላቸው ውጪ የሚያገኙት ማናቸውም ገቢ በጤና ተቋማቱ ስም በተከፈተ ልዩ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ይቀመጣል፤
2. ሆስፒታሎች ከክልሉ መንግስት በጥቅል ከሚመደብላቸው በጀት በተጨማሪም ከሚሰጡት አገልግሎት የሚያገኙትን ገቢ ሙሉ በሙሉ ለስራዎቻቸው ማስፈጸሚያ ያውላሉ ፤
3. የሆስፒታል ገቢ አሰባሰብ እና አጠቃቀም ስልጣን በተሰጠው የመንግስት አካል በየጊዜው ኦዲት ይደረጋል፤
4. የጤና ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ዝርዝር ቢሮው ከክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጋር በመመካከር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

www.chilot.me

25. የጤና አገልግሎት ክፍያ ማሻሻያ

በክልሉ የጤና ተቋማት ሲፈጸም የሚገባው የአገልግሎት ክፍያ መጠን ማሻሻያ ቢሮ አጥንቶ በሚያቀርበው ሃሳብ ላይ ተመስርቶ በክልሉ ካቢኔ ስፀድቅ በስራ ላይ የሚውል ይሆናል።

26. ስለ እቃና አገልግሎት ግዢ

ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች የእቃና አገልግሎት ግዢ የሚፈጽሙት አግባብ ባላቸው የክልሉ መንግስት የእቃና አገልግሎት ግዢ መመሪያዎችን በመከተል ይሆናል።

## ክፍል ስድስት

## ስለ ነፃ ህክምናና ክፍያ ስለማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች

27. የነፃ ህክምና አገልግሎት ተጠቃሚዎች

1. የመክፈል አቅም የሌላቸው ስለመሆኑ ተረጋግጦላቸው ነፃ የህክምና ማስረጃ የሚያቀርቡና በዜግነት ኢትዮጵያዊያን የሆኑ የክልሉ ነዋሪዎች ከክልሉ መንግስት የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ነፃ የህክምና አገልግሎት ያገኛሉ፤
2. የነፃ ህክምና ማስረጃ የሚሰጥ ማንኛውም አካል ለአገልግሎቱ የሚወጣውን ወጪ የመሸፈን ኃላፊነት ይኖርበታል ፤
3. ነፃ የህክምና አገልግሎት የሚሰጣቸው ተጠቃሚዎች የሚለዩበትና የወጪው አሸፋፈን አግባብ ይህንኑ አስመልክቶ በሚወጣው ደንብ ይወሰናል ።

28. ክፍያ ስለማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች

1. በክልሉ ውስጥ የሚገኙና የመንግስት የሆኑ የጤና ተቋማት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የጤና አገልግሎቶች በዚህ አዋጅ መሰረት ያለ ክፍያ ይሰጣሉ ፦

ሀ/ ከሳንባ ነቀርሳ በሽታ ጋር በተያያዘ የአክታ ምርመራ፣ ክትትልና የመድሐኒት አቅርቦት፤

ለ/ በመሰረታዊ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት አማካኝነት የሚሰጥ የቅድመ ወሊድ፣ የወሊድ የድህረ ወሊድና የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ፤

ሐ/ የክትባት አገልግሎት፤

መ/ በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ምርመራ ፤

/voluntary testing and counseling of HIV/ AIDS./

ሠ/ ኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ ከእናት ወደ ጽንስ እንዳይተላለፍ የሚሰጥ የመከላከል አገልግሎት፤

ረ/ የፀረ ኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ መድሐኒትና ተጎዳኝ ምርመራዎች ፤

ሰ/ ስጋ ደዌ፤

ሸ/ ፊስቱላ፤

ቀ/ ወረርሽኝ፤

በ/ ወጪያቸው በመንግስት የሚሸፈን ሆኖ ወደፊት ያለክፍያ እንዲሰጡ በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት የሚወሰኑ ሌሎች የጤና አገልግሎቶች።

2. ክፍያ የማይጠየቅባቸውን የጤና አገልግሎቶች የሚሰጥ ማንኛውም የጤና ተቋም የዚህ አይነቶቹን አገልግሎቶች የሚያሳይ መረጃ ለይቶ እና አደራጅቶ በመያዝ ለቢሮው የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

## ክፍል ሰባት

## የመንግስት ፣መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግሉ ዘርፍ ቅንጅት

29. የስራ አካባቢን ስለማሻሻልና ድጋፍ ስለማድረግ

1. ቢሮው የሙያ ስነ-ምግባር በማስፈን ፣ በፖሊሲ ነክ ጉዳዮች፣ በቴክኒክና በአሰራር ነክ የማሻሻያ ስራዎች ረገድ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከግሉ ዘርፍ የጤና ተቋማት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

2. በክልሉ ውስጥ የጤና ተቋማት እንዲስፋፋና የአገልግሎታቸው ጥራት እንዲሻሻል ቢሮው ለግልና ለሌሎች መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤

30. <u>መረጃን ስለማጠናቀር</u>

1. የግል ጤና ተቋማት የሚያደርጉትን ተሳትፎና የሚያጋጥማቸውን ችግር በአግባቡ መለየትና ተገቢውን እርምጃ መውሰድ እንዲቻል ቢሮው በግሉ የጤና ተቋመት ላይ ወቅታዊ የመረጃ ጥንቅር የሚኖርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ጥናቶችንም በቋሚነት ያካሄዳል፤
2. የመንግስትና የግሉ የጤና ተቋማት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ስለበሽታዎች አይነት እና ስርጭት ወቅታዊ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ አለባቸው፤
3. ማናቸውም የጤና ተቋም የሚሰጠውን አገልግሎት በሚመለከት ዕለታዊና ተዓማኒነት ያለው መረጃ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

## <u>ክፍል ስምንት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

31. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ህግ፣ ደንብ ፣መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

32. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

1. የክልሉ ካቢኔ ለዚህ አዋጅ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ቢሮው ለዚህ አዋጅና በአዋጁ መሰረት ለሚወጡ ደንቦች ተግባራዊነት የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

33. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ሐረር መጋቢት12 ቀን 1999 ዓ/ም**

**ሙራድ አብዱልሃዲ**

**የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት**

**ፕሬዝዳንት**

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA
OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| 11ኛ አመት ቁጥር 17<br>11th year No. 17 | | ሐረር መጋቢት 12/ 1999<br>March 21/2007 |
| ያንዱ ዋጋ ብር 2.80<br>Unit Price Birr 2.80 | በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 952<br>P.o .Box 952 |

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 67/1999 ዓ.ም
የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት የአካባቢ ጥበቃ ባለ ሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ——— ገጽ 511

## አዋጅ ቁጥር 67/1999

## የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ

በአንድ በኩል የአካባቢ ልማት አያያዝ የሥራ እንቅስቃሴዎችና በሌላ በኩል የአካባቢ ጥበቃ ቁጥጥርና ክትትል ተግባራትን ለተለያዩ አካላት መስጠት የሥራ ሃላፊነቶች አለመጣጣምና የሥራ ድግግሞሽን በማስወገድ የአካባቢያዊ ሀብቶች በዘላቂነት ለመጠበቅ የሚረዳ በመሆኑ ፤

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣንን አላማ ተቋማዊ አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባራት በዝርዝርና በግልጽ መደንገግ በማስፈለጉ፤

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት ክልል ም/ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 47(2)3 እና 51(2)ሀ መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል ።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ ‹‹የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 67/1999›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፤

### 2.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ዉስጥ ፣

1. ‹‹ክልል›› ማለት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግሥት አንቀጽ 47(1)(9) ላይ የተቋቋመው የሐረሪ ክልል ነው።
2. ‹‹ባለሥልጣን›› ማለት የክልሉን የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው።
3. ‹‹አካባቢ›› ማለት በመሬት በአካባቢ አየር፣በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት፣ በውሃ፣ በህያዋን፣ በድምጽ በሽታ፣ በጣዕም በማህበራዊ ጉዳዮችና በስነ ውበት ሳይወሰን በተፈጥሯዊ ሁኔታቸው ወይም በሰው አማካኝነት ተሻሽሎ ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በሙሉ ያሉበት ቦታ እንዲሁም መጠናቸውም ወይም ሁኔታቸውን ወይም ደግሞ የሰው ወይም የሌሎች ህያዋን በጎ ሁኔታ የሚነኩ ተስተጋብሮቶቻቸው ድምር ነው።

www.chilot.me

4. ‹‹አደገኛ ነገር›› ማለት በሰው ጤና ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ጠጣር ፣ ፈሳሽ ወይም የጋዝነት ባሕሪ ያለው ነገር ወይም ተክል ፣ እንሰሳ ወይም ረቂቅ ህዋስ ነው፡፡
5. ‹‹ጥበቃ›› ማለት የተፈጥሮ ባህርይ እንዳይናጋ በመጠበቅና የተፈጥሮ ሀብቶች ምንጭ አቅምን በማጎልበት ያሁኑን ትዉልድ ፍላጎት የማርካቱ ሂደት የመጪዉን ትውልድ እድል ላያሰናክል እንዲሟላ ማስቻል ነው፡፡
6. ‹‹ሰው›› ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰዉነት [illegible] የተሰጠው አካል ነው፡፡

## 3.የባለሥልጣኑ መቋቋምና ተጠሪነት

1. ባለሥልጣኑ ራሱን የቻለ እና ህጋዊ የሰዉነት መብት ያለው የክልሉ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት ተቋቁሟል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለክልሉ ፕሬዝዳንት ይሆናል፡፡

## 4. የባለሥልጣኑ ዓላማ

የባለሥልጣኑ ዓላማ በክልሉ ዉስጥ የሚከናወኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት እንቅስቃሴዎች የነዋሪዉን በጎ ሁኔታ እና የአካባቢን ደህንነት በዘላቂነት ሊያራምዱ የሚያስችሉ በፌደራሉ መንግሥት እና በክልሉ የተቀረፁ እና የወጡ የአካባቢ ፖሊሲዎችን ስልቶችን ህጎችን እና ደረጃዎችን ዉጤታማነት በክልሉ ዉስጥ በማረጋገጥ የሚከናወን ተግባር በግንባር ቀደምትነት መምራት ነው፡፡

## 5. የባለስልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. በህገ-መንግሥቱ የተደነገጉ የአካባቢ ደህንነት አላማዎችን በአካባቢ ፖሊሲው እና በክልሉ የአካባቢ እንክብካቤ ስልት የተመለከቱት መሠረታዊ መርሆዎች ከግብ መድረሳቸዉን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን በክልሉ ያስተባብራል
2. በኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲና እንክብካቤ ስልት መመስረትና በዉሳኔ ሂደት ህዝቡን በማሳተፍ የክልሉን የአካባቢ ስልት ያዘጋጃል፣ እንዲሁም የአተገባበር የግምገማና የክለሣ ሥራዎችን ያስተባብራል ፣
3. የክልሉን የአካባቢ ሁኔታ ክትትል ጥበቃና ቁጥጥር ለማከናወን የሚያስችል በፌዴራል የአካባቢ ጥበቃ ህጎችና ደንቦች ላይ በመመሥረት ክልላዊ ህጎችና ደንቦችን ያዘጋጃል ፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ መዋላቸዉን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል ፣
4. የክልሉን የአካባቢ ደረጃዎች ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም በክልሉ መተግበራቸዉን ይቆጣጠራል ፣
5. በመንግሥቱም ሆነ በግል ፕሮጀክቶች በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ስልቶች ፣ ህጎችና መርሃ ግብሮች ላይ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል ፣
6. የአካባቢ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ይገመግማል ፣ ለፍቃድ ሰጪው አካል ዉሳኔዉን ያሳውቃል፣እንደተገቢነቱ የትግበራዉ ይሁንታ ሲሰጥ በግዴታዎች መሠረት ፕሮጀክቶቹ መተግባራቸዉን ያረጋግጣል ፣ ይቆጣጠራል ፣
7. አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በመሆን በረሃማነትን ለመከላከል የሚያስችሉ ጥናቶች ያካሂዳል፣ መፍትሄዎችን ያዘጋጃል ፣ ለአተገባበራቸዉም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ፣
8. አካባቢን ለመጠበቅና የተጎዳ አካባቢን መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ ፣ አግባብብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፣
9. ከከተማ ዉስጥ የሚወጡ ዝቃጮች አካባቢዉን እንዳይበክሉ የማያቋርጥ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ አግባብ ያላቸዉን አካላት በማስተባበር አስፈላጊ የሆ የማሻሻያ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ያደርጋል ፣
10. ህብረተሰቡን በአካባቢ ጥበቃ ሥርዓት ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚረዱ መድረኮችን በማዘጋጀት የህዝብ ተሳትፎ እንዲጎለብት ማድረግ ፣የአካባቢ ክበባት እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ ያበረታታል ፣
11. አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በመመካከር የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን አደረጃጀትንና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ስርዓትን ይዘረጋል፤ ፣
12. የአካባቢ ጥበቃ ምርምሮችን ያስተባብራል፣ያበረታታል እንደአስፈላጊነቱም ራሱ ያካሂዳል ፣
13. የክልሉን የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ በየወቅቱ ያዘጋጃል ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ያደርጋል ፣
14. አግባብ ባላቸው የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የአካባቢ ጥበቃ ግዴታዎች መተግበራቸዉን ለማረጋገጥ በክልሉ ሥልጣን ሥር ወደ ሚገኝ ማንኛዉንም መሬት ፣ ቅጥር ግቢ ወይም ሌላ ቦታ ኃላፊነቱን ለመወጣት ተገቢ ሆኖ ያገኘዉን ማናቸዉንም ነገር ይፈትሻል ፣ ናሙናዎችን ይወስዳል ፣
15. የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን መሠረት በማድረግ ለማምረቻና የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ከአካባቢ ጥበቃ አንፃር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል ፣
16. በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ድንገተኛ ሁኔታዎችን ለመቋቋም ስለሚወሰዱ አስፈላጊ እርምጃዎች መንግሥትን ያማክራል ፣

www.chilot.me

17. የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ የልዩ ልዩ ተቋማትን እንቅስቃሴ ያቀናጃል፣ ያስተባብራል ፤
18. ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው አለም አቀፍ የአካባቢ ጥበቃ ስምምነቶች እንዲሁም የፌዴራል መንግሥት የሚያወጣቸዉን የአካባቢ ጥበቃ ህጎች በክልሉ እንዲተገበሩ ያደርጋል ፤
19. በክልሉ የዉሃ፣ የአፈር፣የአየር፣ የጨረርና የድምጽ ብክለቶች የሚቃለልባቸዉን ስልቶች ጥናትና ምርምር በማድረግ ህጎችንና ደንቦችን በማዘጋጀት እንዲጸድቁና ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል ፤
20. የንብረት ባለቤት ይሆናል ዉል ይዋዋላል፣ ይከሳል ፣ ይከሰሳል ፤
21. ዓላማዎቹን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ያከናዉናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ተቋማዊ ኃላፊነቶችን
## የሚመለከቱ ድንጋጌዎች

### 6.የባለስልጣኑ አቋም

ባለሥልጣኑ ፤

1. የአካባቢ ም/ቤት (ከዚህ በኋላ ‹‹ም/ቤቱ›› እየተባለ የሚጠራ ፤
2. በክልሉ ፕሬዝዳንት የሚሾም አንድ ሥራ አስኪያጅና
3. አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

### 7.የምክር ቤቱ አባላት

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የክልሉ ፕሬዝዳንት ወይም በሱ የሚሰየም ሰብሳቢ
2. የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ አባል
3. የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት አባል
4. የትምህርትና አቅም ግንባታ ቢሮ አባል
5. ጤና ቢሮ አባል
6. ማስታወቂያና ህዝብ ግንኙነት ቢሮ አባል
7. የዉሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣን አባል
8. በክልሉ ካቢኔ የሚሰየሙ ሌሎች ቢሮዎች አባላት
9. የእያንዳንዱ ወረዳ ካቢኔ አስተ/ር ሰብሳቢዎች አባል
10. የሐረር ከተማ ንግድ ም/ቤት ተወካይ ››
11. በአካባቢ አያያዝ የተሰማሩ ሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካይ ››
12. እንደ አስፈላጊነቱ ም/ቤቱ በአካባቢ ላይ ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን አካላት ልጨምር ይችላል፡፡
13. የባለ ሥልጣኑ ሥራ አስኪያጅ አባልና ፀሐፊ

### 8.የም/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

1. በክልሉ የአካባቢ ፖሊሲ ተግባራዊነትን በሚመለከት ባለሥልጣኑ በሚያቀርበው ዘገባ መሠረት ግምገማ ያካሂዳል እንደየአግባቡ አስፈላጊዉን አቅጣጫ ይሰጣል ወይም ለክልሉ ካቢኔ ሀሳብ ያቀርባል ፤
2. በባለስልጣኑ ተዘጋጅተው የሚቀርቡለትን የክልሉ የአካባቢ ፖሊሲዎች ስልቶችና ህጎች ይመረምራል የዉሳኔ ሃሳብ ለክልሉ ካቢኔ ያቀርባል ፤
3. ባለሥልጣኑ የሚያዘጋጀዉን የክልሉን የአካባቢ ደረጃዎችና መመሪያዎች ይገመግማል ፣ ያጸድቃል፣
4. ከክልሉ አጎራባች ክልል ጋር የአካባቢ እንክብካቤና ጥበቃን ብክለትና ቁጥጥርን በተመለከተ በጋራ መሥራት የሚቻልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ የትብብር መስኮችን ስልት ይቀይሳል ፤
5. በ6 ወር 1 ጊዜ ለስራው አፈጻጸም ለክልሉ ካቢኔ ሪፖርት ያቀርባል ፤
6. አካባቢን ከብክለት ለመጠበቅ ወይም ለመከላከል ወይም የአካባቢ ብክለት እንዲቀንስ ወይም እንዲወገድ ጥረት ለሚያደርግ ሰው ሊደረግ ስለሚገባው ማበረታቻ ሊጣልበት ስለሚገባው መቀጫ ከባለሥልጣኑ በሚቀርብለት ጥናት መሠረት ይመክራል፣ ለክልሉ ካቢኔ ያቀርባል ፤
7. ለክልሉ አካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ልዩ አስተዋጽኦ ላደረጉ ሰዎች ማበረታቻ ይሰጣል፡፡

### 9.የምክር ቤቱ ስብሰባ

1. ም/ቤቱ በ6 ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል
2. በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ አብላጫ ቁጥር ያላቸው አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል ፤
3. ምክር ቤቱ ዉሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፣ ሆኖም ድምጽ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል ፤
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ም/ቤቱ የራሱን የስብሰባ ስነስርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

www.chilot.me

**10.ስለባለሥልጣኑ ሥራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባር**

1. ሥራ አስኪያጁ የባለሥልጣኑ ዋና የሥራ ኃላፊ በመሆን የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል ፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራ አስኪያጁ፡-
   ሀ.በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያዉላል፡፡
   ለ. በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህግ መሠረት የባለስልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል ፣ ያስተዳድራል፣ የድስፕልን እርምጃ ይወስዳል ፤
   ሐ. የባለ ስልጣኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያዉላል
   መ. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ባለሥልጣኑን ይወክላል፣
   ሠ. የባለሥልጣኑን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ለም/ቤቱ ዘገባ ያቀርባል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**11.በጀትና የሂሣብ መዛግብት**

1. የክልሉ መንግሥት የባለሥልጣኑን በጀት ይመድባል ፤
2. ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል ፤
3. የባለሥልጣኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ሌሎች ኦዲተሮች በየአመቱ ይመረመራሉ፡፡

**12.ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1. የክልሉ ካቢኔ የዚሁን አዋጅ አላማዎች በሚገባ ለማስፈጸም ደንብ ለማውጣት ይቻላል ፤
2. ባለሥልጣኑ የዚህን አዋጅ አላማዎችና እርሱን ለማስፈጸም የሚወጡ ደንቦችን በሚገባ ለማስፈጸም አስፈላጊዉን መመሪያ ለማውጣት ይችላል ፤

**13.የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

በግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ይከናወን የነበረዉን የክልሉን የአካባቢ ጥበቃ ጅምር ሥራዎች ፤ ቁሳቁሶችና ሠነዶች ፤ እንዲሁም ተፈጥረው የነበሩ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለባለሥልጣኑ ተላልፈዋል፡፡

**14.ተፈጻሚነት የሌላቸው የህግ ድንጋጌዎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር ተቃራኒ የሆኑ ህጎች ልማዳዊ አሠራሮች በዚህ አዋጅ ዉስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸዉም፡፡

**15.አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ፡-**

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሐረር መጋቢት 12 ቀን 1999 ዓ.ም

ሙራድ አብዱልሃዲ

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA
OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

12ኛ አመት ቁጥር 1
12th year No 1

ሐረር ነሐሴ 17 ቀን 1999
Harar, Aug. 23 / 2007

ያንዱ ዋጋ ብር 2.10
Unit Price Bir. 2.10

በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር 952
P. o. Box 952

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 68/1999
የሐረሪ ህዝብ ክልል ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ እና ማሻሻያ አዋጆችን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ...........ገጽ 515

## አዋጅ ቁጥር 68/1999
## የሐረሪ ህዝብ ክልል ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ እና ማሻሻያ አዋጆችን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የሐረሪ ህዝብ ክልል ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988 በአዋጅ ቁጥር 8/1991 እና በአዋጅ ቁጥር 17/1991 የተሻሻለ መሆኑ ይታወቃል፤

ማሻሻያ አዋጆቹ በወቅቱ የነበሩትን ችግሮች በከፊል የፈቱ ቢሆንም አዋጆቹ በሥራ ላይ ከዋሉ ከ7 እስከ 10 ዓመት ያለፋቸው በመሆኑ በአፈፃፀም ላጋጠሙ ችግሮች መፍትሔ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፤

በዚሁ መሰረት በፍርድ ቤቶች ያለውን ውሱን የሰለጠነ የሰው ኃይል በአግባቡ ለመጠቀም በማሰብ፣ ዳኞች ከችሎት ስለሚነሱበት ዝርዝር ሁኔታ በአዋጅ መሸፈን አስፈላጊ መሆኑን በማመን፣ ስለሰበር አቤቱታ /ይግባኝ/ አቀራረብ ግልጽ ድንጋጌ መኖሩ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ የከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች እንዲሁም የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንቶች አሰያየምና አሿሿም የህግ መሰረት እንዲኖረው በማስፈለጉ አዋጆቹን በድጋሚ ማሻሻል ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፤

በመሆኑም በተሻሻለው የሐረሪ ህዝብ ክልል ህገ-መንግስት አንቀፅ 51(2)(ሀ) ላይ ለክልሉ ም/ቤት በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሐረሪ ህዝብ ክልል ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ እና ማሻሻያ አዋጆችን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 68/1999" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ማሻሻያ

የሐረሪ ህዝብ ክልል ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988 እና ማሻሻያ አዋጆች ቁጥር 8/1991 እና 17/1991 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

www.chilot.me

1. አዋጅ ቁጥር 3/1988 አንቀጽ 7 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 17/1991 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ተሰርዘው አዋጅ ቁ.3/1988 በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 7 ተተክቷል፡፡

## አንቀጽ 7
## የችሎት አሰራር

ሀ. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ለስራቸው አስፈላጊ የሆኑ ችሎቶች ይኖራቸዋል፤

ለ. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎት አንድ ሰብሳቢ ዳኛና ሁለት ዳኞች ሆነው ያስችላሉ፡፡ ሆኖም ግን የመያገር ትዕዛዝ፣ የብርበራ ትዕዛዝ፣ የተከሳሽ የእምነት ቃል መቀበል፣ የጊዜ ቀጠሮ ጉዳይ እና ቀጥታ የዋስትና ጉዳይ ማመልከቻን በተመለከተ የሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮች አንድ ዳኛ በተሰየመበት ችሎት ታይተው ይወሰናሉ፤

ሐ. ለክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሚቀርቡ ከአሥር ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እስራት ሊያስቀጡ የሚችሉ ቀጥታ የወንጀል ጉዳዮች እና ማናቸውም የይግባኝ ጉዳዮች ሶስት ዳኞች በሚሰየሙበት ችሎት ታይተው ይወሰናሉ፡፡ ሌሎች ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮች አንድ ዳኛ በተሰየመበት ችሎት ታይተው ይወሰናሉ፡፡

መ. በፌደራሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 80(4)(5) መሰረት ለክልሉ ጠቅላይ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡ የፌደራል ጉዳዮች የሚታዩበት የችሎት አሰያየም የሚወሰነው የፌደራል ፍርድ ቤቶች እና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ በሚደነግገው መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፤

ሠ. የጠቅላይና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶች በየፍርድ ቤቶቻቸው ሦስት ዳኞች በሚሰየሙበት ችሎት ሰብሳቢ ሆነው ሊያስችሉ ይችላሉ፤

ረ. ሦስት ዳኞች በሚሰየሙበት የጠቅላይ እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ችሎቶች በማንኛውም ምክንያት ችሎት ሲጓደል ቀጥሎ ከሚገኘው የበታች ፍርድ ቤት ዳኞች አንዱን ዳኛ ችሎት እንዲያሟላ ማድረግ ይችላል፤

ሰ. ማንኛውም የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ችሎቶች በአንድ ዳኛ ይመራሉ፤

ሸ. በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ችሎቶች በክልሉ ውስጥ ምቹ በሆነ ሥፍራዎች ያስችላሉ፡፡

2. አዋጅ ቁጥር 3/1988 አንቀጽ 10 ተሰርዞ በሚከተለው አንቀጽ 10 ተተክቷል፡፡

## አንቀጽ10

### ሀ. የዳኞች ከችሎት ስለመነሳት

አንድ የክልሉ ፍርድ ቤት ዳኛ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ምክንያቶች በአንዱ ከችሎት ይነሳል፤

I. ዳኛው ከተከራካሪዎቹ ከአንደኛው ወገን ወይም ከጠበቃው ጋር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው እንደሆነ፤

II. ዳኛው ከተከራካሪዎቹ የአንደኛው ወገን ሞግዚት፣ ነገረ ፈጅ ወይም ጠበቃ በነበረበት ወይም በሆነበት ጉዳይ ላይ የተነሳ ክርክር የሆነ እንደሆነ፤

III. ዳኛው ክርክር የተነሳበትን ጉዳይ አስቀድሞ በዳኝነት ወይም በእርቅ መንገድ ያየው ወይም፣ የሚያውቀው እንደሆነ፤

IV. ዳኛው ከተከራካሪዎች ወገኖች ከአንደኛው ወይም ከጠበቃው ጋር በፍርድ ቤት ወይም በፖሊስ ጣቢያ የተያዘ ክርክር ወይም ሙግት ያለው እንደ ሆነ፤

V. ከዚህ በላይ ከ/I/ እስከ /IV/ ከተመለከቱት ምክንያቶች ውጪ ትክክለኛ ፍትህ አይሰጥም የሚያሰኝ ሌላ በቂ ምክንያት ሲኖር ነው፡፡

### ለ. ዳኛ ከችሎት እንዲነሳ ስለማመልከት

I. ከተከራካሪዎች አንደኛው ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (ሀ) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች መሰረት አንድ ዳኛ ከችሎት መነሳት የሚገባው መስሎ የታየው እንደሆነ እንዲነሳለት ጉዳዩን ለያዘው ፍርድ ቤት ችሎት ማመልከቻ ማቅረብ ይቻላል፤

II. ማመልከቻው የሚቀርበው ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ወይም ምክንያቱ መኖሩን አመልካቹ እንዳወቀ ወዲያውኑ መሆን አለበት፤

III. አንድ ዳኛ ብቻውን የሚያስችል ከሆነ ከችሎት ስለመነሳት የሚቀርብለትን ማመልከቻ ተመልክቶ ጥያቄውን የተቀበለው እንደሆነ ከችሎት ይነሳል፡፡ ጥያቄውን ያልተቀበለ እንደሆነ ግን በዚያው ፍርድ ቤት በሚገኝ ሌላ ችሎት ከሌለም የዚህን ፍርድ ቤት ውሳኔ ይግባኝ በሚያየው ፍርድ ቤት እንዲወሰን ማስተላለፍ አለበት፤

IV. ከችሎት እንዲነሳ ማመልከቻ የቀረበበት ዳኛ ከሌሎች ዳኞች ጋር በሚያስችልበት ችሎት በሆነ ጊዜ ማመልከቻው ዳኛው በሌለበት በቀረው ዳኛ ወይም ዳኞች ውሳኔ ያገኛል፤

www.chilot.me

V. ማመልከቻው የቀረበለት ወይም የተላለፈለት ችሎት በሁለት የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡ ውሳኔውም ወዲያውኑ መፈጸም አለበት፡፡

ሐ. በቂ ምክንያት ሳይኖረው እና ከቅን ልቦና ውጪ የሚቀርብ ዳኛ ከችሎት ይነሳልኝ ማመልከቻ ፍርድ ቤቱ ማመልከቻውን ውድቅ ከማድረጉም በተጨማሪ በአመልካቹም እስከ 500 (አምስት መቶ) ብር የገንዘብ መቀጮ ሊወስንበት ይችላል፡፡ እንዲሁም ለተከራካሪ ወገን ተገቢውን ኪሳራ አመልካቹ እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ለማዘዝ ይችላል፡፡

መ. ዳኛ ከችሎት ይነሳልኝ ማመልከቻ ውድቅ በሆነ ጊዜ አመልካቹ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

3. አዋጅ ቁጥር 3/1988 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 3 ተሰርዞ በሚከተለው ንኡስ አንቀጽ 3 ተተክቷል፡፡

"3. መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ የክልሉ ፍርድ ቤት የተሰጠን የመጨረሻ ፍርድ ወይም ውሳኔ በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን ይኖረዋል፡፡ የሰበር አቤቱታ አቀራረብ በፍትሐብሔር ሥነ-ስርዓት እና በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ-ስርዓት ስለ ይግባኝ አቀራረብ በተደነገጉት መሰረት ነው፡፡"

4. በአዋጅ ቁጥር 3/1988 አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ 1(መ) ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (ሠ) ተጨምሯል፡፡

"(ሠ) ለከፍተኛ እና ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች እንደዚሁም ለጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት ፐሬዝዳንት የሚሆኑትን ከዳኞች መካከል የመምረጥና የመሾም፡፡"

## 3. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ማሻሻያ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ሐረር ነሐሴ 17 ቀን 1999 ዓ.ም

ሙራድ አብዱልሃዲ
የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት
ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA
OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

12ኛ አመት ቁጥር 2
12th year No 2

ሐረር ነሐሴ 17 ቀን 1999
Harar, Aug. 23 / 2007

ያንዱ ዋጋ ብር 11.20
Unit Price Birr 11.20

በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት
ጠባቂነት የወጣ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር 952
P. o . Box 952

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 69/1999
የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት የግዥ ሥርዓትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ........ ገጽ 518

## አዋጅ ቁጥር 69/1999
## በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት የግዥ ሥርዓትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ኃላፊነቱን በሚገባ ለመወጣት ለሚያደርገው እንቅስቃሴ ሀብትን በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ማዋል መሠረታዊ ጉዳይ በመሆኑ፤

የዕቃዎች እና የአገልግሎት ግዥ እንዲሁም የግንባታ ሥራ ከመንግስት ጠቅላላ ሀብት ከፍተኛውን የወጪ ድርሻ የሚይዝ በመሆኑ፤

የመንግሥት ግገር በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲፈጸም ከማድረግ በተጨማሪ ሂደቱ ፍትሃዊ፣ ግልጽ እና አድልዎ የሌለበት እንዲሆን ማድረግ ተገቢ ስለሆነ፤ የመንግሥት ግገር በፌደራል እና በክልሎች ለሚከናወኑ የኢኮኖሚ ልማት ተግባሮች መስፋፋት አጋዥ መሣሪያ መሆን ስላለበት፤

በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 51(2) (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት የግዥ ሥርዓትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 69/1999" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1. "ዕቃ" ማለት በጠጣር፣ በፈሣሽ ወይም በጋዝ መልክ የሚገኝ ጥሬ ዕቃ፣ ምርት፣ መሣሪያ፣ ሸቀጥ እና ኤሌክትሪክ እንዲሁም ከሚገዛው ዕቃ ጋር ግንኙነት ያለው እና ከዕቃዎቹ ዋጋ ያልበለጠ ዋጋ ያለው የተከላ ፣ የትራንስፖርት፣ የጥገናና ሌላ ተመሳሳይ አገልግሎት ነው።
2. "አገልግሎት" ማለት ከዕቃ፣ከግንባታ ዘርፍ ሥራ እና ከምክር አገልግሎት ውጪ ያለ ማንኛውም ግዥ ነው።

www.chilot.me

3. "የግንባታ ዘርፍ" ማለት ከህንፃ፣ ከመንገድ ወይም ከመሠረተ ልማት ሥራ ጋር በተያያዘ የሚከናወን አዲስ የግንባታ፣ የመልሶ ግንባታ፣ የማፍረስ፣ የጥገና፣ የማደስ ሥራ እንዲሁም ተጓዳኝ የሆነና ከዋናው ስራ ያልበለጠ ዋጋ ያለው አገልግሎት ሲሆን፣ የመገንባት፣ እንዲሁም በባለቤትነት የመያዝ፣ ሥራውን የማንቀሳቀስ፣እና የማስተላለፍ ውሎችን ይጨምራል፡፡
4. "የምክር አገልግሎት" ማለት አማካሪዎች ያላቸውን ሙያዊ ክህሎት በመጠቀም የሚሰጡት የጥናት፣ የዲዛይን፣ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን የማደራጀት፣ ለደንበኞች ምክር የመስጠት፣ ሥልጠና የመስጠት እና ዕውቀትን የማስተላለፍ የአማካሪነት ባህሪ ያለው የአዕምሮ አገልግሎት ነው፡፡
5. "የቁርጥ ዋጋ ግዥ" ማለት ከተለያዩ ግለሰቦች ወይም ግልሰብ ወይም ድርጅት ለ/ቤቱ የሚጠቅም በአይነት ተለይቶና ተወስኖ ለሚቀርብ ግዥ የሚፈጸም ነው፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡
6. "ግዥ" ማለት ዕቃዎችን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን እና አገልግሎቶችን በግዥ፣ በኪራይ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ውል ማግኘት ነው፡፡
7. "ግዥ ፈጻሚ አካል" ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት መ/ቤት፣ የትምህርት ተቋም እና ተመሳሳይ አቋም ያለው አካል ነው፡፡
8. "የመንግስት ገንዘብ" ማለት ከሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት ግምጃ ቤት ወይም የክልሉ መንግሥት ከፌደራል መንግስት ካገኘው ድጎማ ወይም የውጭ ዕርዳታ፣ ወይም የአገር ዉስጥና የዉጭ አገር ብድር ለግዥ ፈጻሚ አካላት የተመደበ ገንዘብ ወይም የግዥ ፈፃሚ አካላት የውስጥ ገቢ ነው፡፡
9. "የመንግሥት ግዥ" ማለት በግዥ ፈፃሚ አካላት በመንግስት ገንዘብ የሚከናወን ግዥ ነው፡፡
10. "አቅራቢ" ማለት ለግዥ ፈፃሚ አካላት ዕቃ ወይም አገልግሎት ለማቅረብ ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራ ወይም የምክር አገልግሎት ለማከናወን ውል የገባ ሰው ነው፡፡
11. "ዕጩ ተወዳዳሪ" ማለት በመንግሥት ግዥ እንዲሳተፍ የተጋበዘ ወይም ለመካፈል ያመለከተ ሰው ነው፡፡
12. "ተጫራች" ማለት የመጫረቻ ሀሳብ ያቀረበ ሰው ነው፡፡
13 "የጨረታ ሰነድ" ማለት ተጫራቾች የጨረታ መወዳደሪያ ለማዘጋጀት እንዲችሉ በግዥ ፈፃሚ አካላት የሚዘጋጅ ሰነድ ነው፡፡
14. " የግዥ መመሪያ " ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚወጣ መመሪያ ነው፡፡
15. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰዉነት መብት የተሰጠው ድርጅት ነው፡፡
16. "ክልል" ማለት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግሥት 47 (1) (9) ላይ የተቋቋመ የሐረሪ ሕዝብ ክልል ነው፡፡
17. "ቢሮ ወይም ቢሮ ኃላፊ" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እና የዚሁ ቢሮ ኃላፊ ነው፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በማናቸውም የክልሉ መንግስት ግዥ በሚፈፅም አካል ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. ዓለም ዐቀፍ ግዴታዎች

1. ይህ አዋጅ የፌደራል መንግስት ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ መንግሥታት ወይም ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ባደረገው ወይም በሚያደርገው ስምምነት ወይም ከስምምነቱ ከመነጨ ግዴታ ጋር የማይጣጣም ከሆነ በስምምነቱ የተመለከተው ይፀናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ስምምነት በኢትዮጵያ ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆኑ ተጫራቾች ልዩ አስተያየት የሚፈቅድ የሚሆንበት ጊዜ ግዥ ፈፃሚው አካል ተፈፃሚ የሚሆነው ልዩ አስተያየት በጨረታ ሰነድ ውስጥ በግልጽ እንዲመለከት ማድረግ አለበት፡፡

## 5. የግዥ መመሪያዎች

1. ቢሮው የዚህን አዋጅ ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ እና የአዋጁን ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ከአንድ በላይ የሆኑ ግዥ ፈጻሚ አካላት አንድ ዓይነት ዕቃ ወይም አገልግሎት ለመግዛት፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ለማሠራት የሚፈልጉ በሚሆንበት ጊዜ ቢሮው አንድ ግዥ ፈፃሚ አካል ወይም ለዚሁ ሥራ የተቋቋመ ድርጅት ግዥ በሚፈጽሙት አካላት ስም ግዥውን በቅንጅት እንዲያከናውን ወይም ግዥ ፈፃሚ አካላት የሚፈልጉትን ዕቃ፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራ እና አገልግሎት ግዥ በተጠቃለለ ሁኔታ ለመፈጸም የሚያስችል የውል ማዕቀፍ እንዲፈርም ሊያዝ ይችላል፡፡

www.chilot.me

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አፈፃፀም የውል "ማዕቀፍ" ማለት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በተፈቀደለት አካል እና በአቅራቢው መካከል የሚፈረም ግዥ ፈጻሚ አካላት አንድ ዓይነት ዕቃ፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ወይም አገልግሎት በውል ማዕቀፍ በተወሰነ ዋጋ ከአቅራቢው ጋር በሚደረግ የአፈፃጸም ውል ለመግዛት የሚያስችላቸው ስምምነት ነው፡፡

## 6. ኃላፊነትና ተጠያቂነት

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት ስለሚያከናውኑት ግዥ እና ስለውሉ አፈፃጸም ጠቅላላ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን ፣ በተለይም፡-
   - ሀ/ በተገቢው የሰው ኃይል የተደራጀ የግዥ የሥራ ክፍል የማቋቋም፣
   - ለ/ የጨረታ ኮሚቴ ማቋቋም እና አባላቱን የመሰየም፣
   - ሐ/ የጨረታ ማስታወቂያዎችን የማውጣት፣
   - መ/ የጨረታ አሸናፊዎችን የማስታወቅ፣
   - ሠ/ ውሉን ከመፈረሙ በፊት ግዥ ለመፈፀም የሚያስችል በቂ በጀት መኖሩን የማረጋገጥ፣
   - ረ/ የግዥ ውሎችን የመፈረም፣
   - ሰ/ በተጫራቾች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ውሣኔ የመስጠት፣
   - ሸ/ የአቤቱታዎችን ቅጂ እና የምርመራ ግኝቶችንና በግኝቶቹ መሠረት የተሰጠውን ውሳኔ የያዘ ሪፖርት ለቢሮው የማቅረብ፣
   - ቀ/ ከአሸናፊው ጋር የተደረገው ውል፣ አሸናፊ በሆነባቸው ቃሎችና ሁኔታዎች መሠረት መፈፀሙን የማረጋገጥ፣
   - በ/ እንደ አስፈላጊነቱ የግዥ ሥርዓትን የሚያስፈጽሙ ሦስተኛ ወገኖችን የመቅጠር፣ ግዴታ አለባቸው፡፡
2. ግዥ ፈፃሚ አካላት እና ለግዥ ሥራ የተመደቡ ሠራተኞች ወይም የመንግስት ግዥን ለማስተዳደር ኃላፊነትን የተሰጣቸው ይህን አዋጅ እና ቢሮው የሚያወጣቸውን መመሪያዎች በመተላለፍ ስለሚወስዷቸው እርምጃዎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## የመንግሥት ግዥ ስርዓትን የማስፈፀም ኃላፊነት

## 7. የመንግሥት ግዥን የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት

1. ቢሮው በሌሎች አዋጆች የተሰጡት ስልጣን እና ተግባራት እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት ግዥ በዚህ አዋጅ እና እንደ አግባብነቱ በሚወጡት ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት መፈፀሙን የመከታተልና የመቆጣጠር ስልጣን ለገ/ኢ/ል/ቢሮ ተሰጥቷል፡፡
2. ቢሮው አዋጁን በአግባቡ ለመወጣትና ለማስፈጸም የሚያስችለውን ክፍል ያደራጃል፡፡

## 8. ዓላማዎች

የቢሮው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ፍትሀዊ፣ በውድድር ላይ የተመሠረተ፣ ግልጽ፣ አድልዎ የሌለበት፣ ለመንግስት ገንዘብ ተመጣጣኙን ዋጋ ማስገኘት የሚያስችል የግዥ አፈፃፀም መኖሩን ማረጋገጥ፤
2. የክልሉ መንግስት የግዥ አፈፃጸም የሚመራበት ደረጃ ማውጣት፤
3. የግዥ ፈፃሚ አካላት ይህንን አዋጅ ጠብቀው መሥራታቸውን መከታተል፤
4. በክልሉ መንግስት ውስጥ ያለውን የግዥ አፈፃጸም አቅም ማሳደግ፡፡

## 9. የቢሮው ተግባሮች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባሮች ያከናውናል፡-

1. የመንግሥት ግዥ ፖሊሲዎች፣ መርሆዎችና አፈፃፀሞች ላይ የክልሉን መንግስት ማማከር፤
2. በክልሉ መንግሥት ውስጥ ያለውን የመንግስት ግዥ አፈፃፀም ሥርዓት ተግባራዊነት መከታተል፣ በህግና በአፈፃጸም ሥርዓቱ ላይ ማሻሻያ ሀሣቦች ማቅረብ፤
3. አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የግዥ ሥልጠና፣ የግዥ አፈፃፀምን ለመምራት የሚያስፈልገው ችሎታ ሊኖረው የሚገባ ደረጃ፣ ተፈላጊ የሆነ የማስረጃ ዓይነት እና የሙያው ዕድገት የሚከተለው ሂደት እንዲወሰን ማድረግ፤
4. በሥራ ላይ እንዲውሉ የተፈቀዱ መደበኛ የግዥ ሰነዶች፣አሠራሩን የሚመሩ ቅፆች እና ሌሎች ለግዥ አፈፃጸም አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ማዘጋጀት፣ ወቅታዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣
5. ከተፈቀዱ መደበኛ የግዥ ሰነዶች፣ አሠራሩን ከሚመሩ ቅፆች እና ሌሎች ለግዥ አፈፃፀም አግባብነት ካላቸው ሰነዶች ዉጪ ግዥ የሚፈፀመዉ ቢሮው በፅሑፍ ስምምነቱን ሲሰጥ ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ፤
6. በአንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ለመመዝገብ የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን መቀበል፣ መመርመር እና መመዝገብ፣ ለተመዘገቡ አቅራቢዎች የምስክር ወረቀት መስጠት፤

www.chilot.me

7. በመንግስት ግዥ ውል ውስጥ በተመለከቱ ግዴታዎች ላይ ከፍተኛ ቸልተኛነት በማሳየታቸው፣ ስለብቃታቸው የተሳሳተ መረጃ በመስጠታቸው ወይም በአንቀጽ 18 የተመለከተውን ዓይነት መማለጃ በመስጠታቸው ምክንያት በመንግስት ግዥ እንዳይሳተፉ በቢሮው ዕገዳ የተደረገባቸውን አቅራቢዎች ዝርዝር መያዝ፣

8. ይህ አዋጅ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት ግዥ ፈፃሚ አካላት ሰነዶች እና ግዢውን በማስፈፀም ሂደት የተከተሉትን አካሄድ መመርመር፣

9. በቢሮው በሚወሰነው መሠረት በመንግስት ሊፈጸሙ የታቀዱ ግዥዎችን በጨረታ አሸናፊ የሆኑ አቅራቢዎችን ፣ እና ሌሎችንም ህዝብ ሊያውቃቸው የሚገባ መረጃዎችን መያዝ የሚያስችል ሥርዓት ማደራጀት እና መጠበቅ፣

10. የግዥ አፈፃፀም ይህንን አዋጅ ጠብቆ የተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ፡-
   ሀ/ በጨረታ ዝግጅት ሂደት የግዥ ምርመራ፣
   ለ/ በጨረታ አሸናፊ የሆነው ተጫራች በውሉ መሠረት ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የውል ምርመራ፣
   ሐ/ በውሉ መሠረት ሥራው ከተጠናቀቀ የክዋኔ ምርመራ ማካሄድ፣

11. ግዥ ፈፃሚ አካላት በጋራ የሚጠቀሙበት አስገዳጅነት ያለው የዕቃና አገልግሎት ዝርዝር በሥራ ላይ ማዋል፣ ይኸው ዝርዝር ከአሠራር ጋር የተጣጣመ እና ወቅታዊ እንዲሆን ማድረግ፣

12. ለግዥ አሠራር ሥረዓቶች በሙሉ የሚያገለግል የመረጃ ክምችት ማቋቋም፣ ማንቀሳቀስ፣ መጠበቅ እና ወቅታዊነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፣

13. የተቋም እና የሰው ኃይል አቅም፣ለማጎልበት የሚያስችል የአቅም ግንባታ ፖሊሲ እንዲኖር ማድረግ፣

14. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5(2) በተደነገገው መሠረት ከሚመለከታቸው ግዥ ፈፃሚ አካላት ጋር በመስማማት በየዓመቱ እንደገና እየታየ በሚሻሻል ሥርዓት ግዢያቸው በጋራ ሊፈጸም የሚገባ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች፣ ዕቃዎችና አገልግሎቶችን ዝርዝር ማዘጋጀት፣

15. የሙያና ከሙያ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች አግባብነት ካላቸው በመንግሥት ግዥ ለመሳተፍ ፍላጎት ካላቸው አካላት ጋር ተቋማዊ ግንኙነት መፍጠር እና ማዳበር፣

16. ስለመንግሥት ግዥ አፈፃጸም ጥናት ማካሄድ፤

17. የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባሮችን የማከናወን፣

18. ይህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ ናቸው፡፡

## 10. የግዥ ፈፃሚዎችን የመቆጣጠር ስልጣንና ኃላፊነት

ቢሮው ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የሚከተለው ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

1. ማናቸውም ግዥ ፈፃሚ አካላ ወይም አቅራቢ ህግ ከሚያዘው ውጪ ስለመፈፀሙ፣ ግዥ በትክክል ስላለማከናወኑ፣ የግዥውን አመራር በትክክል ስላለመፈፀሙ ወይም ስለመመሳጠሩ ሪፖርት የቀረበ ወይም የተረጋገጠ እንደሆነ ከግዥው አፈፃጸም ጋር የተያዩዙ መረጃዎች፣ ሰነዶች መዝገቦች እና ሪፖርቶች እንዲቀርቡለት የማዘዝ፣

2. ምስክሮችን የመጥረት፣ ምስክሮችና ግዢው የሚመለከታቸው ወገኖች ቃላቸውን በመ[illegible] እንዲሰጡ ማድረግ፣ የሂሳብ መዝገብ፣ ፕላን ፣ ሰነድ እንዲቀርብለት ማድረግ፣

3. በመንግሥት ግዥ አፈፃጸም ላይ ምርመራ እንዲካሄድ ማድረግ ወይም ምርመራውን ማከናወን፣ የመንግሥት ግዥ ውል እና የክንዋኔ ኦዲት ማካሄድ፣

4. ግዥ ፈፃሚ አካላት የጨረታው አሸናፊ የመሆን ውሳኔ በተሰጠበት አኳኋን ግዢውን የፈፀሙ መሆኑን ለማረጋገጥ በግዥው ሂደት ላይ ምርመራ ማካሄድ፣

5. በዚህ አዋጅ ምዕራፍ 8 ውስጥ የተዘረጋውን ሥርዓት በመከተል ግዥ ፈፃሚ አካላት፣ አቅራቢዎች እና ማናቸውም ሌላ ሰው ወይም ድርጅት በግዥው እንቅስቃሴ ተሳትፎ በነበረው ማናቸውም ሰው ላይ የሚያቀርቡትን አቤቱ[illegible] የመመርመር፡፡

## ምዕራፍ ሶስት
## መሠረታዊ የግዥ ድንጋጌዎች

## 11. የግዥ ሰነዶች

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት ከመንግስት ግዥ ጋር የተያየዙ መዝገቦችን እና ሰነዶችን ግዢው ከተፈፀመበት ቀን አንስቶ ለ10 ዓመት ያህል ማቆየት አለባቸው፡፡ በዚህ ዓይነት የሚያዙት መረጃዎች የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡
   ሀ/ የሚገዙት ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች አጭር መግለጫ፣

ለ/ የጨረታ ማስታወቂያ፣

ሐ/ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ወይም የዋጋ ማቅረቢያ ያቀረቡ አቅራቢዎች ስምና አድራሻ እንዲሁም በጨረታው አሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች ስመና አድራሻ፣

መ/ ለጨረታ ግምገማ የተዘጋጀውን መስፈርት እና ተፈፃሚ የተደረገበትን ሁኔታ ፣ የጨረታ ግምገማና የወሰደውን አፈፃፀም እና ከተወዳዳሪዎች የቀረበውን መወዳደሪያ ሀሳብ እና የዋጋ ማቅረቢያ የሚያሳይ አጭር መግለጫ፣

ሠ/ በቀረበው አቤቱታ መሠረት ጨረታውን ለማገድ ወይም ለመሠረዝ ውሳኔ የተሰጠበትን አካሄድ የሚያሳይ መረጃ ፣

ረ/ ከግልፅ ጨረታ ውጪ ሌሎች የግዥ ሥርዓቶችን መከተል የተመረጠበትን ምክንያት፣

2. የግዥው ሂደት ተጠናቆ ከአሸናፊው ጋር ውል ከተፈረመ ወይም በማናቸውም ምክንያት ውሉ ከተቋረጠ በኋላ የግዥውን ዝርዝር አፈፃፀም የሚያሳየው መረጃ በጨረታው ዕጩ ተሳታፊ የሆኑ ተወዳዳሪዎች ሲጠይቁ እንዲያዩት መደረግ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ካልታዘዘ እና በፍ/ቤቱ በተሰጠው ትዕዛዝ በተመለከተው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ግዥ ፈፃሚው አካል የሚከተሉትን መረጃዎች መስጠት የለበትም፡፡

ሀ/ የመረጃው ይፋ መሆን በህግ የማይፈቀድ፣ የህግ አፈፃፀምን የሚያሰናክል፣ የህዝብን ጥቅም የሚቃረን፣ የተዋዋዮችን ህጋዊ የንግድ ጥቅም እንዲሁም ቀና ውድድርን የሚጎዳ ከሆነ፣

ለ/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) (መ) በተመለከተው መሠረት በማሳጠር የተዘጋጀውን ሰነድ ካለሆነ በስተቀር ከተጫራቾች የቀረበውን የመወዳደሪያ ሃሳብ ከመመርመር እና ከመገምገም ተግባር ጋር የተያያዙ መረጃዎችን፣ እና ተጫራቾች ያቀረቡዋቸውን የመወዳደሪያ ሀሳቦች እና የጨረታ ሰነዶች ይዘት የሚገልፁ መረጃዎች፡፡

## 12. አድልዎ ያለማድረግ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ በዜግነት፣ በዘር ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች በመንግስት ግዥ ተሳታፊ እንዳይሆን ሊደረግ አይችልም፡፡

## 13. ልዩ አስተያየት

1. በጨረታ ግምገማ ወቅት፡-

ሀ/ በኢትዮጵያ የተመረቱ ዕቃዎች እስከ 15/%፣

ለ/ በኢትዮጵያ ኩባንያዎች የሚከናወኑ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች እስከ 7.5% ልዩ አስተያየት ይደረግላቸው፡፡

2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈፃጸም ማናቸውም ዕቃ ከዋጋው ከ20% በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የታከለ ከሆነ በኢትዮጵያ ዉስጥ እንደተመረተ ይቆጠራል፡፡

## 14. የግንኙነት ስልት

1. በግዥ ፈፃሚ አካላትና በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች በጽሁፍ መደረግ አለባቸው፡፡ በፅሁፍ ያልተደረጉ ማናቸውም ግንኙነቶች በማከታተል በፅሁፍ መረጋገጥ አለባቸው፡፡

2. ቢሮ የመረጃ ልውውጡን ትክክለኛነት እና በምስጢር መጠበቁን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥርዓቶች መዘረጋታቸውን እና በቴክኒክ ረገድ ተፈላጊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ከፅሁፍ በተጨማሪ ወይም በፅሑፍ ምትክ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ግንኙነት እንዲደረግ ሊፈቀድ ይችላል፡፡

## 15. የዕጩ ተወዳዳሪዎች ብቃት

1. በማንኛውም የመንግስት ግዥ ለመሳተፍ እጩ ተወዳዳሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እና ግዥ ፈፃሚ አካላት በግዥው ልዩ ባህሪይ በመነሳት የሚያወጧቸው ሌሎች መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡፡

ሀ/ በሚገቡት ውል መሠረት ለመፈፀም የሚያስችል የሙያና የቴክኒክ ብቃት፣ የፋይናንስ አቅም፣ መሣሪያ እና ሌሎች መገልገያ ሥፍራዎች፣ ግዥው በሚፈፀምበት ተግባር የሥራ አመራር ችሎታ፣ መልካም ዝና እና የሰው ኃይል ያላቸው፣

ለ/ ውል ለመፈፀም የሚያስችል የህግ ችሎታ ያለው፣

ሐ/ በዕዳ ያልተያዘ፣ ያልከሠረ ወይም የሥራ እንቅስቃሴውን ያላቋረጠ፣ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው ያልታገደ፣ ወይም በእነዚህ ምክንያቶች ተከሶ በክርክር ላይ ያልሆነ፣

መ/ በኢትዮጵያ የግብር ህጎች በተደነገገው መሠረት የግብርና የታክስ ግዴታውን የተወጣ፣

ሰ/ የጨረታ ማስታወቂያ፣

ሐ/ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ወይም የዋጋ ማቅረቢያ ያቀረቡ አቅራቢዎች ስምና አድራሻ እንዲሁም በጨረታው አሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች ስመና አድራሻ፣

መ/ ለጨረታ ግምገማ የተዘጋጀውን መስፈርት እና ተፈፃሚ የተደረገበትን ሁኔታ ፣ የጨረታ ግምገማና የወሰደውን አፈፃፀም እና ከተወዳዳሪዎች የቀረበውን መወዳደሪያ ሀሳብ እና የዋጋ ማቅረቢያ የሚያሳይ አጭር መግለጫ፣

ሠ/ በቀረበው አቤቱታ መሠረት ጨረታውን ለማገድ ወይም ለመሠረዝ ውሳኔ የተሰጠበትን አካሄድ የሚያሳይ መረጃ ፣

ረ/ ከግልፅ ጨረታ ውጪ ሌሎች የግዥ ሥርዓቶችን መከተል የተመረጠበትን ምክንያት፣

2. የግዥው ሂደት ተጠናቆ ከአሸናፊው ጋር ውል ከተፈረመ ወይም በማናቸውም ምክንያት ውሉ ከተቋረጠ በኋላ የግዥውን ዝርዝር አፈፃፀም የሚያሳየው መረጃ በጨረታው ዕጩ ተሳታፊ የሆኑ ተወዳዳሪዎች ሲጠይቁ እንዲያዩት መደረግ አለበት። ይሁን እንጂ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ካልታዘዘ እና በፍ/ቤቱ በተሰጠው ትዕዛዝ በተመለከተው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ግዥ ፈፃሚው አካል የሚከተሉትን መረጃዎች መስጠት የለበትም።

ሀ/ የመረጃው ይፋ መሆን በህግ የማይፈቀድ፣ የህግ አፈፃፀምን የሚያሰናክል፣ የህዝብን ጥቅም የሚቃረን፣ የተዋዋዮችን ህጋዊ የንግድ ጥቅም እንዲሁም ቀና ውድድርን የሚጎዳ ከሆነ፣

ለ/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) (መ) በተመለከተው መሠረት በማሳጠር የተዘጋጀውን ሰነድ ካለሆነ በስተቀር ከተጫራቾች የቀረበውን የመወዳደሪያ ሃሳብ ከመመርመር እና ከመገምገም ተግባር ጋር የተያያዙ መረጃዎችን፣ እና ተጫራቾች ያቀረቡዋቸውን የመወዳደሪያ ሀሳቦች እና የጨረታ ሰነዶች ይዘት የሚገልፁ መረጃዎች።

## 12. አድልዎ ያለማድረግ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ በዜግነት፣ በዘር ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች በመንግስት ግዥ ተሳታፊ እንዳይሆን ሊደረግ አይችልም።

## 13. ልዩ አስተያየት

1. በጨረታ ግምገማ ወቅት:-

ሀ/ በኢትዮጵያ የተመረቱ ዕቃዎች እስከ 15/%፣

ለ/ በኢትዮጵያ ኩባንያዎች የሚከናወኑ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች እስከ 7.5% ልዩ አስተያየት ይደረግላቸው።

2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈፃጸም ማናቸውም ዕቃ ከዋጋው ከ20% በላይ በኢትዩጵያ ውስጥ የታከለ ከሆነ በኢትዮጵያ ዉስጥ እንደተመረተ ይቆጠራል።

## 14. የግንኙነት ስልት

1. በግዥ ፈፃሚ አካላትና በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች በጽሁፍ መደረግ አለባቸው። በፅሁፍ ያልተደረጉ ማናቸውም ግንኙነቶች በማከታተል በፅሁፍ መረጋገጥ አለባቸው።

2. ቢሮ የመረጃ ልውውጡን ትክክለኛነት እና በምስጢር መጠበቁን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥረዓቶች መዘረጋታቸውን እና በቴክኒክ ረገድ ተፈላጊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ከፅሁፍ በተጨማሪ ወይም በፅሑፍ ምትክ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ግንኙነት እንዲደረግ ሊፈቀድ ይችላል።

## 15. የዕጩ ተወዳዳሪዎች ብቃት

1. በማንኛውም የመንግስት ግዥ ለመሳተፍ እጩ ተወዳዳሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እና ግዥ ፈፃሚ አካላት በግዥው ልዩ ባህሪይ በመነሳት የሚያወጧቸው ሌሎች መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።

ሀ/ በሚገቡት ውል መሠረት ለመፈፀም የሚያስችል የሙያና የቴክኒክ ብቃት፣ የፋይናንስ አቅም፣ መሣሪያ እና ሌሎች መገልገያ ሥፍራዎች፣ ግዥው በሚፈፀምበት ተግባር የሥራ አመራር ችሎታ፣ መልካም ዝና እና የሰው ኃይል ያላቸው፣

ለ/ ውል ለመፈፀም የሚያስችል የህግ ችሎታ ያለው፣

ሐ/ በዕዳ ያልተያዘ፣ ያልከሠረ ወይም የሥራ እንቅስቃሴውን ያላቋረጠ፣ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው ያልታገደ፣ ወይም በእነዚህ ምክንያቶች ተከሶ በክርክር ላይ ያልሆነ፣

መ/ በኢትዮጵያ የግብር ህጎች በተደነገገው መሠረት የግብርና የታክስ ግዴታውን የተወጣ፣

www.chilot.me

2. ግዥ ፈፃሚው አካል ዕጩ ተወዳዳሪዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩት መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ የሰነድ መረጃዎችን ወይም ሌሎች መረጃዎችን እንዲያቀርቡ መጠየቅ ይችላል ::
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት ዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲያሟሉ የሚጠበቁት መስፈርቶች በጨረታ ሰነድ ወይም የተጫራቾችን የመወዳደሪያ ሃሳብ ለመጠየቅ በሚዘጋጁ ሰነዶች ውስጥ መመልከት ያለባቸው ሲሆን፣ በሁሉም ተጫራቾች ላይ በእኩልነት ተፈፃሚ መሆን አለባቸው።
4. ግዥ ፈፃሚው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የሚቀርቡትን ሰነዶች እና የመመዘኛ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ የዕጩ ተወዳዳሪዎች ብቃት መገምገም አለበት።
5. ግዥ ፈፃሚ አካል ብቃት ያላቸው መሆኑን ለማስረዳት ሀሰተኛ መረጃ የያዙ ሰነዶችን ያቀረቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ብቃታቸውን ለማረጋገጥ ያቀረቡት መረጃ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ወይም ያልተሟላ መሆኑ በማናቸውም ጊዜ የተረጋገጠ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከጨረታ ውጪ እንዲሆኑ ለመወሰን ይችላል።
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከ(1) እስከ (4) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚያሟሉ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚከናወነውን ተግባር ቀላል ለማድረግ ቢሮው ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚቀርቡ መረጃዎችን በተቀላጠፈ አሠራር በመመርመር የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል። ይህ መረጃ በየጊዜው ወቅታዊ መደረግ አለበት። የአቅራቢዎችን ዝርዝር የሚይዝ አጭር መግለጫ ተዘጋጅቶ አቅራቢዎች ወይም ግዥ ፈፃሚ አካላት በሚጠይቁበት ጊዜ መስጠት አለበት። ቢሮው የአቅራቢዎችን አመዘጋገብ ሥርዓት የሚወስን ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

## 16. የዕቃና አገልግሎት ዝርዝር

1. ስለግዢው ምንነት ትክክለኛና የተሟላ መግለጫ እንዲኖር እንዲሁም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ፍትሀዊና ግልጽ በሆነ ሁኔታ መወዳደር የሚችሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ግዥ ፈፃሚ አካላት የሚገዙዋቸውን ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች ባህርይ የሚያሳይ የቴክኒክ ዝርዝር ወይም መግለጫ ማዘጋጀት አለባቸው።
2. የቴክኒክ መግለጫው ግዥ ፈፃሚው አካል ሊገዛ የሚፈልገውን ዕቃ ጥራት ጠቀሜታ፣ ጉዳት የማያደርስ መሆኑን፣ መለኪያውን፣ መለያውን፣ መጠሪያውን፣ አስተሻሸጉን፣ ምልክቱን፣ ወይም የአመራረቱን ሂደትና ዘዴ እና ተፈላጊውን የሚያሟላ መሆኑ የሚረጋገጥበትን ሥርዓት የሚገልጽ መሆን አለበት።
3. በግዥ ፈፃሚ አካላት የሚዘጋጀው የቴክኒክ ዝርዝር አግባብነት እስካለው ድረስ፣
   ሀ/ በዲዛይን ወይም ባህሪያትን በመዘርዘር ላይ ሳይሆን በጠቀሜታ ላይ፣
   ለ/ አገራዊ ደረጃ የወጣለት ሲሆን ደረጃውን ወይም ዓለም ዐቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን ደረጃዎች ወይም የግንባታ ኮዶች፣ መሠረት ያደረገ መሆን አለበት።
4. የግዥ ፈፃሚውን አካል ፍላጎት በትክክል ለመግለጽ አስቸጋሪ ካልሆነ ወይም ሌላ ዘዴ ካልታጣ በስተቀር የቴክኒክ መግለጫ የተለየ የንግድ ምልክት ወይም ስም ፓተንት፣ ዲዛይን ወይም የተወሰነን አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ የሚጠቅስ መሆን የለበትም። አስገዳጅ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ <<ወይም ተመሳሳዩን>> የሚል ሐረግ በዕቃና አገልግሎት ዝርዝሩ ውስጥ መታከል ይኖርበታል።

## 17. ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሀሳብ እና ዋጋ ማቀረቢያን ውድቅ ስለማድረግ

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት ጨረታን፣ የዕቃና አገልግሎት አቅርቦት መወዳደሪያ ሀሳብን እና የዋጋ ማቀረቢያን የግገር ፈፃሚ መ/ቤት ጥቅምና ፍላጎትን የሚጎዳ ሆኖ ሲገኝ የግዥ ስምምነት ከመደረጉ በፊት በማናቸውም ጊዜ ውድቅ ማድረግ ይችላሉ። ግዥ ፈፃሚ አካላት ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሀሳብን ፣ የዋጋ ማቀረቢያን ሙሉ በሙሉ ውድቅ ያደረጉበትን ተወዳዳሪዎች መግለጽ አለባቸው። ይሁን እንጂ የምክንያቶቹን አግባብነት እንዲያስረዱ አይገደዱም።
2. ግዥ ፈፃሚ አካላት ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሠረት ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሀሳብን፣ የዋጋ ማቀረቢያን ውድቅ በማድረጋቸው ምክንያት ምንም ዓይነት ተጠያቂነት አይኖርባቸውም።
3. ጨረታ፣ የመወዳደሪያ ሀሳብን የዋጋ ማቀረቢያ ውድቅ መደረጉን የሚገልጽ ማስታወቂያ ወዲያውኑ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲደርስ መደረግ አለበት።
4. ጨረታውን ውድቅ የማድረጉ ውሳኔ የተሰጠው ከጨረታው መዝጊያ ቀን በፊት ከሆነ የጨረታው ሰነዶች ሳይከፈቱ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች መመለስ አለባቸው።

www.chilot.me

18. **በዕጩ ተወዳዳሪዎች ስለሚሰጥ መደለያ**

ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ የግዥ ፈፃሚ አካልን ወይም የሌላ የመንግስት መ/ቤት ኃላፊን ወይም ሠራተኛ ተግባር ወይም ውሳኔ ለማዛባት ወይም ከግዥው አፈፃፀም ጋር በተያያዘ መ/ቤቱ ሊከተለው የሚገባውን አሠራር ለማስለወጥ በመደለያ መልክ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ማናቸውንም ዓይነት ስጦታ የሠጠ ወይም ስጦታ ለመስጠት ቃል የገባ ወይም የሥራ ዕድል ወይም ሌላ ማናቸውንም የገንዘብ ዋጋ ያለውን ነገር ወይም አገልግሎት መስጠቱ የተደረሰበት እንደሆነ ግዥውን የሚፈፅመውን አካል የዕጩ ተወዳዳሪውን ጨረታ፣ የመወዳደሪያ ሀሳብ ወይም የዋጋ ማቀረቢያ ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡ በዚህ ዓይነት የአቅራቢው መወዳደሪያ ውድቅ የተደረገ እንደሆነ ለውሳኔው መሠረት የሆነው ምክንያት በግዥው አፈፃፀም ሰነዶች ላይ መመዝገብ ያለበት ሲሆን፣ መወዳደሪያው ውድቅ የተደረበትን ምክንያት ዕጩ ተወዳዳሪው ወዲያውኑ እንዲያውቀው መደረግ አለበት፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የግዥ ዘዴዎችን ስለመምረጥ

19. **የግዥ ዘዴዎች**

1. በዚህ አዋጅ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ግዥ ፈፃሚ አካላት ማናቸውም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈፀም አለባቸው፡፡
2. ግዥ ፈፃሚ አካላት ከግልፅ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈፀም የሚችሉት ከዚህ በታች ከአንቀጽ 20-25 በተመለከቱት ሁኔታዎች ብቻ ይሆናል፡፡
3. በቂ የኢኮኖሚ ምክንያት ያለ መሆኑን ሲረዳ ቢሮው ከአንቀጽ 20-25 ባልተጠቀሱ ሌሎች ምንክንያቶች ግዥ ከግልፅ ጨረታ ውጪ በሌሎች ዘዴዎች እንዲፈፀም በልዩ ሁኔታ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
4. ግዥ ፈፃሚ አካላት በምክንያት የተደገፈ የገዥ ዕቅድ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ በዚህ አዋጅ ወይም በግዥ መመሪያው የተዘረጉ የግዥ ሥርዓቶችን ለመሸሽ ግዥ ፈፃሚ አካላት በአንድነት ሊፈፀም የሚገባቸውን የዕቃ፣ የግንባታ ወይም የአገልግሎት ግዥዎች መከፋፈል የለባቸውም፡፡

20. **በውስን ጨረታ ለመጠቀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች**

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት በአንቀጽ 39 በተደነገገው መሠረት በውስን ጨረታ ግዥ ለመፈፀም የሚችሉት የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያሟሉ ብቻ ነው፡፡

ሀ/ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ በባህርይው በከፍተኛ ደረጃ ውስብስብ ወይም የተለየ በመሆኑ ምክንያት ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝ ሲሆን ወይም፣

ለ/ በርካታ የጨረታ ሰነዶችን ለመመርመር እና ለመገምገም የሚጠይቀው ከፍተኛ ወጪና ጊዜ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ ከሚያወጣው አነስተኛ ዋጋ ጋር የማይመጣጠን ሆኖ ሲገኝ፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) ለሠፈሩት ሁኔታዎች ተሟልተዋል ለማለት የሚቻለው የግዥው ዋጋ ግምት በግዥ መመሪያ ከተመለከተው ጣሪያ ያልበለጠ ሲሆን ነው፡፡

21. **ከአንድ አቅራቢ ለሚፈፀም ግዥ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች**

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት በአንቀጽ 40 በተደነገገው መሠረት ከአንድ አቅራቢ ግዥ የሚፈፅሙት በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ውድድር እንዳይኖር ወይም በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ልዩነት ለመፍጠር ታስቦ መሆን የለበትም፡፡ ሆኖም ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ሲያጋጥም ግዥ ፈፃሚ አካላት ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈፀም ይችላሉ፡፡

ሀ/ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ የተለየ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል ሆኖ ሲገኝ፣

ለ/ በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ ለእቃዎች፣ አገልግሎቶች ወይም ለተገጣሚዎች ተጨማሪ መለዋወጫ ዕቃዎችን ከመጀመሪያው አቅራቢ ግዥው ቢፈፀም የሚገዛው መሣሪያ ወይም አገልግሎት ግዥ ፈፃሚው አካል ከሚጠቀምበት መሣሪያ ወይም አገልግሎት ግዥ ፈፃሚው መግዛት ሲፈልግ ወይም ከሌላ አቅራቢ ከሚጠቀምበት መሣሪያ ወይም አገልግሎት ጋር የማይጣጣም ሆኖ በመገኘቱ ከመጀመሪያው አቅራቢ ተጨማሪ አቅርቦቶችን፣ አገልግሎቶችን ወይም ተገጣሚዎችን መግዛት አስፈላጊ ሲሆን፣

www.chilot.me

ሐ. በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ያልታሰቡ ሁኔታዎች በማጋጠማቸው ምክንያት በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ማሠራት አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ እና የቴክኒክ ወይም በኢኮኖሚ ምክንያቶች እነዚህን ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች ከመጀመሪያው ውል ነጥሎ ማሰራት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ፣

መ/ በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አሸናፊው በግልፅ ወይም በውስን ጨረታ ዘዴ ከተመረጠ በኋላ በተፈረመ ውል የመጀመሪያው ፕሮጀክት ከተከናወነባቸው ዓይነት ተመሳሳይ ሥራዎች በድጋሚ እንዲሠሩ ማድረግ በማስፈለጉ አዲስ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ውል መፈፀም አስፈላጊ ሲሆን፣

ሠ/ በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመጀመሪያ የምክር አገልግሎት ውል አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ መጠናቀቁ እና ውሉ እንዲራዘም ማድረግ ቁጠባንና ቅልጥፍናን የሚያስገኝ መሆኑ በመረጋገጡ አገልግሎቱን መቀጠል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

ረ/ ለአጭር ጊዜ የሚቆይ እና ለግዥ ፈፃሚው አካል ልዩ ጥቅም በሚያስገኝ ሁኔታ የሚፈፀም የዕቃ ግዥ ሲሆን ነው። ይህ ንዑስ አንቀጽ በመደበኛ አቅራቢነት ያልተሠማሩ ድርጅቶች ለሚሸጡዋቸው ዕቃዎች የሚያገለግል ሲሆን፣ በመደበኛ አቅራቢነት ከተሠማሩ አቅራቢዎች አዘውትረው የሚፈፅሙ ግዥዎችን አይጨምርም፣

ሰ/ በጣም አስቸኳይ ከመሆኑ የተነሳ ከባድ ችግር የሚፈጥርና መ/ቤቱ ሥራ አፈፃፀም ላይ ጉዳትን የሚያስከትል በመሆኑ መክንያ ምክንያት በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የተፈቀደ ግዥ፣

2. ግዥፈፃሚ አካላት በግዥ መመሪያው ከሚወሰን የገንዘብ መጠን ያልበለጡ ግዥዎችን ከአንድ አቅራቢ በሚፈጸም የግዥ ዘዴ በመጠቀም መግዛት ይችላሉ።

## 22. በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

ግዥ ፈፃሚ አካላት በአንቀጽ 41 በተደነገገው መሠረት በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ግዥ ለመፈፀም ሚችሉት ለምክር አገልግሎት ወይም ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ ውስጥ የምክር አገልግሎቱ ዋጋ ከ50% ባለይ ለሚሆን ግዥ ነው።

## 23. በዋጋ ማቀረቢያ ለሚፈፀም ግዥ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

ግዥ ፋጻሚ አካላት በአንቀጽ 42 በተደነገገው መሠረት በዋጋ ማቀረቢያ ግዥ ለመፈፀም የሚችሉን ግዥው በገ/ኢ/ል/ቢ.ሮ በሚወጣው የግዥ መመሪያ ከሚወሰነው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ እና የሚገዙትም ለገበያ የተዘጋጁ ዕቃዎች ወይም የታወቀ ገበያ ያላቸው የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች ሲሆኑ ነው።

## 24. በሁለት ደረጃ ግዥ ለመፈጸም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

ግዥ ፈፃሚ አካለት በአንቀጽ 43 በተመለከተው መሠረት በሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥን ለመፊጸም የሚችሉት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው።

1. ለሚገዙት ዕቃዎችና አገልግሎቶች በቂ ዝርዝር ማዘጋጀት በመ/ቤቱ ደረጃ የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ወይም አገልግሎቶችን በሚመለከት ባህሪያቶችን ለይቶ ለማሳየት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ እና መ/ቤቱ የግዥ ፈፃሚው አካል የግዥ ፍላጎቱን በከፍተኛ ደረጃ ለማሟላት የሚያስችል መፍትሔ ለመፈለግ፣
   - ሀ/ ጨረታን፣ የዕቃና የአገልግሎት የአቅርቦት መወዳደሪያ ሀሳብን ወይም የዋጋ ማቀረቢያን በሥራ ማዋል ሲፈልግ፣
   - ለ/ በሚገዙት ዕቃዎች፣ አገልግሎቶች የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችና አገልግሎቶች ባህርይ ወይም ተፈጥሮ ምክንያት ከአቅራቢዎች ወይም ሥራ ተቋራጮ ጋር ድርድር ማድረግ ሲያስፈልግ፣
2. መጠናቸው በገበያ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ዕቃዎችን የሚጨምር ወይም የምርምር እና የልማት ወጪዎችን ለመተካት ካልሆነ በስተቀር ግዥ ገዥ ፈፃሚው አካል የምርምር፣ የሙከራ፣ የጥናት እና የልማት ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ውል ለመፋፀም ሲፈልግ፣
3. ጨረታ እንዲወጣ ተደርጎ ተጫራቾች ውድቅ ሲደረጉ እና መ/ቤቱ ሌላ ጨረታ ቢወጣ ውጤት መገኘቱ አጠራጣሪ ነው ብሎ ሲያምን።

## 25. የቀርጥ ዋጋ ግዥ አቅራረብና አፋፃፀም

የቀርጥ ዋጋ ግዥ ለመንገድ ሥራ፣ ለህንፃ ግንባታ፣ እና ለአከባቢ ልማት ሥራዎች መፈፀም የሚቻልበት

ሁኔታ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ከዚህ በታች የሚከተሉትን በጽሁፍ ለገ/ኢ/ል/ቢሮ ሲያረጋግጥና ቢሮውም ስምምነቱን ሲቀበልና ሲገልጽ ነው፡፡

1. በቁርጥ ዋጋ በመተመን የሚፈፀም ግዥ ከሌሎች የግዥ አፈፃጸም ዘዴዎች በተሻለ ሁኔታ የግዥ ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችል መሆኑን ሲያረጋግጥ፣
2. በሌሎች የግዥ አፈፃጸም ዘዴዎች በመጠቀም የሥራ አፈፃፀሙን የሚያጓትት መሆኑ ስረጋገጥ እና
3. በቁርጥ ዋጋ ግዥ ቢፈፀም ቁጠባንና ቅልጥፍናን የሚያስገኝ መሆኑ ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ አምስት
## ግልፅ ጨረታ

### 26. የጨረታ ማስታወቂያ

1. የጨረታ ማስታወቂያ አገራዊ ሽፋን ባለው ቢያንስ አንድ ጋዜጣ ላይ መውጣት አለበት፡፡
2. ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ለጨረታ ማቀረቢያ የሚሰጠው ጊዜ በግዥ መመሪያ ከሚወሰነው አነስተኛ የቀን ብዛት ያነሰ መሆን የለበትም፡፡

### 27. የጨረታ ጥሪ

የጨረታ ጥሪ ቢያንስ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡፡

1. የግዥ ፈፃሚውን አካል ስምና አድራሻ፣
2. እቃው መቅረብ ወይም ሥራው መጠናቀቅ ያለበትን ጊዜ ጨምሮ የዕቃውን፣ የግንባታ ሥራውን እና አገልግሎቱን አጭር መግለጫ፣
3. የጨረታውን ሰነድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች እና የጨረታ ሰነዱ የሚገኝበትን ቦታ፣
4. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ የሚቀርብበት ቦታ እና የማቅረቢያው የመጨረሻ ጊዜ፣
5. ጨረታው የሚከፈትበትን ቦታ እና ጊዜ እንዲሁም ተጫራቾች ወይም ተወካዮች ጨረታው ሲከፈት መገኘት የሚችሉ መሆኑን የሚገልጽ ማሳሰቢያ፡፡

### 28. የጨረታ ሰነድ

በተጫራቾች መካከል የሚደረገው ውድድር በተሟላ፣ ገለልተኛና ተጨባጭ መሠረት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ ለማድረግ የጨረታው ሰነድ በቂ መረጃ የያዘ መሆን አለበት፡፡ በተለይም ሰነዱ የሚከተሉትን ሊያካትት ይገባል፡፡

1. የጨረታ ሰነዱን ለማዘጋጀትና ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን፣
2. የጨረታ ሰነዱን ማስረከቢያ የመጨረሻ ቀን፣ የጨረታ ሰነዱ የሚላክበትን አድራሻ፣ የጨረታ ሰነዱ የሚከፈትበትን ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ፣ እንዲሁም የተጫራቾች ወኪሎች በጨረታው መክፈቻ ሥነ-ሥረዓት ላይ ሊገኙ የሚችሉ መሆኑን የሚገልፅ መረጃ፣
3. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ማቀረቢያ ቅፆች፣ እንዲሁም አግባብነት እስካለው ድረስ የጨረታ ማስከበሪያ ቅፆች፣
4. ከዋናው የጨረታ ሰነድ ጋር መቅረብ ያለባቸውን ተጨማሪ ኮፒዎች፣
5. የውሉን አጠቃላይ እና ልዩ ሁኔታዎች፣
6. እንደአግባብነቱ ዕቃውን እና አገልግሎቱን አቅርቦቱን ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ለማጠናቀቅ ይወሰዳል ተብሎ የሚገመተውን የጊዜ ገደብ ጨምሮ ተፈላጊውን የዕቃና አገልግሎት ዝርዝር፣
7. ተጫራቹ በጨረታው ለመሳተፍ ብቃት ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያቀርባቸውን መረጃዎች ዓይነት እንዲሁም የፋይናንስ አቋሙን እና በአቅራቢዎች ዝርዝር ወስጥ የተመዘገበ መሆኑን ለማረጋገጥ ማቀረብ ያለበትን መረጃ፣
8. ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፣
9. ጨረታውን ለመገምገም እና በጨረታው አሸናፊ የሆነውን ለማስታወቅ የሚያገለግሉ መስፈርቶችን እና ለእያንዳንዱ መስፈርት የተሰጠውን ነጥብ፣
10. ግዥውን የሚፈፅመው አካል የጨረታው አሸናፊ ይፋ ከመደረጉ በፊት በማናቸውም ጊዜ ጨረታውን የመሠረዝ መብት ያለው መሆኑን፣

### 29. የጨረታ ሰነድ ሽያጭ

የጨረታ ሰነዶች ለጨረታ ሰነድ ዝግጅት እና ሰነዱን ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ለማቅረብ ከወጣው ወጪ ባልበለጠ ዋጋ፣ በተፋጠነ ሁኔታ እና በጨረታ ማስታወቂያው በተገለጸው አኳኋን ለዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲደርሱ መደረግ አለበት፡፡

### 30. በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት በራሳቸው ወይም የጨረታ ሰነድ ከገዙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡ ጥያቄዎች መነሻ የጨረታ ሰነዱ ማቀረቢያ ጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የጨረታ ሰነዶችን ይዘት ለማሻሻል ይችላል፣
2. የተደረገው ማሻሻያ በፅሑፍ ተዘጋጅቶ የጨረታ ሰነዶችን ለገዙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሁሉ በተገቢው ሁኔታ በእኩል እንዲደርስ መደረግ አለበት፣

www.chilot.me

3. ግዥ ፈፃሚው አካል የጨረታ ሰነዱን ይዘት ማሻሻያ አስፈላጊ ሆኖ ያገኘው እና በማሻሻያው የተመለከቱ ማስተካከያዎችን ለማድረግ በቂ ጊዜ የሌለ መሆኑን የተረዳ እንደሆነ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ማሻሻያውን መሠረት አድረገው የጨረታ ሰነዱን ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው ለማድረግ የግዥውን ባህርይ መሠረት በማድረግ የጨረታውን ማቅረቢያ ጊዜ ለተወሰኑ ቀናት ሊያራዝም ይችላል፡፡

## 31. የጨረታ ማስከበሪያ

1. በዚህ አዋጅ በተለይ ካልተወሰነ በስተቀር ግዥ ፈፃሚ አካላት በሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነድ ተጫራቾች ከጨረታ ሰነዶቻቸው ጋር በተቀማጭ ገንዘብ ወይም በጨረታ ዋስትና መልክ የጨረታ ማስከበሪያ የማቅረብ ጌዴታ እንዳለባቸው መግለፅ አለባቸው፡፡ የጨረታ ማስከበሪያው መጠን በጨረታው ኃላፊነት በሞላው ሁኔታ የማይሳተፉትን ለማስቀረት የሚያስችል ሆኖ፣ በግዥ መመሪያው ከተወሰነው መጠን ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
2. የጨረታ ማስከበሪያው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ታጫራቹ ራሱን ከውድድሩ ካገለለ ወይም አሸናፊውን ተጫራች በሚመለከት አሸናፊነቱ ከተገለጸለት በኋላ ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ሆኖ ካልተገኘ ወይም እንዲያቀርብ የተጠየቀውን የውል ማስከበሪያ ካላቀረበ የጨረታ ማስከበሪያው በግዥ ፈፃሚው አካል ውርስ ይደርጋል፤

## 32. የጨረታ ሰነድ ስለማቅረብና ስለመቀበል

1. የጨረታ ሰነድ በፅሁፍ ተዘጋጅቶና ተፈርሞበት በታሸገ ኤንቨሎፕ ውስጥ ሆኖ በጨረታ ማስታወቂያው ከተመለከተው የጊዜ ገደብ በፊት በተገለፀው ቦታ ገቢ መደረግ አለበት፤
2. የጨረታው ሰነድ ትልቅ በመሆኑ በጨረታ ሣጥን ውስጥ ሊቀመጥ የማይችል ከሆነ ግዥ ፈፃሚው አካል የጨረታ ሰነዱ ገቢ የተደረገበትን ቀንና ሰዓት የሚያሳይ ደረሰኝ ለተጫራቹ መስጠት አለበት፤
3. ከዚህ በላይ በተ.ቁ.2 የተገለፀው ዓይነት የጨረታ ሰነድ ለጨረታ ማቅረቢያ ከተወሰነው ጊዜ በኃላ ከቀረበ ሳይከፈት ለተጫራቹ መመለስ አለበት፤

## 33. ጨረታን ስለመክፈት

1. ግዥ ፈፃሚው አካል በጨረታ ሰነዱ የተመለከተው ለጨረታ ሰነድ ማቅረቢያ የተወሰነው የጊዜ ገደብ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ፣ የጨረታ ሰነድ ከማቅረቢያ የጊዜ ገደብ በፊት የተረከባቸውን የጨረታ ሰነዶች መክፈት አለበት፤
2. ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በጨረታ ሰነድ መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ እንዲገኙ መጋበዝ አለባቸው፡፡
3. የተጫራቾች ስም እና በእያንዳንዱ የጨረታ ሰነድ የቀረበው የመጫረቻ ዋጋ ድምር ከፍ ባለ ድምጽ መነበብ እና መመዝገብ እንዲሁም ተጫራቾች በጠየቁ ጊዜ የተመዘገበውን ዝርዝር እንዲያገኙ መደረግ አለበት፤

## 34. የጨረታ ሰነዶችን ስለመመርመር እና ስለመገምገም

1. ጨረታውን ለመመርመርና ግምገማውን ለማከናወን የሚረዳ ሆኖ ሲገኝ፣ ግዥ ፈፃሚው አካል ተጫራቾች ባቀረቡት የጨረታ ሰነድ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ሆኖም የዋጋ ለውጥን ጨምሮ በጨረታው ሰነድ ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስከትል ሀሳብ ማቅረብ ወይም መፍቀድ አይቻልም፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም ግዥ ፈፃሚው አካል በጨረታ ምርመራው ወቅት የተገኙ የሂሳብ ስህተቶችን ለማረም ይችላል፡፡ ግዥ ፈፃሚው አካል እነዚህን ማስተካከያዎች የጨረታ ሰነዱን ላቀረበው ተጫራች በአፋጣኝ መግለፅ አለበት፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ግዥ ፈጻሚው አካል ጨረታው የተሟላ ነው ብሎ ሊቀጥል የሚችለው በጨረታው ሰነድ የተመለከቱትን ተፈላጊ ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ የሚያሟላ ሆኖ ሲያገኘው ነው፤
4. በጨረታው ሰነድ ከተዘረዘሩት ባህሪያት፣ የዉል ቃሎች፣ ሁኔታዎች እና ሌሎችም ተፈላጊ ነጥቦች ጋር በተወሰነ ደረጃ ልዩነት ቢኖረዉም መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እና ልዩነት እስከሌለው ድረስ ወይም የጨረታው ቁምነገር ሳይለውጥ ሊታረም የሚችል ጥቃቅን ስህተት ወይም ግድፈት ቢኖረዉም ግዥ ፈጻሚው አካል ጨረታዉን እንደተሟላ አድርጎ ሊቀበል ይችላል፡፡ ማናቸዉም ልዩነት እስከተቻለ ድረስ በአሀዝ ተገልጾ በጨረታ ግምገማ እና ዉድድር ወቅት ከግምት ዉስጥ መግባት አለበት፡፡
5. ማናቸዉም ግዥ ፈጻሚ አካል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የማያሟሉ ጨረታዎችን ለዉድድር ማቅረብ የለበትም፡፡

ሀ. ተጫራቹ በአንቀጽ 28 (ለ) የተጠቀሱትን መስፈርቶች ማሟላት የማይችል ሆኖ ሲገኝ፣

ለ. ተጫራቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የተደረገዉን የሂሳብ ማስተካከያ የማይቀበል ሆኖ ሲገኝ፣

ሐ. የቀረበው የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ተፈላጊዉን የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ::

6. ግዥ ፈጻሚው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 በተደነገገው መሠረት አሸናፊዉን ተጫራች ለመምረጥ በጨረታ ሰነዱ በተመለከተው ስርዓት እና የግምገማ መስፈርት መሠረት ተፈላጊዉን ያሟሉ የጨረታ ሰነዶችን መገምገምና ማወዳደር አለበት:: በጨረታ ሰነድ ያልተመለከተ የማወዳደሪያ መስፈርት በጥቅም ላይ ሊዉል አይችልም::

7. በጨረታ አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው፣

ሀ. በጨረታ ግምገማ የቴክኒክ መመዘኛዎችን ማሟላት የተረጋገጠ እና አነስተኛ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች፣ ወይም

ለ. ግዥ ፈጻሚው አካል በጨረታ ሰነድ ውስጥ አሸናፊው ተጫራች የሚመረጥበትን መስፈርት የገለጸ ከሆነ፣ በጨረታ ሰነዱ የሰፈረውን የጨረታውን ኢኮኖሚያዊ እሴት የሚወስነውን መስፈርት መሠረት በማድረግ በሚካሄድ ግምገማ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ተጫራች አሸናፊ ይሆናል:: ሆኖም መስፈርቱ በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ በአኃዝ ሊገለጽ የሚችል ሆኖ በግምገማው ሂደት አንጻራዊ ክብደት የሚሰጠው እና እስከተቻለ ድረስ በገንዘብ የሚገለጽ መሆን አለበት፤

8. ግዥ ፈፃሚው አካል የጨረታ ሰነድ ምርመራና የግምገማውን ውጤት በአጭሩ የሚገልጽ የግምገማ ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት::

## 35. በሚስጥር ስለሚያዙ አሠራሮች

1. ጨረታው ከተከፈተበት ጊዜ አንስቶ ከጨረታ ምርመራ፣ ከማብራሪያ ከግምገማ እና አሸናፊውን ተጫራች በሚመለከት ከቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ጋር የተያያዙ መረጃዎች በሚስጥርነት መጠበቅ ያለባቸው ሲሆን፣ አሸናፊው ተጫራች እስከ ሚገለጽ ድረስ ለተጫራቶች ወይም ከሥራው ሂደት ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ሰዎች መገለጽ የለባቸውም፤

2. ጨረታው ከተከፈተበት ጊዜ አንስቶ ውሉ እስከሚፈረም ድረስ ማናቸውም ተጫራች በማናቸውም አኳኋን የጨረታውን ምርመራና ግምገማ ለማዛባት መሞከር የለበትም፤

3. ጨረታው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ውሉ እስከሚፈረም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ዕጩ ተወዳዳሪ ከጨረታው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ከግዥ ፈፃሚው አካል ጋር ግንኙነት ማድረግ የሚችለው በጽሁፍ ብቻ ይሆናል::

## 36. በጨረታው አሸናፊ እንዲሆኑ ለማድረግ ተጫራቾች ያቀረቡትን የመወዳደሪያ ሀሳብ አሻሽለው እንዲያቀርቡ በቅድመ ሁኔታነት መጠየቅ የማይቻል ስለመሆን

ማናቸውም ተጫራች በጨረታው ሰነድ ከተመለከተው ውጪ፣ በጨረታው አሸናፊ ለመሆን ያቀረበውን የመጫረቻ ዋጋ እንዲለዉጥ ወይም በሌላ አኳኋን ያቀረበውን መወዳደሪያ ሃሳብ እንዲያሻሽል ወይም ይህንን ለመፈጸም ግዴታ እንዲገባ በቅድመ ሁኔታነት ሊጠየቅ ወይም ሊገደድ አይችልም::

## 37. አሸናፊነት ስለመግለጽ እና ዉል ስለመፈረም

1. ግዥ ፈጻሚ አካላት የመወዳደሪያ ሀሳቡ ፀንቶ የሚቆይበት ቀን ከማለፉ በፊት በጨረታው አሸናፊ ለሆነው ተጫራች አሸናፊነቱን መግለጽ አለባቸው:: የአሸናፊነት መግለጫ ማስታወቂያው ዉሉ የሚፈረምበትን ጊዜ የሚገልጽ ይሆናል:: በጨረታው ተሸናፊ ለሆኑ ተጫራጮችም የአሸናፊዉን ምክንያት የሚገልጽ ማስታወቂያ ሊደርሳቸው ይገባል፤

2. በግዥ ፈጻሚው አካል እና በአቅራቢው መካከል ዉል ተመስርቷል የሚባለው በሁለት ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የተደረሰባቸዉን ጉዳዮች በሙሉ የሚይዘው የዉል ሰነድ ሲፈረም ይሆናል፤

3. ግዥ ፈጻሚው አካል ለተሸናፊዎቹ ተጫራቾች ተሸናፊነታቸዉን የሚገልጸው ማስታወቂያው ከመድረሱ እና በአንቀጽ 37 የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የግዥዉን ዉል መፈረም የለበትም::

## 38. ዉል ማስከበሪያ

አቅራቢው በዉሉ መሠረት ባለመፈጸሙ በግዥ ፈጻሚው አካል ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ማካካሻ የሚዉል የዉል ማስከበሪያ ለግዥ ፈጻሚው አካል መስጠት አለበት:: የዉል ማስከበሪያ የሚጠየቅባቸው የግዥ ዓይነቶች፣ የዉል ማስከበሪያው አይነትና መጠን ገ/ኢ/ል/ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

www.chilot.me

## ምዕራፍ ስድስት
## ሌሎች የግዥ ዘዴዎች

### 39. ዉስን ጨረታ

የዉስን ጨረታ ሥርዓቶች ከግልጽ ጨረታው ጋር ተመሳሳይ ሲሆኑ፣ የዉስን ጨረታው የሚከተሉት ልዩ አሠራሮች ይከተላሉ፡፡

1. የጨረታ ጥሪው በጨረታው ለመሳተፍ ፍላጎት ላላቸው የተወሰኑ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ብቻ ይላካል፡፡ ተጫራቾች አድልዎ በሌለበት ሁኔታ መመረጥ ያለባቸው ሲሆን፣ የሚቻል እስከሆነ ድረስ ጥሪ የሚደረግላቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች ብዛት ዉጤታማ የሆነ ዉድድር እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል መሆን አለበት፡፡
2. ግዥ ፈጻሚ አካላት በዉስን ጨረታ ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪ የሚደረግላቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚመረጡት በአቅራቢዎች ዝርዝር ዉስጥ ለተመዘገቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ፍትሃዊ የሆነ እድል የሚያስገኝ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በላይ የተነገረው ቢኖርም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ጥሪ ቢደረግላቸው በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ መሆኑን መግለጽ እንዲችሉ ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27(1) በተደነገገው መሠረት ማስታወቂያ ለማውጣት ይችላል፤
3. ለጨረታው ሰነድ ዝግጅት የሚፈቀደው ጊዜ በግዥ መመሪያው ከተወሰነው አነስተኛው የቀን ብዛት ያነሰ ሊሆን አይችልም፤
4. ግዥ ፈጻሚው አካል የግዥዉን ሁኔታ መሠረት በማድረግ የጨረታ ማስከበሪያ ማቅረብ የሚያስፈልግ መሆን ያለመሆን ይወስናል፡፡

### 40. ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ

1. ግዥ ፈጻሚው አካላት በአንቀጽ 21 (1) በተደነገገው መሠረት ከአንድ አቅራቢ ግዥ ለመፈጸም ሲፈልጉ ግዥዉን መፈጸም ያስፈለገበትን ምክንያት እና የሚገዛዉን ዕቃ ወይም አገልግሎት ጥራት፣ ብዛት፣ የማቅረቢያ ጊዜና ሁኔታዎች የሚያብራራ መግለጫ ማዘጋጀትና ከአቅራቢው ጋር በግልጽ መደራደር አለባቸው፡፡ ድርድሩ ከተካሄደ በኋላ በአንቀጽ 21(1) መሠረት ግዥ ለመፈጸም የሚደረሰው ስምምነት በሁለት ተዋዋይ ወገኖች በሚፈረም ዉል መረጋገጥ አለበት፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 (2) በተደነገገው መሠረት ከአንድ አቅራቢ ለሚፈጸም ግዥ ዉል መዋዋል አስፈላጊ አይደለም፡፡

### 41. በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ የሚፈጸም ግዥ

1. የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ከሦስት ላላነሱ እና ከሰባት ላልበለጡ በግዥ ፈጻሚው አካል ለሚመረጡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች መላክ ይኖርበታል፡፡ የምክር አገልግሎቱ የሚጠይቀው ወጪ በመመሪያ ከሚወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ ከሆነ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚመረጡት በዉድድሩ ተሳታፊ ለመሆን የሚፈልጉ ሀሳባቸዉን እንዲገልጹ ከተጠየቀ በኋላ ይሆናል፡፡
2. የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፣
   ሀ. ግዥ ፈጻሚው አካል ስምና አድራሻ፣
   ለ. የሚፈለገዉን አገልግሎት የሚያሳይ የማጣቀሻ ጽሑፍ፤
   ሐ. የጥቅም ግጭትን ሊያስከትል የሚችል የምክር አገልግሎት በሚሆንበት ጊዜ በዚህ ዓይነቱ ዉድድር የሚቀርቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከምክር አገልግሎቱ በማስከተል ከምክር አገልግሎት ጋር በተያያዘ ከሚከናወኑ የዕቃ አቅርቦትና የግንባታ ሥራዎች ራሳቸዉን ማግለል የሚገባቸው መሆኑን የሚገልጽ ማሳሰቢያ፤
   መ. የመወዳደሪያ ሀሳቦችን መገምገሚያ መስፈርቶችን፣ለዋጋና ለሌሎች መስፈርቶች የሚሰጠዉን ነጥብ፣ መስፈርቶቹ የመወዳደሪያ ሀሳብ የሚገመገምበት ወቅት ጥቅም ላይ የሚዉሉበተን አኳኋን፣
   ሠ. የመወዳደሪያ ሀሳብ የሚቀርብበትን ቦታና የመጨረሻ ቀን፡፡
3. ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመወዳደሪያ ሀሳብ ለማዘጋጀት የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፤
4. ግዥ ፈጻሚው አካል አንደኛ ሆኖ ከተመረጠው ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር በመወዳደሪያ ሀሳቡ ዉስጥ የተመለከተዉን የአገልግሎቱን ባህሪ ፣ መጠን እና አደረጃጀት የሚመለከት ድርድር ማካሄድ ወይም ማሻሻያ እንዲደረግ መፍቀድ ይችላል፤
5. ግዥዉን የሚፈጽመው መ/ቤት በአሸናፊነት ሊመርጥ የሚችለው በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ሰነድ በተመለከተው የመገምገሚያ መስፈርት እና ሥርዓት መሠረት በሚካሄደው ግምገማ ያቀረበው የመወዳደሪያ ሀሳብ ይበልጥ ጠቃሚ ሆኖ የተገኘዉን ተወዳዳሪ ነው፡

### 42 በዋጋ ማቅረቢያ የሚካሄድ ግዥ ሥርዓት

1. ግዥ ፈጻሚ አካላት የዋጋ ማቅረቢያ ብዛት ካላቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች መጠየቅ አለባቸው፡፡

www.chilot.me

ስለሆነም የሚቻል እስከሆነ ድረስ ቢያንስ ሦስት አቅራቢዎች የዋጋ ማቅረቢያ እንዲሰጡ ሊጠየቁ ይገባል፤

2. በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈጸም ግን ለዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚላኩ መጠየቂያ የሚቀርበዉን ዕቃ ወይም አገልግሎት ጥራት፣ ብዛት፣ የማቅረብያዉል ቃሎች እና ጊዜ እንዲሁም ሌሎች የግዥ ፈጻሚውን አካል ፍላጎቶች የሚይዝ መሆን አለበት፤

3. ዕጩ ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያዉን ለማዘጋጀት የሚያስችል በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፤

4. ግዥ ፈፃሚው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩትን ተፈላጊ ሁኔታዎች ለሚያሟላ እና አነስተኛ ዋጋ ላቀረበ ተወዳዳሪ የግዥ ትዕዛዝ ይሰጣል፤

5. ግዥ ፈፃሚ አካላት በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ አቅራቢዎች እኩል ዕድል ማግኘታቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው።

## 43. የሁለት ደረጃ ጨረታ

1. ጨረታው የሚከናወነው በሁለት ደረጃ የጨረታ ዘዴ ሲሆን፣ በጨረታው ሰነድ ተጫራቾች በመጀመሪያው ደረጃ ዋጋን ያልጨመረ የመወዳደሪያ ሀሳብ እንዲያቀርቡ ጥሪ ይደረጋል። በጨረታው ሰነድ አቅራቢዎች ከቴክኒክ ጋር ግንኙነት ያላቸው መግለጫዎች፣ ጥራት ወይም የዕቃዉን ወይም የአገልግሎቱን ሌሎች ባህርያት እንዲሁም እንዲሁም የአቅረቦቱን ዉል ቃሎችና ሁኔታዎች እና አግባብነት እስካለው ድረስ የአቅራቢዎች የሙያ እና የቴክኒክ ችሎታ እንዲገልጹ ሊጠየቁ ይችላል።

2. በሁለት ደረጃ ጨረታ ዘዴ ሁለተኛ ደረጃ፣ ጨረታዉን ያወጣው ግዥ ፈጻሚ አካል ጨረታቸዉ ውድቅ ያልተደረገው ተጫራቾች አንድ የተለየ ዝርዝርን በሚመለከት ዋጋ እንዲያቀርቡ ይጋብዛል። ይህንን የተለየ ዝርዝር ሲያዘጋጅ መ/ቤቱ በመጀመሪያ የጨረታ ሰነድ ዉስጥ ከተቀመጡት ማናቸዉም የዕቃው ወይም የአገልገሎቱ የቴክኒክ ወይም የጥራት ባህርያት እና ሰነዶቹን ለመገምገም እና ለማወዳደር እንዲሁም አሸናፊዉን ለመምረጥ ከተቀመጡት መስፈርቶች ዉስጥ ማናቸዉንም ለመሠረዝ ወይም ለማሻሻል ወይም ከዚህ አዋጅ ጋር የሚስማሙ አዳዲስ ባህርያትንና መስፈርቶችን ለመጨመር ይችላል። እንደዚህ ያሉት ማናቸዉም ሥራዎች መሻሻያዎች ወይም ጭማሪዎች የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሀሳብ እንዲቀርብ በሚተላለፍ ጥሪ ለተጫራቾች መግለጽ አለባቸው የመጨረሻ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ለማቅረብ ያልፈለገ ማናቸዉም አቅራቢ የጨረታ ማስከበሪያው ዉርስ ሳይደረግበት ከጨረታው ዉድድር እራሱን ሊያገል ይችላል።

3. በሁለት ደረጃ ጨረታ አሸናፊዉን ተጫራች ለመወሰን ግምገማ እና ዉድድር የሚያደርገው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 43 በተደነገገው መሠረት ይሆናል።

4. ጨረታዉን ያወጣው ግዥ ፈጻሚ አካል በጨረታ ግምገማ ከፍተኛ ዉጤት ካገኘው አቅራቢ ጋር ከዋጋ በስተቀር በሌሎች ጉዳዮች ላይ ድርድር ሊያደርግ ይችላል።

## ምዕራፍ ሰባት

## ዓለም ዐቀፍ የግዥ ዘዴ

## 44. ዓለም ዓቀፍ የግዥ ጨረታ

1. ዓለም ዐቀፍ ግልጽ የጨረታ ዘዴ ጥቅም ላይ ሊዉል የሚችለው የዉጭ ኩባንያዎች በጨረታው ተሳታፊ እንዲሆኑ ካልተደረገ በግልጽ ጨረታው ዉጤታማ የሆነ ዉድድር ሊኖር እንደማይችል የታመነበት እና ግዥው ገ/ኢ/ል/ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ ሲሆን ነው።

2. ዓለም ዐቀፍ ግልጽ ጨረታ በምዕራፍ 5 የተጠቀሱትን እንዲሁም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሥርዓቶች መከተል አለበት።

 ሀ. የጨረታ ማስታወቂያ እና የጨረታ ሰነዶች የአለም ዐቀፍ ንግድ መገልገያ በሆነ ቋንቋ መዘጋጀት አለባቸው።

 ለ. የጨረታ ማስታወቂያው በተዘጋጀበት ቋንቋ በሚታተም፣ በቂ ሥርጭት ባለው እና ዓለም አቀፍ ዉድድርን በሚጋብዝ ጋዜጣ ላይ የጨረታ ማስታወቂያው መታተም አለበት።

 ሐ. የጨረታ ሰነድ የማቅረቢያ ጊዜው የጨረታው ማስታወቂያ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲደርስ ለማድረግ እና ዕጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳባቸዉን አዘጋጅተው ለማቅረብ የሚያስፈልጋቸዉን በቂ ጊዜ የሚፈቅድ መሆን አለበት።

www.chilot.me

መ. የዕቃና የአገልግሎት ዝርዝር ከአገር ውስጥ ደረጃዎች ጋር የሚወጣም ሆኖ በዓለም ዐቀፍ ደረጃዎች ወይም በዓለም ዐቀፍ ንግድ በስፋት የሚሠራበትን ደረጃ መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

ሠ. ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ዋጋቸዉን እንዲሁም የሚያቀርቡትን ማናቸዉንም የዋስትና ሰነድ በኢትዮጵያ ብር ወይም በጨረታ ሰነዱ በተመለከተው እና በዓለም ዐቀፍ ንግድ በስፋት የሚሠራበት የገንዘብ ዓይነት እንዲያቀርቡ መፈቀድ አለበት፡፡

ረ. አጠቃላይ እና ልዩ የዉል ቃሎችና ሁኔታዎች በዓለም ዓቀፍ ንግድ የሚሠራባቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## 45. ሌሎች ዓለም ዐቀፍ ሥርዓቶች

ከግልጽ ጨረታ ዉጪ እንደዉስን ጨረታ ወይም የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ባሉት የግዥ ዘዴዎች የዉጭ አገር ኩባንያዎች እንዲሳተፉ ካልተደረገ ዉጤታማ የሆነ ዉድድር ሊኖር እንደማይችል ከታመነበት ከምዕራፍ አምስት በተጨማሪ እስከተቻለ ድረስ የአንቀጽ 41 (2) ድንጋጌዎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

## ምዕራፍ ስምንት
## በመንግሥት ግዥ ላይ ስለሚቀርብ አቤቱታ

## 46. ጠቅላላ

1. የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆነው፣ ግዥዉን በፈጸመው አካል የተከናወነው ወይም ሳይከናወን የቀረው ተግባር የዚህን አዋጅ፣ የግዥ መመሪያዉን ወይም እንዚህን መሠረት በማድረግ የተላለፉ ትዕዛዞችን ይጥሳል ብሎ የሚያምን ዕጩ ተወዳዳሪ በአስተዳደር አካላት ተጣርቶ ዉሳኔ እንዲሰጥበት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችልል፡፡
2. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በዚህ ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት አቤቱ ሊቀርብባቸው አይችልም፡፡

ሀ. በምዕራፍ አራት በተደነገገው መሠረት የሚከናወን የግዥ ዘዴዎች ምርጫ፣

ለ. በአንቀጽ 17 መሠረት ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሀሳብ ወይም የዋጋ ማቅረቢያን ዉድቅ ለማድረግ የሚሰጥ ዉሳኔ፡፡

3. ግዥ ፈጻሚው አካል በጨረታው አሸናፊ ከሆነው ተወዳዳሪ ጋር የግዥ ዉል ከፈረመ በኋላ፣ ዉድድሩ ከዚህ ደረጃ እስከሚደርስ ድረስ በተከናወኑ ወይም ሳይከናወኑ በቀሩ ተግባራት ምክንያት የሚቀርቡ አቤቱታዎች በአስተዳደር አካላት ሊታዩ አይችሉም፡፡

## 47. ለግዥ ፈጻሚው አካል የበላይ ኃላፊ ስለሚቀርቡ አቤቱታዎች

1. በግዥ ፈጻሚው አካል በተከናወነ ወይም ሳይከናወን በቀረ ተግባር ምክንያት የሚቀርብ አቤቱታ በመጀመሪያ ደረጃ መቅረብ ያለበት ለግዥ ፈጻሚው አካል የበላይ ኃላፊ ይሆናል፡፡
2. ዕጩ ተወዳዳሪው አቤቱታዉን ሊያቀርብ የሚችለው ለአቤቱታው መሠረት የሆነዉን ዉሳኔ ካወቀበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት ቀን ጀምሮ በአምስት የሥራ ቀን ጊዜ ዉስጥ ይሆናል፡፡
3. አቤቱታው በሁለቱ ወገኖች መካከል በሚደረግ ስምምነት ካልተፈታ በስተቀር የግዥ ፈጻሚው አካል የበላይ ኃላፊ የግዥዉን አፈጻጸም ማገድ እና አቤቱታው ከቀረበበት ቀን አንስቶ በ15 ቀን ጊዜ ዉስጥ፣ ዉሳኔው የተሰጠበትን ምክንያት ወይም አቤቱታው ተቀባይነት ጥገኛ ከሆነ የሚወሰደውን የማስተካከያ እርምጃ በመጥቀስ የጽሑፍ ዉሳኔ መስጠት አለበት፡፡
4. የግዥ ፈጻሚው አካል የበላይ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተወሰነው ጊዜ ዉስጥ ዉሳኔ ካልሰጠ ወይም ተወዳዳሪው በግዥ ፈጻሚው አካል የበላይ ኃላፊ ዉሳኔ ያልረካ እንደሆነ የግዥ ፈጻሚው አካል ዉሳኔ ከተገለጸለት ቀን አንስቶ የሚቆጠር 5 የሥራ ቀን ጊዜ ዉስጥ ለ/ገ/ኢ/ል/ቢሮ አቤቱታ ሊያቅርብ ይችላል፡፡

## 48. ግዥን በተመለከተ ለሚቀርቡ አቤቱታዎች

1. ቢሮው አቤቱታ ሲቀርብለት ወዲያዉኑ አግባብ ላለው ግዥ ፈጻሚ አካል አቤቱታ የቀረበ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ ይልካል፡፡ አቤቱታ የቀረበ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ እንደተላከ ግዥ ፈጻሚው አካል ቢሮው በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ማናቸዉንም ቀጣይ እንቅስቃሴ ወዲያዉኑ ማቆም አለበት፡፡
2. ቢሮው የዕጩ ተወዳዳሪዉን አቤቱታ ዉድቅ ካላደረገው በስተቀር፣ ግዥ ፈጻሚው አካል ሕጉን ያልጠበቀ ተግባር እንዳያከናዉን እና ዉሳኔ እንዳይሰጥ ሊያግድ ወይም ከሕግ ዉጭ የሆነዉን የግዥ ሥርዓት እንዳይከተል ሊያደርግ ወይም ግዥ ፈጻሚው አካል በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ሥራዉን እንዲያከናዉን ትዕዛዝ

ሲያስተላልፍ፣ አሸናፊዉን ተጫራች ከመምረጥ ወይም ዉል ከመፈረም ጋር ከተያያዙ ዉሳኔዎች በስተቀር ግዥ ፈጻሚው አካል ሥራዉን እንዲያከናዉን ወይም ግዥ ፈጻሚው አካል ከህግ ዉጪ ያከናወነው ተግባር ወይም የሰጠው ዉሳኔ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

3. ቢሮው አቤቱታው ላይ ዉሳኔ ከመስጠቱ በፊት ስለአቤቱታው ለማወቅ ፍላጎት ላላቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች ማሳወቅ፣ ከእነዚህ ተወዳዳሪዎች እና ከግዥ ፈጻሚው አካል የቀረበዉን መረጃ እና መከራከሪያ መመርመር አለበት፡፡

4. ቢሮው አቤቱታው ከቀረበለት ቀን አንስቶ በ15 ቀናት ዉስጥ ለዉሳኔው መሠረት የሆኑትን ምክንያቶች እና የተወሰዱትን የመፍትሔ እርምጃዎች በመጥቀስ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

49. ጥፋቶችና ቅጣቶች

1. ይህንን አዋጅ ለመፈጸም በማናቸዉም የመንግሥት መ/ቤት የተሸመ ወይም የተመደበ ሰው፡-

   ሀ. በሕግ መሠረት ሊከፈለው ከሚገባ በስተቀር የተመደበበትን ሥራ በማከናወኑ ማናቸዉንም ክፍያ ከተቀበለ፤

   ለ. የመንግሥት መ/ቤትን የግዥ አሠራር በማጭበርበር ወይም ሌላ ሰው እንዲያጭበረብር ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተባበረ ወይም ያሴረ፤

   ሐ. ሕጉን የጣሰ ወይም በሌላ ማንኛዉም ሰው ሕጉ እንዲጣስ ሆን ብሎ የፈቀደ፤

   መ. በፈቃደኝነት በማናቸዉም መንገድ ሀሰተኛ ሰነድ ላይ የተፈረመ ወይም የመዘገበ ወይም ሀሰተኛ የምስክር ወረቀት የሰጠ፣ ከብር 25 ሺ.ህ/ከሃያ አምስት ሺ.ህብር/ በማያንስ ከብር 35ሺ.ህ/ከሠላሳ አምስት ሺ.ህ ብር/ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫና ከ10 ዓመት በማያንስና ከ15 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

2. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም የተቀጠረ ማናቸዉም የግዥ ባለሙያ በዚህ አዋጅ ይፋ እንዲሆን ከታዘዘው ዓይነት መረጃ በስተቀር፡-

   ሀ. ግዥዉን በማስፈጸም ረገድ ባለው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ምክንያት ያወቀዉን የሌላ ሰው ማናቸዉንም መረጃ ለማናቸዉም ሌላ ሰው ወይም የዚህ ሰው ወኪል ለሆነ ሰው አሳልፎ የሰጠ፤

   ለ. በዚህ አዋጅ መሠረት ግዥን በማከናወን ረገድ ያለዉን ሥልጣን ለማስፈጸም ወይም የሥራ ግዴታዉን ለመወጣት እንዲያስችል ግዥዉን በሚፈጽመው መ/ቤት ዘንድ የሚገኘዉን ማናቸዉንም መረጃ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 10, 000 በማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና ከ2/ሁለት ዓመት በማያንስ፣ ከ5/አምስት/ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

3. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ሥራ ላይ ለማዋል ግዥዉን በሚፈጽመው መ/ቤት የተቀጠረ ሠራተኛ፡-

   ሀ. በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የገንዘብ ወይም ሌላ ዓይነት ክፍያ ወይም ስጦታ እንዲያደርግለት የጠየቀ ወይም የተቀበለ ለክፍያው ወይም ለስጦታው ተስፋ ወይም መያዣ የጠየቀ ወይም የተቀበለ፣ ወይም ፤

   ለ. በግዥ ተግባር ላይ ማጭበርበር ወይም ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር ወይም ከተሰጠው ኃላፊነት መልካም አፈጻጸም ጋር የሚቃረን ተግባር ለመፈጸም፣ ማድረግ የሚገባዉን ከማድረግ ለመታቀብ፣ ተገቢ ያልሆነን ነገር ለመፍቀድ፣ በግዥ ላይ የሚፈጸምን የማጭበርበር ተግባር ለመደበቅ፣ ወይም በሚስጥር ለመተግበር ዉል የገባ ወይም በሚገባው ዉል ዉስጥ በዚህ ተግባር መተባበሩን የሚያሳይ ስምምነት የሰጠ፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 50 ሺ.ህ የማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ10 ዓመት በማያንስ ከ20 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

4. ማንኛዉም ሰው በመንግሥት ግዥ ላይ ለተሾመ ወይም ለተመደበ ሰው፡-

ሀ. የቀረበለትን ዉሳኔ በመጠበቅ ላይ ያለዉን ጉዳይ ወይም በሥራ ኃላፊነቱ ምክንያት ሊቀርብለት በሚችል ጉዳይ ላይ የሚሰጠዉን ዉሳኔ ወይም የሚወስደዉን እርምጃ ለማዛባት ወይም፤

ለ. በመንግሥት ግዥ ላይ የማጭበርበር ድርጊት እንዲፈጸም ወይም ድርጊቱ ሊፈጸም እንዲረዳ ወይም እንዲተባበር ወይም ለድርጊቱ መፈጸም ሁኔታዎችን ለማመቻቸት እንዲስማማ እንዲመሳጠር ወይም እንዲፈቀድ ለማድረግ በማሰብ ጉቦ ለመስጠት ቃል ከገባለት ከቀረበለት ወይም ከሰጠው ጥፋተኛ ሆኖ መገኘቱ ሲረጋገጥ በወንጀል ሕግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ከብር 50 ሺህ ያላነሰ የገንዘብ መቀጫ እና ከ10 ዓመት የማያንስ እና ከ20 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

## 50. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የክልሉ ካቢኔ እንደ አስፈላጊነቱ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።
2. ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ቢሮው መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## 51. የተሻሩና ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች

1. ይህ አዋጅ ከሚፀናበት ቀን ጀምሮ፣
   ሀ. በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 9/1991 አንቀጽ 54 እስከ አንቀጽ 56፣
   ለ. በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት መስተዳደር ምክር ቤት የፋይናንስ ደንብ ቁጥር 3/93 አንቀጽ 66-73፣ ተሽረዋል።
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛዉም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረዉም።

## 52. በግዥ ሂደት ላይ ያለ

ይህ የግዥ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በግዥ ሂደት ላይ ያሉና ያልተጠናቀቁ ቢኖሩ በቀድሞው የግዥ መመሪያ መሠረት ይፈጸማሉ።

## 53. አዋጁ የሚፀናበት

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ከታተመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር ነሐሴ 17 ቀን 1999 ዓ.ም
ሙራድ አብዱልሐዲ
የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት
ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐ ረ ር ነ ጋ ሪ ጋ ዜ ጣ
# HARAR NEGARI GAZETA
OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

12ኛ ዓመት ቁጥር 3
12th year No 3

ሐረር ነሐሴ 17 ቀን 1999
Harar, Aug. 23 / 2007

ያንዱ ዋጋ ብር 7.00
Unit price Birr.7.00

በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት
ጠባቂነት የወጣ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር 952
P .O. Box 952

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 70 /1999
የሐረሪ ሕ/ክልላዊ መንግስት የአስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ............................ ገጽ 534

## አዋጅ ቁጥር 70/1999

## የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀትና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

አሁን በሥራ ላይ ያለው አስፈፃሚ አካል አደረጃጀት በተግባር ሲታይ በተወሰኑ መሥሪያ ቤቶች የማስፈጸም ብቃት ማነስ በዋንኛነት የታየ ሲሆን ፣ በአንዳንድ ሥራዎች የመበታተንና የመደጋገም ሁኔታዎች እንዲሁም ሴክተር መሥሪያ ቤቶች ቀደም ሲል የነበራቸው የማስፈጸም አቅም እየተዳከመ የሄደበት ሁኔታ በመኖሩ ፤

በዚህም የተነሳ ችግሩን ለመቅረፍ የመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን በአግባቡ ለመፈጸም የሚያስችል አደረጃጀት ለመፍጠር የቢሮዎችን እና የጽ/ቤቶችን አደረጃጀት ለማሻሻል የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖረው በማስፈለጉ፤

የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት ምክር ቤት በ1997 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው ህገ-መንግስት አንቀጽ 51 (2) /ሀ/ ላይ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 70/1999 » ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

1. «ክልል ምክር ቤት » ማለት በሐረሪ ሕዝብ ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ 46 /1/ የተመለከተው የክልሉ መንግስት ከፍተኛ የሕግ አውጪ አካል ነው።
2. «መስተዳድር ምክር ቤት » ማለት በሐረሪ ሕዝብ ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ 46/2 የተመለከተው የክልሉ መንግስት ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል ነው።
3. «ቢሮ ወይም መሥሪያ ቤት» ማለት በዚህ አዋጅና በሌሎች ህጎች መሰረት በክልሉ መንግስት የተቋቋሙ የክልሉ መንግስት ቢሮዎች ፣ ኮሚሽኖች ፣ ኢንስቲቲዩቶች ፣ ተቋማትና ሌሎች መሰል አስፈፃሚ አካላትን ይጨምራል።

www.chilot.me

4. «የቢሮ ኃላፊ ወይም ምክትል ኃላፊው» ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ከንዑስ አንቀጽ /1/ እስከ /9/ ከተመለከቱት ቢሮዎችና ሌሎች መሥሪያ ቤቶች መካከል አንዱን የሚመራና የመስተዳድሩ ምክር ቤት /ካቢኔ/ አባል የሆነ ወይም ምክትሉ ማለት ነው።

## ክፍል ሁለት

## ስለ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት

### 3. የክልል መስተዳድር ምክር ቤት አወቃቀርና አደረጃጀት

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት /ካቢኔ/ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።
   ሀ/ ርዕሰ መስተዳድር፤
   ለ/ ም/ርዕሰ መስተዳድር፤
   ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ስር የተመለከቱትን ቢሮዎች የሚመሩ ኃላፊዎች፤
   መ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ስር ከተመለከቱት ውጭ ርዕሰ መስተዳድሩ የመስተዳድር ም/ቤት አባላት እንዲሆኑ በተለይ የሚመርጣቸው ሌሎች የቢሮ ኃላፊዎችና ባለሥልጣናት፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 /ሐ/ ሥር የተመለከተው ማንኛውም የቢሮ ኃላፊ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ እንደ ሁኔታው ምክትሉ ወይም ከአንድ በላይ ምክትሎች ካሉ በግልጽ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ምክትል በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በምክትል አባልነት ይሳተፋል።

### 4. ቢሮዎች ስለ መቋቋም

የሚከተሉት መስተዳድር ምክር ቤት አባል የሆኑ ቢሮዎች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-

1. የትምህርት ቢሮ ፤
2. የአቅም ግንባታ ቢሮ ፤
3. የባህል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤
4. የግብርናና የገጠር ልማት ቢሮ፤
5. የፍትህና ፀጥታ ጉዳይ ቢሮ፤
6. የንግድ ኢንዱስትሪ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ፤
7. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፤
8. የጤና ጥበቃ ቢሮ እና
9. የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ናቸው።

### 5. ጽህፈት ቤቶችን ስለማቋቋም

የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት አስፈጻሚ አካላት የሆኑ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጽህፈት ቤቶች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-

1. ማህበራት ማደራጃ፤ ሕዝብ አደረጃጀት፤ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት፤
2. የወጣቶችና ስፖርት ጽህፈት ቤት፤
3. የጥቃቀንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ሥራዎች ማስፋፊያ ጽህፈት ቤት፤
4. የገቢዎች ባለሥልጣን ፤
5. የአደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ጽህፈት ቤት እና
6. የመንገድ ሥራ ባለሥልጣን ናቸው።

### 6. የቢሮዎች ተጠያቂነት

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ከንዑስ አንቀጽ /1/ እስከ /9/ የተዘረዘሩት ቢሮዎች በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለሚያሳልፉት ውሳኔ የጋራ ኃላፊነትና ተጠያቂነት አለባቸው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ ቢሮና አስፈጻሚ አካል የተቋቋሙለትን ዓላማ መሠረት በማድረግ በዚህ አዋጅ እና በሌሎችም አዋጆች ተለይተው የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች የመወጣት ግዴታ አለባቸው።

### 7. የቢሮ ኃላፊዎች ተጠሪነት

1. የቢሮ ኃላፊዎች ፤ የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሥራ አስኪያጅ እና ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ተጠሪነት ለርዕሰ መስተዳድሩና ለመስተዳድሩ ምክር ቤት ይሆናል።
2. የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ ተጠሪነት ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል።
3. በዚህ አንቀጽ ን ዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ ከተ መለከተት ውጪ ያሉ ቢሮዎችና ሌሎች መስሪያ ቤቶች ኃላፊዎች ተጠሪነት እንደ አግባብነቱ ለሚመለከተው ቢሮ ኃላፊ ወይም አካል ይሆናል።

### 8. የቢሮዎችና የሌሎች አስፈጻሚ አካላት የወል ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ የተቋቋሙ የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት ቢሮዎች እና አስፈጻሚ አካላት በዚህ አዋጅ ውስጥና በሌሎች አዋጆች ለእያንዳንዳቸው የተሰጣቸው ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት የወል ሥልጣንና ተግባር ይኖራቸዋል፡-

1. የክልሉን የአጭር ፤ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ መርሃ-ግብር መሠረት በማድረግ ዕቅድና በጀት በማዘጋጀት ለበላይ አካል በማቅረብ እንዲፀድቅ የማድረግ፤ ሲጸድቅም በሥራ ላይ የማዋል፤
2. የፌዴራል መንግስትና የክልሉ መንግስት ሕጎች፤ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ በሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፤
3. አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ፖሊሲዎችን ፤ ሕጎችንና ደንቦችን በማመንጨት እንዲጸድቁ ለክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ወይም ለበላይ ኃላፊ ማቅረብ ሲፀድቅም በስራ ላይ የማዋል፤

www.chilot.me

4. እያንዳንዱ ቢሮ ወይም አስፈጻሚ አካል ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ወይም ለቀርብ ተጠሪ ቢሮ የመሥሪያ ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴ በየሦስት ወሩ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ወቅት ዘገባ ያቀርባል፡፡

## 9. የቢሮና የሌሎች አስፈፃሚ አካላት ኃላፊዎች የወል ሥልጣንና ተግባር

የቢሮ ወይም የአስፈጻሚ አካላት ኃላፊዎች በዚህ አዋጅ እና በሌሎች አዋጆች ለቢሮው ወይም ለመሥሪያ ቤቱ ከተሰጠው ስልጣንና ተግባር በተጨማሪ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖራቸዋል፡-

1. ቢሮዎቻቸውን ወይም መሥሪያ ቤቶቻቸውን በበላይነት ይመራሉ ፤ይወክላሉ፤
2. ለቢሮዎቻቸው ወይም ለመ/ቤቶቻቸው የተፈቀደውን በጀት በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት ያስተዳድራሉ፤
3. በዚህ አዋጅ እና በሌሎች ሕጎች ለቢሮው ወይም ለመ/ቱ የተሰጠውን ስልጣንና ኃላፊነት ያከናውናሉ፤
4. ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሥራ ቅልጥፍና እና ውጤታማነት አስፈላጊ በሆነ መጠን ለበታች ኃላፊዎች መስጠት ይችላሉ፡፡

## 10. የአስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት

1. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለአቅም ግንባታ ቢሮ ይሆናል ፡-
   ሀ/ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን እና
   ለ/ የሥራ አመራር ኢንስቲቲዩት፡፡
2. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለባህል ቱሪዝምና ማስተወቂያ ቢሮ ይሆናል፡-
   ሀ/ የማህበራት ማደራጃ፣ ሕዝብ አደረጃጀት፣ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት እና
   ለ/ የወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት፡፡
3. የሚከተለው አስፈጻሚ አካል ተጠሪነት ለግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ይሆናል፡፡
   ሀ/ የአደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ጽህፈት ቤት፡፡
4. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለፍትህና ፀጥታ ጉዳይ ቢሮ ይሆናል ፡-
   ሀ/ የሚሊሺያ ጉዳይ ጽ/ቤት ፤
   ለ/ የፖሊስ ኮሚሽን እና
   ሐ/ የማረሚያ ኮሚሽን፡፡
5. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለንግድ ኢንዱስትሪ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ይሆናል፡-
   ሀ/ የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ሥራዎች ማስፋፊያ ጽ/ቤት እና
   ለ/ የኢንቨስትመንት ጽህፈት ቤት፡፡
6. የሚከተለው አስፈጻሚ አካል ተጠሪነት ለጤና ጥበቃ ቢሮ ይሆናል፡-
   ሀ/ የኤች አይ ቪ /ኤድስ/ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬተሪያት ጽ/ቤት፡፡
7. የሚከተለው አስፈጻሚ አካል ተጠሪነት ለሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ይሆናል፡-
   ሀ/ የመንገድ ሥራ ባለሥልጣን፡፡
8. የሚከተለው አስፈጻሚ አካል ተጠሪነት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ይሆናል ፡-
   ሀ/ የገቢዎች ባለሥልጣን፡፡
9. በዚህ አዋጅ በግልጽ ያልተመለከቱት ሌሎች መሥሪያ ቤቶች በሙሉ ተጠሪነት ለክልሉ ፕሬዝዳንትና /ወይም/ ለመስተዳድር ምክር ቤት ወይም በማቋቋሚያ አዋጆቻቸው ለተገለጹት አካላት ሆኖ አደረጃጀትና ዘላቂ ተጠሪነታቸው በመስተዳድር ምክር ቤት የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 11. ስለ ምክትል ቢሮ ኃላፊ

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ከንዑስ አንቀጽ /1/ እስከ /8/ የተመለከቱት ቢሮዎች ምክትል ኃላፊ ይኖራቿዋል፡፡
2. የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ምክትል ሥራ አስኪያጅ በሐረር ከተማ አዋጅ ቁጥር 58/1998 አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ /4/ ከ/ሀ/ እስከ /ሐ/ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

## 12. የምክትል ቢሮ ኃላፊዎች የወል ሥልጣንና ተግባር

ምክትል ቢሮ ኃላፊው ተጠሪነቱ ለቢሮ ኃላፊው ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ቢሮ ኃላፊው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤
2. በመደበኛ ሁኔታ በመዋቅራዊ የስራ ዝርዝር በተመለከተው መሠረት የኃላፊው የቅርብ ረዳት ሆኖ ይሰራል፤
3. ከኃላፊው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የቢሮዎችና የሌሎች መስሪያ ቤቶች ሥልጣንና ተግባር

## 13. የትምህርት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ላይ ለቢሮው የተሰጡት ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቁ ሆኖ ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የሐረሪ ሕ/ክ/ መንግስት የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ለማሻሻልና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/1997 አንቀጽ 8 ከንዑስ አንቀጽ /1/ እስከ ንዑስ አንቀጽ /10/ እና በሌሎች ሕጎች ለትምህርትና አቅም ግንባታ ቢሮ ትምህርትን በሚመለከት የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

2. የሐረሪ ሕ/ክ/ መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1988 አንቀጽ 14 እና በሌሎች ህጎች ትምህርትን በሚመለከት የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤
3. ሌሎች በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ትምህርትን ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚያስፈልጉ ተግባራትን ያከናውናል።

## 14. የአቅም ግንባታ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ላይ ለቢሮው የተሰጡት ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፡-

1. የሐረሪ ሕ/ክ/ መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን አደ ረጃጀት ለማሻሻልና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/1997 አንቀጽ 8 ከንዑስ አንቀጽ /11/ እስከ ንዑስ አንቀጽ /17/ እና በሌሎች ሕጎች አቅም ግንባታን በሚመለከት ለትምህርትና አቅም ግንባታ ቢሮ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ /1/ የተ መለከቱትን አስፈጻሚ አካላት በበላይነት ይመራል ያስተባብራል፤
3. ሌሎች በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን አቅም ግንባታን ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚያስፈልጉ ተግባራትን ያከናውናል።

## 15. የግብርናና የገጠር ልማት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ላይ ለቢሮው የተሰጡት ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የሐረሪ ሕ/ክ/መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻልና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/1997 አንቀጽ 10 ከንዑስ አንቀጽ/1/ እስከ ንዑስ አንቀጽ /6/፣ ከንዑስ አንቀጽ/8/ እስከ ንዑስ አንቀጽ /43/ ፣ ከንዑስ አንቀጽ/48/ እስከ ንዑስ አንቀጽ /50/፣ እንዲሁም ከንዑስ አንቀጽ/61/ እስከ ንዑስ አንቀጽ /71/ እና በሌሎች ህጎች የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ /3/ የተመለከተ ውን አስፈጻሚ አካል በበላይነት ይመራል ያስተባብራል፤
3. ሌሎች በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

## 16. የፍትህና ፀጥታ ጉዳይ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ላይ ለቢሮው የተሰጡት ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የሐረሪ ሕ/ክ/ መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻልና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/1997 አንቀጽ 11 እና በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ /4/ የተመለከቱትን አስፈጻሚ አካላት በበላይነት ይመራል ያስተባብራል፤
3. ሌሎች በክልል መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን የፍትህና አስተዳደር ሥራዎችን ለማጠናከር የሚረዱ ተግባራትን ያከናውናል።

## 17. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ላይ ለቢሮው የተሰጡት ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የሐረሪ ሕ/ክ/ መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻልና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/1997 አንቀጽ 13 እና በሌሎች ህጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ /8/ የተመለከተ ውን አስፈጻሚ አካል በበላይነት ይመራል ያስተ ባብራል፤
3. ሌሎች በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

## 18. የጤና ጥበቃ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ላይ ለቢሮው የተሰጡት ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የሐረሪ ሕ/ክ/ መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻልና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/1997 አንቀጽ 14 እና በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ /6/ የተመለከተ ውን አስፈጻሚ አካል በበላይነት ይመራል ያስተባብራል፤
3. ሌሎች በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፤

www.chilot.me

**19. የባህል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ላይ ለቢሮው የተሰጡት ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቁ ሆኖ ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የሐረሪ ሕ/ክ/ መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻልና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/1997 አንቀጽ 9 እና በሌሎች ሕጎች ባህልን በተመለከተ ለሕዝብ አደረጃጀት ባህልና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤
2. የሐረሪ ሕ/ክ/ መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻልና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/1997 አንቀጽ 15 እና በሌሎች ህጎች ማስታወቂያና ህዝብ ግንኙነትን በተመለከተ ለማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት ቢሮ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤
3. የሐረሪ ሕ/ክ/ መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻልና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/1997 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (1)/ሀ/ እና በሌሎች ህጎች ቱሪዝምን በተመለከተ ለ ንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤
4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ /2/ የተመለከቱትን አስፈጻሚ አካላት በበላይነት ይመራል ያስተባብራል፤
5. ሌሎች በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል፡፡

**20. የንግድ ኢንዱስትሪ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ላይ ለቢሮው የተሰጡት ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቁ ሆኖ ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የሐረሪ ሕ/ክ/መንግስት የአስፈፃሚ አካላትን ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1988 በአንቀጽ 9 ከንዑስ አንቀጽ /1/ እስከ ንዑስ አንቀጽ /10/ ፣ እንዲሁም ከንዑስ አንቀጽ /12/ እስከ ንዑስ አንቀጽ /15/፣ እና በሌሎች ሕጎች ለሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የተሰጡት ሥልጣናንና ተግባራት ይኖሩታል፤
2. የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻልና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/1997 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (1) /ሐ/ እና በሌሎች ህጎች የማዕድንና ኢነርጂን በተመለከተ ለንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 5 የተመለከቱትን አስፈጻሚ አካላት በበላይነት ይመራል ፣ያስተባብራል፤
4. ሌሎች በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**21. የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሥልጣንና ተግባር**

ማዘጋጃ ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የሐረር ከተማ አዋጅ ቁጥር 58/1998 እና በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤
2. የሐረሪ ሕ/ክ/ መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻልና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/1997 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (1) /ሀ/፣ በንዑስ አንቀጽ (3) /ሀ/ እና /ሐ/ እና በሌሎች ህጎች ትራንስፖርትን ተመለከተ ለንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-
   ሀ/ በኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ቁጥጥር ሥር የነበሩትን ቤቶች የማከራየት፣ ኪራዩንም በጊዜ የመሰብሰብ፣ ቤቶቹንም የመጠበቅ፣የማደስና አስፈላጊ ሲሆንም ፈርሰው በሌላ እንዲተኩ የማድረግ፤
   ለ/ ትርፍ ቤት ተወርሶባቸው አበል ለሚገባቸው በአዋጅ ቁጥር 47/1997 መሠረት የተወሰነውን አበል መክፈል፤
   ሐ/ አከራይ የሚፈጽመውን የህግ ግዴታ ሁሉ የመፈጸም፤
   መ/ የቤት ኪራይ መጠን እንደ ደረጃው እንዲወሰን ጥናት የማድረግና ለክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ለውሳኔ ማቅረብ፤
   ሠ/ በክልሉ ውስጥ ያለውን የመኖሪያ ቤት ችግር ለማቃለል አዳዲስ ቤቶችን እንደ አስፈላጊነቱ ማሰራት፣ በተመጣጣኝ ዋጋ ማከራየት፤
   ረ/ ትርፋማ ያልሆኑ ቤቶችን የክልሉ መንግስት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መሸጥ መለወጥ ወይም ፈርሶ በሌላ እንዲተካ ማድረግ፤
   ሰ/ ኪራይ ቤቶች አስተዳደርን በተመለከተ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡
4. የውልና ማስረጃ ምዝገባ ሥራን ያከናውናል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ ለምዝገባ ተግባራት የአገልግሎት ክፍያን ይቀበላል፤
5. የሐረሪ ህ/ክ/ መንግስት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/88 አንቀጽ 12(7) ላይ የውልና ማስረጃ ምዝገባን በተመለከተ የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት እና በሌሎች ህጎች የሚሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከተው ቢኖርም ስለ አወቃቀር አደረጃጀትና አመዘጋገብ ዝርዝር ሁኔታን በተመለከተ ወደፊት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል።
7. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 7 የተመለከተ ውን የአስፈፃሚ አካል በበላይነት ይመራል፣ ያስተ ባብራል፤
8. ሌሎች በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤትን በተመለከተ የሚሰጡትን ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

## 22. የወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ላይ ለጽ/ቤቱ የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቀ ሆኖ ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. ወጣቶች ለክልሉ ልማትና ዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የድርሻቸውን ለመወጣት እንዲችሉ በአካልና በአእምሮ የዳበሩ ኃላፊነት የሚሠማቸው በስነምግባር የታነፁ ወጣቶች ለማፍራት የሚቻልበትን ስልት ይቀይሳል፣ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
2. ወጣቶች ጤንነታቸውን ጠብቀው ከጎጂ ልምዶችና ከወንጀል ድርጊቶች ርቀው አምራች ዜጎች በመሆን እራሳቸውን ችለው ለሕብረተሰቡ ልማት ጠቃሚ ሊሆኑ የሚያስችላቸውን የሙያ፣ የቴክኒክ ፣ የምክርና ሌሎች አገልግሎቶች ያገኙ ዘንድ እንዲመቻች ያደራጃል እንዲደራጁም ያግዛል፤
3. ወጣቱ ትውልድ የስራ ፍቅርና የአገር መውደድ ስሜት ኖሮት ለዚህም እራሱን እንዲያዘጋጅና ሁሉ-ገብ ስብዕናውን ለማጠናከር የሚረዳ የስነ-ዜጋ ትምህርት መሰጠቱን ያረጋግጣል፤
4. ወጣቱ የፈጠራና የስነ-ጥበብ ችሎታ እየዳበረ እንዲሄድ ያበረታታል፣ የተለያዩ ውድድሮችእንዲዘጋጁና ወጣቶች እንዲሳተፉበትም ድጋፍ፣ ያደርጋል የፈጠራ ውጤት ባለቤትነታቸውም መከበሩንም ያረጋግጣል፤
5. በክልሉ ውስጥ ለሚቋቋሙ የስፖርት ማህበራት ፈቃድ ይሰጣል፣ፕሮግራሞቻቸውንም ያስተባብራል፣ ይቆጣጠ ራል፤
6. በክልሉ ውስጥ በክልል ደረጃ ውድድሮችን ያዘጋጃል እንዲዘጋጁም ፈቃድ ይሰጣል፤
7. በክልል ደረጃ የሚዘጋጁትን የስፖርት ውድድሮች በሚመለከት በስፖርት ማህበሮች መካከል የሚነሳውን ክርክር ይዳኛል፤
8. በክልሉ ውስጥ ባሕላዊ ስፖርቶች የበለጠ እንዲታወቁ፣ እንዲሻሻሉና እንዲያድጉ ያደርጋል፤
9. በክልሉ ውስጥ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ያዘጋጃል ፣ እንዲዘጋጁም ያበረታታል፤
10. የክልሉ ስፖርት ምክር ቤቶችንና የባህል መማክርት ጉባዔን ያቋቁማል፤
11. የክልሉ ስፖርት ማህበራት የሚያገኙት ገቢ ለዓላማቸው ማስፈጸሚያ ብቻ መዋሉን በማረጋገጥ ሂሳባቸውን ይመረምራል፤
12. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ትጥቅና መሣሪያዎች እንዲሁም የስነ-ጥበብ መሣሪያ ዎች የሚገኙበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤
13. ከክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ ጋር በመተባበር ስፖርታዊ ሕክምና ያዘጋጃል፤
14. ውል ይዋዋላል፤ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ይገዛል ይሸጣል ባለቤት ይሆናል፤ይከራያል ያከራያል፤ እርዳታ/ስጦታ ይቀበላል እና የመሳሰሉት... ህጋዊ ሰውነት ኖሮት በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፤
15. ሌሎች አግባብነት ካላቸው የበላይ አካላት የሚሰጡ ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

## 23. ማህበራት ማደራጃ ፤ ሕዝብ አደረጃጀት ፤ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ላይ ለጽ/ቤቱ የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቀ ሆኖ ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በሙያ በዕድሜና በሌሎች ሲቪክ ማኅበራት ተደራጅተው መብትና ጥቅማቸውን በማስጠበቅ ለሀገሪቱ ልማትና እድገት አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
2. ሴቶች ለመብታቸው እንዲታገሉና የጾታ እኩልነት እንዲረጋገጥ ያደራጃል፤
3. የሕዝቡን የልማት አደረጃጀት ይከታተላል፣ በተለይ አርሶ አደሩ በአደረጃጀቱ ተጠቃሚ መሆኑን ያረጋግጣል፤
4. የልማት ቡድኖች ያልተደራጁበትና ያልተጠናከሩትን አካባቢዎች በመለየት ሕዝቡ በስፋት እንዲደራጅ ያበረታታል፣ያደራጃል፣ ያጠናክራል፤
5. ሕዝቡን በማደራጀት ሊሳተፍባቸው የሚገባ የልማት መስኮችንና ሕዝቡን ለማደራጀት መከተል ስለሚገባው ስልቶች ያጠናል ተግባራዊ ያደርጋል፤
6. የሕዝብ አደረጃጀትና ተሳትፎን የሚመለከቱ መረጃ ዎችንና እስታቲስቲክስ ያሰባስባል፣ ያጠናክራል፣ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤
7. የሕዝቡን አደረጃጀትና ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ለማጎልበት የሚረዱ ጽሁፎችን በማዘጋጀት ያሰራጫል፤

8. የተደራጁ ሕዝባዊ ማህበራት እንዲጠናከሩና እራሳቸውን እንዲችሉ ስልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
9. በክልሉ የተደራጁ የሙያ፣ የልማትና ሕዝባዊ ማህበራት ያሉባቸውን ችግሮች ያጠናል ፤ ችግሮቹ መፍትሄ የሚያገኙበትን መንገድ ይቀይሳል፤
10. ሕዝባዊና የሙያ ማህበራት በልማት ስራዎች የሚሰማሩበትን ቦታ ያጠናል የልማት ሥራዎች ላይ እንዲሠማሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
11. በክልሉ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሕዝባዊ ማኀበራት ጋር በቅንጅት መስራት እንዲችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
12. የሀገሪቱ የሠራተኛ ማህበራት ጉዳይ ፖሊሲዎች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
13. የሠራተኞችን ጉዳይ በሚመለከት የወጡ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፤
14. የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነትን ለመጠበቅ የወጡ የሥራ ሁኔታ ደረጃዎችና መከላከያ ዘዴዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤
15. በክልሉ ደረጃ የሚቋቋሙትን ሠራተኛና አሠሪ ማህበራትን ይመዘግባል አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤
16. የህብረት ስምምነት ድርድሮችና የስራ ክርክሮች በሕግ የተዘጋጀውን ሥርዓት ተከትለው በተቀላጠፈ ሁኔታ ፍፃሜ እንዲያገኙ አስፈላጊውንጥረት ያደርጋሉ፣ እንዲሁም የህብረት ስምምነቶችን ይመዘግባል፤
17. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ስለተሰማራ፣ የሰው ኃይል፣ ስለሙያ አመዳደብና አደጋ ሊመጣ የሚችልበትን ጥናት ያደርጋል፤
18. በክልሉ ውስጥ ስራ ፈላጊዎችንና ክፍት የስራ መደቦች እንዲመዘገቡ እና ሥራና ሠራተኛ እንዲገናኙ የሚያስችል እርምጃ ይወስዳል፤
19. ስለክልሉ የሰው ኃይልና የሥራ ስምሪት ስለ ሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት እንዲሁም ስለ አሠሪና ሠራተኛን በሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች ላይ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናክራል፣እንዲሁም አስተያየቱን በማከል ለሚመለከቱት አካሎች ያስተላልፋል፤
20. የክልሉ ሴቶች በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በባህል ያላቸውን ተሳትፎ በማጎልበት በፌደራል መንግስት የወጡ ፖሊሲዎች በክልሉ መንግስትና በሕብረተሰቡ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
21. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ህፃናትና ወጣቶች መልካም አስተዳደግ እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያስችሉ ዘዴዎች በክልሉ እንዲዘረጉ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል፣ እንዲሁም የሕፃናትን መብት በተ መለከተ የዓለም አቀፍ ሰነዶች እና በአገር አቀፍ የወጡ ሕጎችና ደንቦች መከበራቸውን ይከታተላል፤
22. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የሚገኙ አረጋዊያንና የአካል ጉዳተኞችን ለመርዳትና መልሶ ለማቋቋም የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ሲፈቅድም በሥራ ላይ ያውላል፤
23. የህበረት ሥራ ማህበራት ማደራጃን በተመለከተ በክልሉ መንግስት የህበረት ሥራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽህፈት ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 35/1996 እና በሌሎች ህጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤
24. ውል ይዋዋላል፣ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ይገዛል ይሸጣል ባለቤት ይሆናል፣ ይከራያል ያከራያል፣ እርዳታ/ስጦታ ይቀበላል እና የመሳሰሉት... ህጋዊ ሰውነት ኖሮት በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፤
25. ሌሎች አግባብነት ካላቸው የበላይ አካላት የሚሰጡትን ተዛማጅ ተግባራትን ያከነውናል።

## 24. <u>የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ሥራዎች ማስፋፊያ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ላይ ለጽ/ቤቱ የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቀ ሆኖ ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በክልሉ ውስጥ አነስተኛ የንግድ ተቋማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
2. በክልሉ ውስጥ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራ ማህበራት ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል በተለይም የማምረቻና የመሸጫ ቦታዎች፣ የፋይናንስና የብድር አገልግሎቶች ፣ የጥሬ እቃ እና የማምረቻ መሣሪያዎች እንዲሁም የመሠረተ ልማት አውታሮች የሚገኙበትን ሁኔታ ዎች ያመቻቻል፤
3. ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች ማሠልጠኛ ማዕከል እንዲቋቋም ያመቻቻል፣ በክልሉ ውስጥ በጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች ለተሰማሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ስልጠናዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ያስተባብራል፤
4. በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን ሥራ-አጥ የሆኑ ወጣቶችና ሴቶች አምራች ዜጋ ሊያደርጉ የሚችሉ ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራ ፕሮጀክቶች እንዲጠኑ ፣ያደርጋል፣ተግባራዊ መሆናቸውንና ውጤት ማስገኘታቸውን ይከታተላል፤
5. መረጃና የምክር አገልግሎት ለተጠቃሚዎች የሚሰጥበት ስርዓት ይዘረጋል፤
6. የአገሪቱን ንግድ፣ የንግድና ኢንዱስትሪ መሠረት በማድረግ በክልሉ ንግድ ኢንዱስትሪና እደ-ጥበባት እንዲስፋፉ ያበረታታል እንዲሁም የቴክኒክ የምክርና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

7. የክልሉን የንግድ እንቅስቃሴ በሀገሪቱ ሕግና ፖሊሲ መሠረት መካሄዱን ይቆጣጠራል፣ እንዲሁም ሕጋዊ ያልሆኑ የማምረት አገልግሎት የመስጠትና የንግድ ልውውጥ ሥራ እንዳይካሄድ ያደርጋል ፤
8. በኢቨስትመንት ፖሊሲና ሕግ መሠረት ሲጠኑና በሥራ ላይ ሲውሉ የሚገባቸውን የኢንዱስትሪ ፕሮጀክት ሐሳቦችን ለሚመለከተው ለፌደራል መንግስት መ/ቤት ያስተላልፋል ፣ እንዲሁም ሌሎች የኢንዱስትሪ ፕሮጀክት ሀሳቦች በክልል ደረጀ እንዲጠኑና በስራ ላይ እንዲውሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
9. በክልሉ ውስጥ በመሠራታዊ የንግድ እቃዎችና አገልግሎቶች ስርጭት አግባብነት ባለው አካል የተወሰኑ የዋጋ ተመንና የጥራት ደረጃ መከበሩን ይቆጣጠራል፤
10. የክልሉ የእንዱስትሪ የእርሻና ሌሎች የምርት ውጤቶችን ለማስተዋወቅ ኤግዚቢሽን እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ በሌሎች ክልሎች የሚዘጋጀውን ተመሳሳይ ኤግዚቢሽኖች ክልሉ ከሌሎች ክልሎች ጋር የሚያደርገው የንግድ ልውውጥ የሚስፋፋበትና የሚዳብርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
11. በክልሉ ውስጥ በንግድና ኢንዱስትሪ ሥራ ለሚሰማሩ ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ እንዲሁም ተገቢውን የአገልግሎት ገቢ ይሰበስባል፤
12. ለዕደ-ጥበባት፣ለጎጆ ኢንዱስትሪዎችና ለአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች የኤክስቴንሽን አገልግሎት ይሰጣል፣ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ የእደ-ጥበባትና ጎጆ ኢንደስትሪዎች የሙያ ማሻሻያ ማዕከሎች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፤
13. የክልሉን የንግድ መዝገብ ያቋቁማል ፣ ያስተዳድራል፣
14. የአነስተኛ ኢንዱስትሪ ፣ የእደ-ጥበባትና ሽማቾች፤ ሕብረት ሥራ ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤
15. በክልሉ የንግድ ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙ ያበረታታል ፣ድጋፍ ይሰጣል፤
16. ስለ ክልሉ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴና የኢንዱስትሪ ልማት መረጃዎችን ያሰባስባል ፣ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፤
17. ውል ይዋዋላል፤ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ይገዛል ይሸጣል ባለቤት ይሆናል፤ ይከራያል ያከራያል፤ እርዳታ/ስጦታ ይቀበላል እና የመሳሰሉት... ህጋዊ ሰውነት ኖሮት በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፤
18. ሌሎች አግባብነት ካላቸው የበላይ አካላት የሚሰጡትን ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

## 25. የገቢዎች ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ላይ ለባለስልጣኑ የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. በህግ ተለይተው በክልሉ መንግስት እንዲሰበሰቡ የተመደቡ የግብር /የታክስ ገቢዎችን ይወስናል፣ ይሰባስባል ይፈጽማል፤
2. ለግብር /ታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ በክልሉ ለሚገኙ ቅርንጫፍ የግብር/ታክስ ሰብሳቢ አካላት ያሰራጫል፤
3. የመረጃ አያያዙን በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ያደርጋል፤
4. የግብር /ታክስ ህጎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ በማናቸውም ሰው እጅ የሚገኙ ሰነዶችን ይመረምራል፤
5. የግብር /ታክስ አወሳሰን ፣አሰባሰብ ሂሳብ አያያዝ እና ሌሎች ተጓዳኝ ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችሉ የአሰራር ዘዴዎችንና ሥልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊነታቸውንም ያረጋግጣል፤
6. የግብር ከፋዮች መብትና ግዴታቸውን እንዲጠቁ ለማድረግ የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ያደርጋል፤
7. የግብር /የታክስ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን አፈጻጸም ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶችን በማካሄድ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፤
8. ለግብር /ለታክስ አስተዳደር ብቃት ያላቸው ባለሙያዎችን ለማፍራት የሚያስችለውን ሥልጠናና የሙያ ማሻሻያ ዘዴዎችንና ሌሎች ስልቶችን ይዘረጋል፤
9. ውል ይዋዋላል፣ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ይገዛል፣ ይሸጣል፣ ባለቤት ይሆናል፣ ይከራያል ያከራያል እርዳታ/ስጦታ ይቀበላል እና የመሳሰሉት... ህጋዊ ሰውነት ኖሮት በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፤
10. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፤
11. ሌሎች አግባብነት ካላቸው የበላይ አካላት የሚሰጡ ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

## 26. ፖሊስ ኮሚሽን

ለፖሊስ ኮሚሽን በሌሎች ህጎች የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ:-

1. ለሐረሪ ሕ/ክ/ መንግስት የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 58/1998 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2/III እና በሌሎች ህጎች የእሳት አደጋ አገልገሎትን በተመለከተ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለፖሊስ ኮሚሽን ተሰጥቷል፤

2. የሐረሪ ሕ/ክ/ መንግስት አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻልና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/1997 እና በሌሎች ህጎች ለሕዝብ አደረጃጀት ባህልና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኪነትን በተመለከተ ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለፖሊስ ኮሚሽን ተሰጥቷል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 27. ስለ ሌሎች አስፈጻሚ አካላት

በዚህ አዋጅ ውስጥ ሥልጣንና ተግባራቸው ያልተገለጸ የክልሉ አስፈጻሚ አካላትና ሌሎች ተቋማት ሥልጣንና ተግባራቸው በተቋቋሙበት ሕግ እና በአዋጅ ቁጥር 47/1997 በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡

### 28. በየደረጃው ስለሚቋቋሙ አስፈጻሚ አካላት

1. በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ቢሮዎችና ሌሎች መሥሪያ ቤቶች እንደሥራቸው ዓይነትና ስፋት በቀበሌው ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ቀበሌዎችን በማማከል ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖራቸው ይችላል፤
2. በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በዋናነት በክልል ደረጃ ከዋናው መሥሪያ ቤት የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ማዋል ይሆናል፤
3. ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች የተሰጣቸውን ሥልጣንና ተግባር አፈጻጸም በተመለከተ ተጠሪነታቸው በየደረጃው ለሚገኝ አስተዳደር ምክር ቤትና ለበላይ መሥሪያ ቤት ነው፡፡

### 29. የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ተግባርና ኃላፊነታቸው እንዲቀጥል የተደረጉ አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን የሐረሪ ሕ/ክ/ መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣው ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1988 እንዲሁም የሐረሪ ሕ/ክ/ መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻልና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 47/1997 እና ሌሎች የክልሉ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጆች ድንጋጌዎች ይህ አዋጅ በሚመለከታቸው ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡
2. የሐረሪ ሕ/ክ/ መንግስት የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 16/1991 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
3. የሐረሪ ሕ/ክ/ መንግስት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ /7/ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
4. ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

### 30. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

1. ከዚህ አዋጅ በፊት ለየብቻ የነበሩና በዚህ አዋጅ እንዲዋሀዱ የተደረጉ ቢሮዎች ወይም መሥሪያ ቤቶች መብትና ግዴታቸውም በዚህ አዋጅ መሠረት በእነርሱ ውህደት ወደ ተመሰረተው አዲስ መሥሪያ ቤ ት ተላልፏል፡፡
2. ቀድሞ በአንድ ላይ የነበሩና በዚህ አዋጅ እንዲለያዩ የተደረጉ የአስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች በዚህ አዋጅ ከተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መለያየት የሚቻል ከሆነ በዚህ አዋጅ ሥልጣኑና ተግባራቸው ወደ ተላለፈበት መሥሪያ ቤት ተላልፏል፡፡
3. በዚህ አዋጅ ከመለየታቸው በፊት የጋራ መብትና ግዴታ እያላቸው በመለያየታቸው ምክንያት መብትና ግዴታን ለይቶ ወደ አንዱ አካል ማስተላለፍ አስቸጋሪ ሆኖ ስገኝ ጉዳዩ ለክልል መስተዳድር ምክር ቤት ቀርቦ የሚወሰን ይሆናል፡፡
4. በአዋጅ ቁጥር 58/1998 እና በሌሎች ህጎች መሠረት እሳት አደጋ አገልግሎትን በተመለከተ የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት የነበሩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለፖሊስ ኮሚሽን ተላልፏል፡፡
5. በአዋጅ ቁጥር 47/1997 እና በሌሎች ህጎች መሠረት ኪነትን በተመለከተ የህዝብ አደረጃጀት ባህልና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የነበሩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለፖሊስ ኮሚሽን ተላልፏል፡፡
6. በአዋጅ ቁጥር 16/1991 ተቋቁሞ የነበረው የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ተላልፏል፡፡
7. የሐረሪ ሕ/ክ/ መንግስት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባዔን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 3/1988 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ /7/ እና በሌሎች ህጎች ውልና ማስረጃ ምዝገባ ሥራን በተመለከተ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የነበሩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ተላልፏል፡፡

www.chilot.me

8. የሐረሪ ሕ/ክ/ መንግስት አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻልና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/1997 እና በሌሎች ሕጎች ግብር/ታክስ አስተዳደርን በተመለከተ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ወይም የሌሎች አካላት የነበሩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለገቢዎች ባለሥልጣን ተላልፏል፡፡

## 31. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. በዚህ አዋጅ መሠረት አስፈላጊ መዋቅር ተዘርግቶ ሥራ ላይ እስከሚውል ድረስ በሥራ ላይ ያሉ ደንቦችና መመሪያዎች ለስድስት ወራት ያህል ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል፡፡
2. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተጀመሩት ሥራዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚመለከተው አካል እንደተ ጀመሩ ተቀጥረው አፈጻጸማቸው ይቀጥላል፡፡

## 32. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. በዚህ አዋጅ የተቋቋሙትን ቢሮዎችና መሥሪያ ቤቶች ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ የሚያውሉ ቦርዶች፣ ኤጀንሲዎች፣ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቶችና ሌሎች ተቋማት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አጥንቶ በደንብ እንዲያቋቁም በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፤
2. ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ወይም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፤
3. በዚህ አዋጅ የተቋቋመ ማንኛውም ቢሮ ወይም ሌላ መስሪያ ቤት በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ለማዋል የሥራ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 33. የመተባበር ግዴታ

ጉዳዩ የሚመለከተው ማንኛውም አካል በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በስራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት ፡፡

## 34. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከነሐሴ 17 ቀን 1999 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሐረር ነሐሴ 17 ቀን 1999 ዓ/ም

ሙራድ አብዱልሐዲ

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐ ረ ር ነ ጋ ሪ ጋ ዜ ጣ
# HARAR NEGARI GAZETA
OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

12ኛ አመት ቁጥር 4
12th year No 4

ሐረር ነሐሴ 17 ቀን 1999
Harar, Aug. 23 / 2007

ያንዱ ዋጋ ብር 4.20
Unit Price Bir. 4.20

በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት
ጠባቂነት የወጣ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር 952
P. o . Box 952

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 71/1999
የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የሥነ-ምግባርና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ........................................ገጽ 544

## አዋጅ ቁጥር 71/1999

## የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የሥነ-ምግባርና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት እና የክልሉ ነዋሪዎች ሙስና እና ብልሹ አሰራር የክልሉን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እድገት የሚገታ ተግባር መሆኑን የተገነዘቡ በመሆናቸው፤

በክልሉ የተያዘውን የእድገት ጎዳና እና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ለማፋጠንና ቀጣይነት ያለው እንዲሆን ሙስናን እና ብልሹ አሠራርን በቁጥጥር ሥር ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ሙስናንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ይቻል ዘንድ ይህንኑ ለመመርመር፣ አጣርቶ ለፍርድ ለማቅረብ፣ ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲሁም በህብረተሰቡ ውስጥ መልካም ስነ-ምግባር ይስፋፋ ዘንድ እና ብልሹ አሰራርን መዋጋት የሚችል ነፃና እራሱን የቻለ ክልላዊ ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

ለሐረሪ ህዝብ ክልል ም/ቤት በተሻሻለው ህገ-መንግስት አንቀጽ 51(2)(ሀ) ላይ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠ ቅ ላ ላ

1. **አጭር ርዕስ**
   ይህ አዋጅ ‹‹የሥነ-ምግባር እና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 71/1999›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**
   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ :-
   1. “ኮሚሽን” ማለት የክልሉ የሥነ ምግባር እና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን ነው፡፡
   2. “መንግስት” ማለት የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት ነው፡፡
   3. “የመንግስት መ/ቤት” ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደር እና የክልሉ መንግስት ስራዎች የሚከናወኑበት ማናቸውም መስሪያ ቤት ነው፡፡
   4. “የመንግስት የልማት ድርጅት” ማለት የመንግስት ባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት ማናቸውም የክልሉ መንግስት የልማት ድርጅት ወይም የአክሲዮን ኩባንያ ነው፡፡

www.chilot.me

5. "የመንግስት ባለስልጣን" ማለት በክልሉ ምክር ቤት ወይም በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ወይም በርዕሰ መስተዳድሩ ለመንግስት መ/ቤቶች የተሾሙ፣ ወይም የተመረጡ ከመምሪያ ኃላፊ ደረጃ በላይ የሆኑ የክልሉ መንግስት ባለሥልጣኖች፣ የቢሮ ኃላፊዎች፣ ምክትል ቢሮ ኃላፊዎች፣ ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣ ኮሚሽነሮች፣ ምክትል ኮሚሽነሮች፣ ረዳት ኮሚሽነሮች፣ ሥራ አስኪያጆች፣ ምክትል ሥራ አስኪያጆች፣ ቀበሌ አስተዳዳሪዎች እና አስተባባሪዎችን ያጠቃልላል። እንዲሁም ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሌሎች የክልሉ ባለሥልጣኖችን ይጨምራል።
6. "የመንግስት ሰራተኛ" ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ ከተጠቀሱት መ/ቤቶች ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ነው።
7. "የሥነ-ምግባር አውታሮች" ማለት በመንግስት አስተዳደር ውስጥ ምግባረ ብልሹ ባህርያትን በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ እና ሙያዊ ብቃትን እና መልካም ሥነ-ምግባር ለማበረታታት የሚያገለግሉ ዘዴዎች፣ አካላት፣ ስርአቶች ወይም አስፈላጊ ሁኔታዎች እና የመሳሰሉት ናቸው።
8. "ከባድ የሥነ-ምግባር መጣስ" ማላት አግባብ ባለው የሥነ-ምግባር ደንብ መሰረት ከስራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት ነው።
9. "ከባድ የሙስና ወንጀል" ማለት፡-
   ሀ/ ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸው ያመንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ላይ የሚፈጸሙ ከፍተኛ የገንዘብ መጠንን ያካተቱ የሙስና ወንጀሎች ወይም፣
   ለ/ የመንግስት ባለስልጣንን የሚመለከቱ የሙስና ወንጀሎች ወይም፣
   ሐ/ በክልሉ ሉአላዊነት፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፀጥታ እንዲሁም በህብረተሰቡ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ሊያደርሱ የሚችሉ የሙስና ወንጀሎች ናቸው።
10. "የባንክ ሂሳብ" ማለት በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ፣ ወርቅና የመሳሰሉት ውድ እቃዎች እንዲሁም አንድ ደንበኛ ከባንኩ ጋር የሚያደርጋቸውን ማናቸውም ግንኙነቶች/ትራንዛክሽኖች/ የሚያጠቃልል ነው።
11. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

## ክፍል ሁለት
## ስለ ኮሚሽኑ መቋቋም ፣ አላማ እና ሥልጣንና ተግባር

### 3. ስለ መቋቋም

1. የክልሉ የሥነ-ምግባር እና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን /ከዚህ በኃላ ኮሚሽን እየተባለ የሚጠራ/ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት መ/ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል።

### 4. የኮሚሽኑ ዓላማዎች

ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የሥነ-ምግባር እና የጸረ–ሙስና ትምህርቶችን በማስፋፋት የነቃ እና ሙስናን ሊሸከም የማይችል ህብረተሰብ እንዲፈጠር ጥረት ማድረግ፤
2. የሙስና ወንጀልን እና ብልሹ አሰራርን መከላከል ፣ መመርመርና ሙሰኞችን ለፍርድ ማቅረብ፤
3. በክልሉ ውስጥ ሃቀኛና ታማኝ የህዝብ አገልግሎት እንዲሰፍን ጥረት ማድረግ።

### 5. የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር

ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በክልሉ መንግስት መሥሪያ ቤቶች፣ በመንግስት ልማት ድርጅቶች ወይም በክልል በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ ከባድ የሥነ-ምግባር ጉድለት ስለመፈፀሙ ጥቆማ ሲደርሰው ወይም በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው የማጣራት ወይም እንዲጣራ የማድረግና ተገቢውን እርምጃ እንዲወሰድ የመከታተል፤
2. በወንጀል ህግና በሌሎች ህጎች ውስጥ የተመለከቱት የሙስና ወንጀሎች በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ወይም እነዚህ የተካፈሉበት በሆነ ጊዜ በግል ዘርፍ ስለመፈፀማቸው ጥቆማ ሲደርሰው ወይም በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው የመመርመር፣ እንዲመረመር የማድረግ እና ክስ የመመስረት፤
3. የሙስና ወንጀሎችን በመመርመር ሂደት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ- ስርዓት ህግ መሰረት ማናቸውንም ግቢ፣ የስራ ቦታ፣ ተሽከርካሪ ወይም ማናቸውም ሌላ ንብረት እንደአስፈላጊነቱ የመፈተሽ፣ የመበርበር ወይም የመያዝ፤

www.chilot.me

4. በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ስርዓት ህግ መሰረት በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎችን ከ48 ሰዓት ሳልበለጠ ጊዜ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ አስሮ የማቆየት እና በህግ መሰረት በዋስትና የመልቀቅ እና የተጠርጣሪዎችን የጣት አሻራና ፎቶ ግራፍ የመውሰድ፤
5. ለምርመራ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማናቸውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ስርዓት ህግና በሌሎች ህጎች መሰረት አስቀርቦ የመጠየቅ፣ ቃል የመቀበል እና ከማናቸውም ሰው ወይም መሥሪያ ቤት ማስረጃ እንዲቀርብለት የማዘዝ፤
6. ከሙስና ወንጀል ጋር የተያያዘ እና በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ ለመኖሩ በቂ ጥርጣሬ ወይም ማስረጃ ሲኖረው በማናቸውም ባንክ የሚገኝ የተጠርጣሪዎች የባንክ ሂሳብ በኮሚሽኑ ትዕዛዝ መሰረት እንዲመረመር የማድረግና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲከበር የማድረግ፤
7. በክልሉ መንግስት መሥሪያ ቤቶች፣ በልማት ድርጅቶች ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ ለሙስና የተጋለጡ የአሰራር ስርዓቶችን በመመርመር እንዲሻሻሉ በማድረግ ሙስናን የመከላከል፣ በሌሎች ሰዎች ሲጠየቅ ተመሳሳይ ምክርና ድጋፍ የመስጠት፤
8. የመንግስት ባለሥልጣኖችን እና በህግ ሃብታቸውንና የገንዘብ ጥቅማቸውን እንዲያስመዘግቡ ግዴታ ያለባቸውን የመንግስት ሰራተኞች ሀብትና የገንዘብ ጥቅሞች መዝግቦ የመያዝ ወይም ተመዝግበው እንዲያዙ የማድረግ፤
9. ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ በምርመራ ላይ ያሉ ሰዎች ሀብት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዳይንቀሳቀስ የማድረግ፣ በሙስና ወንጀል የተገኘ መሆኑ የተረጋገጠ ማናቸውም ንብረት ወይም ሀብት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲወረስና በሃራጅ ተሸጦ ወይም ሳይሸጥ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግ፤
10. የሥነ-ምግባር ደንቦች እና የፀረ- ሙስና ህጎች መከበራቸውን የመከታተል እና የማረጋገጥ፣ ስለ አፈጻጸማቸው የምክር አገልግሎት የመስጠት፤
11. ሥነ-ምግባርና ሙስናን በተመለከተ ጥናትና ምርምር ማድረግ፣ ተመሳሳይ ስራዎችን የመደገፍና የኮሚሽኑን አላማዎች ለማራመድ የሚረዱ ሪፖርቶችን እና ቴክኒካዊ ጥናቶችን አሳትሞ ለህብረተሰቡ የማሰራጨት፤
12. የሥነ-ምግባር ደንቦች ሲጣሱ የሚወሰዱ እርምጃዎች ከተፈፀሙ ጥፋቶች ጋር የተጣጣሙ ወይም የተመጣጠኑ እንዲሆኑ ሌሎች የስነ-ምግባር አውታሮችን የማስተባበር፤
13. ስለ ሙስና ጎጂነት የህዝቡ ንቃት ህሊና እንዲጎለብት በማስተማር እና መልካም ስነ-ምግባር በህዝቡ አገልግሎት እና በህብረተሰቡ ውስጥ እንዲስፋፋ በማድረግ ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን መዋጋት፤
14. የህግ አውጪና የዳኝነት አካላትን ሳይጨምር ለመንግስት መ/ቤቶችና ለመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚያገለግሉ የሥነ-ምግባር ደንቦች ማዘጋጀት፣ መዘጋጀታቸውን የማረጋገጥና አፈፃጸማቸውን የመከታተል፣ ከህግ አውጪና ከዳኝነት አካላት ጥያቄ ሲቀርብለት በሥነ-ምግባር ደንብ አዘገጃጀት ረገድ ምክር የመስጠት፤
15. ለጠቋሚዎችና ለምስክሮች የአካልና የስራ ዋስትና ጥበቃ የመስጠት፤
16. ሙስናን በመታገልና በመከላከል ረገድ ውጤት ያስገኙ ሰዎችን እና መስሪያ ቤቶችን አወዳድሮ ለሽልማት የሚበቁበትን ሥርዓትና መለኪያ በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ፤
17. ተመሣሣይ አላማዎች ካሏቸው ክልላዊና ሀገራዊ አካላት ጋር ግንኙነት የመፍጠርና ትብብር የማድረግ፤
18. የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋልና በራሱ ስም የመክሰስም ሆነ የመከሰስ፤
19. ከፍ ብሎ ከተዘረዘሩት ኃላፊነቶች መካከል የመመርመርና የመክሰስ ስልጣኑን እንደ አስፈላጊነቱ ለክልሉ ፖሊስ፣ የአቃቢ ህግ አካላት በውክልና የመስጠትና የማሰራት፤
20. በህግ የሚሰጡትንና አላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱትን ሌሎች ተግባራት የማከናወን።

## 6. ስለ ኮሚሽኑ የአሠራር ነፃነት

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም ኮሚሽኑ ሥራውን በማከናወን ረገድ ከማንኛውም ሰው ወይም አካል ጣልቃ ገብነት ወይም አመራር ነፃ ነው።

## 7. የኮሚሽኑ አቋም

1. በፕሬዝዳንቱ አቅራቢነት የሚሾም አንድ ኮሚሽነርና ምክትል ኮሚሽነር እና
2. ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞች ይኖሩታል።

www.chilot.me

## 8. የኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር

1. ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ዋና ስራ አስፈጻሚ በመሆን የኮሚሽኑን ሥራዎች ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፤
2. የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፤
   ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 የተዘረዘሩ የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ) በዚህ አዋጅ በተመለከተው መሰረት እና የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህግ አጠቃላይ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ በሚወጣው የአስተዳደር ደንብ መሰረት የኮሚሽኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል ፣ ያሰናብታል፤
   ሐ) የኮሚሽኑን በዚህ ህግ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህግ አጠቃላይ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ የኮሚሽኑ የአስተዳደር ደንብ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው ያቀርባል። ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤
   መ) የኮሚሽኑ ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም እና የ5 ዓመት በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤
   ሠ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደለት በጀትና ፕሮግራም መሠረት የፋይናስ ህግን ተከትሎ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
   ረ) በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎችን የኮሚሽኑ ሰራተኞች በህግ መሰረት ለመመርመር ወይም ለመክሰስ ወይም ለማሰር እንዲችሉ ሥልጣን ይሰጣል፤
   ሰ) ምርመራው በመከናወን ላይ ላለ ጉዳይ አግባብነት ያለው በሆነ ጊዜ የማንኛውም ሰው የባንክ ሂሳብ እንዲፈተሽ እና አስፈላጊው መረጃ እንዲሰበሰብ ትእዛዝ ለመስጠት ይችላል፤
   ሸ) የኮሚሽኑ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ኮሚሽኑን ይወክላል፤
   ቀ) የኮሚሽኑ ጠቅላላ የአሠራር ሂደት የሥራ ግምገማ ውጤትና አስተያየት አስመልክቶ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ሪፖርት ያቀርባል፤
3. ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለምክትል ኮሚሽነሩ እና ሰራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

## 9. የኮሚሽነሩ የሥራ ዘመንና ከሥራ መነሳት፤

1. የኮሚሽነሩ የሥራ ዘመን ለስድስት ዓመት ይሆናል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሲሆን እንደገና ሊሾም ይችላል።
2. የኮሚሽነሩ የስራ ዘመን ከማለቁ በፊት ከዚህ በታች በተመለከቱት ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር ከስራው አይነሳም፣
   ሀ) አግባብ ባለው የሥነ-ምግባር ደንብ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተላልፎ ሲገኝ፣
   ለ) ጉልህ የሆነ የስራ ችሎታና ቅልጥፍና የሌለው ሲሆን፣
   ሐ) በህመም ምክንያት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን የማይችል ሆኖ ሲገኝ፣
   መ) እራሱ የመልቀቂያ ጥያቄ ሲያቀርብ ነው።

## 10. የምክትል ኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር

1. ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ስራውን ይሰራል፤
2. ምክትል ኮሚሽነሩ ሥር የሚገኙትን ኃላፊዎች ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣ ውሳኔ ይሰጣል።
3. በኮሚሽኑ ስር የተዋቀሩትን አደረጃጀትና የሥራ ክፍሎች በኮሚሽነሩ በሚሰጠው መመሪያ እና በኮሚሽኑ የአሰራር ደንብ መሠረት ይመራል፣ ያስተባብራል።

## 11. የምክትል ኮሚሽነሩ የሥራ ዘመንና ከሥራ መነሳት፤

የምክትል ኮሚሽነሩ የሥራ ዘመንና ከሥራ መነሳት አስመልክቶ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ኮሚሽነሩን አስመልክቶ የተደነገጉት ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## 12. ስለ ኮሚሽኑ ሰራተኞች ቅጥር ሁኔታ

1. የኮሚሽኑ ሠራተኞች የቅጥር፣ አስተዳደርና ስንብት ሁኔታ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እና የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህግ አጠቃላይ መርሆዎች መሰረት በማድረግ በሚወጣው የአስተዳደር ደንብ መሠረት ይሆናል።
2. የኮሚሽኑ አቃቢያነ ህግ የቅጥር፣አስተዳደርና ስንብት ሁኔታ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች አጠቃላይ መርሆዎች መሰረት በማድረግ በሚወጣው የአስተዳደር ደንብ መሠረት ይሆናል።

## 13. ቃለ መሃላ ስለመፈጸም

በኮሚሽኑ የተቀጠረ ማንኛውም ሰራተኛ ለፌዴራሉ እና ለክልሉ ህገ-መንግስት ታማኝ በመሆን የተጣለበትን ህዝባዊ አደራና ሙያዊ ኃላፊነት ለመወጣት ቃለ መሃላ ይፈጽማል። የቃለ መሃላው ዝርዝር ይዘት በአስተዳደር ደንቡ ይወሰናል።

www.chilot.me

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

14. በጀት

የኮሚሽኑ በጀት በመንግስት ይመደባል።

15. የሂሳብ መዛግብት

1. ኮሚሽኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል።

16. ስለ ኮሚሽኑ የፖሊስነትና የአቃቤ ህግነት ስልጣን

1. የኮሚሽኑ አቃቤ ህግ ሙያዊ ነጻነቱን ለመጠበቅ በሚያስችል መልክ ነጻ ሆኖ ይደራጃል፤
2. ስለ መመርመርና ስለ ክስ በሃገሪቱ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ስርዓት ህግና በሌሎች ህጎች ለፖሊስና ለአቃቤ ህግ የተሰጠ ስልጣን በዚህ አዋጅ ውስጥ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ለኮሚሽኑ ተሰጥቶታል።

17. ተፈፃሚነት ስላላቸው ህጎች

የሙስና ወንጀሎችን በመዳኘት በፌደራል መንግስት የወጣውና በሥራ ላይ ያለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ ስርዓት እና የማስረጃ ህግ ቁጥር 236/1993 እና ማሻሻያ አዋጆቹ በክልሉ ውስጥ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

18. የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች መቋቋም

1. በየደረጃው በሚገኙ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች እና ልማት ድርጅቶች የሚያስተባብሩ እና ለየመስሪያ ቤቶቹ የበላይ ኃላፊዎች የሚያማክሩ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ይቋቋማል።
2. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ተጠሪነቱ ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሆኖ ከኮሚሽኑ ጋር የሥራ ትብብር ይኖረዋል።
3. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሰራተኛን የመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በቅጥር፣ በእድገት ወይም በዝውውር ይመድባል፣ ለሥራ መደቡ ልምድ እንዱሁም የሥነ-ምግባር ሁኔታ በሚመለከት ከኮሚሽኑ ጋር በመመካከር ይወሰናል።
4. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ ከኮሚሽኑ ጋር የሚኖረውን የስራ ግንኙነት በሚመለከት በዝርዝር ደንብ ይወሰናል።

19. የመተባበር ግዴታ

ማናቸውም ሰው ከኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር ጋር በተያያዘ ለሚጠየቀው ትብብርና ድጋፍ የመተባበር ግዴታ አለበት።።

20. ቅጣት

በሌላ ህግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፤

1. ማንኛውም ሰው ለኮሚሽኑ፣ ለፍትህ አካላት ወይም ለመንግስት መሥሪያ ቤት ኃላፊ ወይም ለልማት ድርጅት ኃላፊ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ መረጃ ወይም ማስረጃ በሰጠ ሰው ላይ ተጽኖ ለማድረግ ወይም ጉዳት ለማድረስ የሞከረ ወይም ያደረሰ ወይም ይህንኑ ሰው ለመቅጣት የሞከረ ወይም የቀጣ እንደሆነ ከሶስት ዓመት በማያንስ ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከስድስት ሺህ ብር በማያንስ ከሃያ አምስት ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።
2. ማንኛውም የኮሚሽኑ ዐቃቤ ህግ ወይም ሰራተኛ በህግ የተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት ያለ አግባብ የተገለገለ እንደሆነ በዚያም የተነሳ ያገኘው ጥቅም መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአምስት ዓመት በማያንስ ከአስራ አምስት ዓመት በማይመልጥ ጽኑ እስራት እና ከሶስት ሺህ ብር በማያንስ ከአስር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።
3. ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ ኮሚሽኑን ለማሳሳት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት ሀሰተኛ ሪፖርት ጥቆማ ወይም መረጃ ለኮሚሽኑ ያቀረበ እንደሆነ ከአንድ አመት በማያንስ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከሦስት ሺህ ብር በማያንስ ከአስር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።
4. ማንኛውም ሰው የኮሚሽኑ ሰራተኛ መስሎ በመቅረብ የማታለል ሥራ የፈጸመ እንደሆነ ከሶስት ዓመት በማያንስ ከአስር ዓመት በማይበልጥ በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማያንስ ከአስራ አምስት ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።
5. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 19 በተደነገገው መሰረት ኮሚሽኑን ለመተባበር ኢምቢተኛ የሆነ እንደሆነ ከስድስት ወር በማያንስ ከአራት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

www.chilot.me

6. ማንኛውም ሰው የኮሚሽኑን ሥራ ያደናቀፈ ወይም ለማደናቀፍ የሞከረ እንደሆነ ከሁለት ዓመት በማያንስ ከአስር አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማያንስ ከሃያ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡ ወንጀሉ የተፈጸመው ኃይል በመጠቀም የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ የተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ይሆናል፡፡
7. የሙስና ወንጀል ምርመራ ሲጀምር ስለመሆኑ ወይም በምርመራ ላይ ስለመሆን ወይም ጉዳይ በምርመራ ላይ መሆኑን እያወቀ ስለተፈጸመው ድርጊት ምርመራውን ከያዘው ጉዳዩ በምርመራ ላይ መሆኑን እያወቀ ስለተፈጸመው ድርጊት ምርመራውን ከያዘው ክፍል ፈቃድ ውጭ መግለጽ፣ መጻፍ፣ ማሰራጨት ከስድስት ወር በማያንስ ከአራት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና ከአንድ ሺህ ብር በማያንስ ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ያስቀጣል፡፡
8. ማንኛውም የመንግስት ባለሥልጣን ወይም የመንግስት ሰራተኛ በሚሰራበት መስሪያ ቤት የሙስና ወንጀል ስለመፈጸሙ እያወቀ ሳያሳውቅ መቅረት እስከ አምስት ዓመት ቀላል እስራት እና እስከ ሺህ ብር መቀጮ ይቀጣል፡፡
9. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1፣ 3፣ 4፣ 5 እና 6 የተመለከቱት ወንጀሎች በህግ ሰውነት ባለው ድርጅት በተፈጸመ ጊዜ የገንዘብ ቅጣቱ አምስት እጥፍ ይሆናል፡፡

## 21. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ተፈጽመው ምርመራቸው በሌሎች አካላት በጅምር ወይም በሃደት ያለ፣ የተጠናቀቁ ወይም በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያሉ የሙስና እና ከሙስና ጋር የተያያዙ የወንጀል ጉዳዮች በነበሩት ሁኔታ ቀጥለው ውሳኔ ያገኛሉ፡፡

## 22. የተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሌሎች ህጎች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 23. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ኮሚሽኑ ይህንን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 24. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሐረር ነሐሴ 17 ቀን 1999 ዓ.ም

ሙራድ አብዱልሃዲ
የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት
ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| 12ኛ ዓመት ቁጥር 5<br>12th Year No. 5 | | ሐረር ነሐሴ 17 ቀን 1999<br>Harar, Aug. 23 /2007 |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ ብር 4.20<br>Unit price Bir 4.20 | በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 952<br>P.o.Box 952 |

ማዉጫ

አዋጅ ቁጥር 72/1999
የሐረሪ ሕ/ክ/መንግስት ብዙሃን መገናኛ ኤጄንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ........................................................ገጽ 550

## አዋጅ ቁጥር 72/1999
## የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት ብዙሃን መገናኛ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ

በህገ-መንግሥቱ በተደነገገው መሠረት በመንግሥት ባለቤትነት ሥር በሚገኙት የብዙሃን መገናኛዎች ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ሐሳቦችና አመለካከቶች በነጻ መንሸራሸራቸዉን ለማረጋገጥ ብዙሃን መገናኛዎቹ የተቋምና የአሠራር ነጻነት እንዲሁም የህግ ጥበቃ እንዲኖራቸው ማድረግ በማስፈለጉ፤

የብዙሃን መገናኛዎች በክልሉ ማቋቋሙ በአከባቢያችን የሚከናወኑ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ዉስጥ የሚኖራቸዉን የላቀ ሚና እና አስተዋጽኦ ከግምት ዉስጥ በማስገባት የአገልግሎት አድማሳቸዉን ለማስፋት የሚያስችላቸዉን ተቋማዊ ጥንካሬ እንዲያገኙ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የመረጃ ልውውጥ ፍላጎት በዓለም አቀፍም ሆነ በአገራዊ ደረጃ በፍጥነት እያደገ መምጣቱን ከግምት ዉስጥ በማስገባት፣ የክልሉ ብዙሃን መገናኛ ኤጀንሲ የህብረተሰቡን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች በቅርበት ሆኖ በስፋት በመዘገብ ሊጫወት የሚችለዉን ሚና ለመረዳት ኤጀንሲው በተገቢ መንገድ ተዋቅሮ በአገሪቱ ካሉ ሌሎች የብዙሃን መገናኛዎች ጋር ተወዳዳሪ ሆኖ ሃላፊነቱን በብቃት እንዲወጣ ማድረግ በማስፈለጉ፣

በሐረሪ ህዝብ ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ 5 (2) (ሀ) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ ‹‹የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት ብዙሃን መገናኛ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 72/2000›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ዉስጥ፦

1. “ቦርድ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6(1) እና 8(1) መሠረት የተቋቋመው የብዙሃን መገናኛ ኤጀንሲ ሥራ አመራር ቦርድ ነው።
2. “ የብዙሃን መገናኛ” ማለት በሬዲዮና ቴሌቪዥን እንዲሁም በጋዜጦችና በመጽሔቶች አማካኝነት መረጃ /ኢንፎርሜሽን/ ማዘጋጀትና የማሰራጨት ሥራዎችን የሚያከናዉኑ፣ የዜና እና የፕሮግራም ሥራዎችንና መጣጥፎችን በማጠናቀር በልዩ ልዩ

www.chilot.me

ዘዴዎች ለሕዝብ የሚሰራጩ ወይም እነዚህን በቀጥታ ለሚያስተላልፉ ሌሎች ተቋማት የሚያከፋፍሉ ተቋማት ናቸው።

3. "ጋዜጠኛ" ማለት በብዙሃን መገናኛ ድርጅት ዉስጥ በአዘጋጅነት፣ በአርታኢነት፣ በዘጋቢነት፣ በተንቀሳቃሽ ፊልም አንሺነት፣ በፊልም ኢዲተርነት ፣ በፊልም ዳይሬክተርነት ፣ በቴክኒሻንነት ወይም ዜና እና መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማቀነባበርና በማሰራጨት ሙያ የተሰማራ ማናቸዉም ሰው ነው።

4. "ሰው" ማለት ማናቸዉም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰዉነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

5. "ኤጀንሲ" ማለት የብዙሃን መገናኛ ኤጀንሲ ነው።

## 3. መቋቋም

1. የብዙሃን መገናኛ ኤጀንሲ /ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲ"/ እየተባለ የሚጠራ ህጋዊ ሰዉነት ያለዉና እራሱን የቻለ የሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለቦርዱ ይሆናል።

## 4. አላማ

ኤጀንሲው የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል።

1. የፌደራሉና የክልሉ ህጎች እንዲሁም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ፖሊሲዎች፣ ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ሐሳብን በነፃ የመግለጽ ነጻነትን ማበረታታት፤
2. የክልሉ ሕዝብ ለመረጃ ቅርበት እንዲኖረው ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃዎችን እንዲያገኝ ማድረግ፣ በዚህም በዋና ዋና የአገሪቱንና የክልሉ ጉዳዮች ላይ ብሔራዊ መግባባትን መፍጠር እንዲችል መሥራት፤
3. በክልሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ዉስጥ ኢጋሻር ሚና መጫወትና በህብረተሰቡ ዉስጥ ዲሞክራሲያዊ ባህል እንዲጎለብት ማበረታታት።

## 5. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፦

1. ለክልሉ ህዝብ ጠቀሜታ ያላቸዉን አስፈላጊ ዜናና ዜና ነክ መረጃዎችን በፕሬስ ዉጤቶች፣በሬዲዮና በቴሌቪዥን ማሰራጫዎች ለህዝብ ያስተላልፋል፣ ለዚህም እንዲረዳው መደበኛ የጋዜጣና የመጽሔት፣ ሌሎች ህትመቶች እንዲሁም የሬዲዮና የቴሌቪዥን ማሰራጫ ፕሮግራሞች እንዲኖሩት ይደረጋል።
2. የመንግሥት ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች፣ ፖሊሲዎችንና ህጎች ለህዝብ ያስተዋዉቃል፣ ህዝቡም በስትራቴጂዎቹ፣ ፖሊሲዎቹና በህጎቹ ላይ ሐሳቡን እንዲለዋወጥባቸው፣ እንዲመክርባቸዉና አስተያየቱን እንዲሰጥባቸው በዚህም ብሔራዊ መግባባት ላይ እንዲደርስ ምቹ የሚዲያ መድረኮችን ይፈጥራል።
3. የክልሉ ህዝብ ስለሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለዉን ግንዛቤ ለማጎልበት የሚረዱ ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን ከተሞክሮዎቹ ጋር እያዛመደ ያቀርባል።
4. ነፃ የህዝብ አስተያየቶችንና ጥቆማዎችን ተቀብሎ ያስተናግዳል የሚመለከታቸዉንም አካላት በመጠየቅ ያጣራል ዉጤቱንም መልሶ ለህዝብ ይገልጻል።
5. የህዝብ ጠቅላላ ዕዉቀት የሚያዳብሩና የመዝናናት ፍላጎቱን የሚያረኩ ልዩ ልዩ ጽሑፎችን የሬዲዮም ሆነ የቴሌቪዥን ዝግጅቶችን እየሠራ በተለያዩ ዘዴዎች ያሰራጫል።
6. ወቅታዊነት ያላቸዉን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ተከታትሎ ይዘግባል።
7. የፎቶግራፍና የተንቀሳቃሽ ምስል ዶክመንቴሽን፣ የህትመትና የማስታወቂያ፣ አገልግሎቶችን ይሰጣል።
8. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የህትመት አገልግሎቶችን የሬዲዮና ቴሌቪዥን ፕሮግራም ማቀነባበሪያና ማሰራጫዎችን፣ የዜናና መረጃ ማስተላለፍ ወይም ማሸጋገሪያዎችን እንዲሁም

www.chilot.me

ለተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚዉሉ ሌሎች ተቋማትን እና መሳሪያዎችን በተገቢው ሥፍራ ይተክላል፣ ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፡፡

9. ለሚሰጠው አገልግሎት ተመጣጣኝ ዋጋ ያስከፍላል፣ እንደአስፈላጊነቱም በከፊልም ሆነ በሙሉ ከክፍያ ነጻ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል፡፡

10. በአገሪቱ ህግ መሠረት በአገር ዉስጥ ካሉ ተመሳሳይ ድርጅቶች ጋር ዜናዎችንና መረጃዎችን ለመለዋወጥ ሆነ የሥልጠናና የልምድ ልዉዉጦችን ለማድረግ የሚያስችሉትን የሥራ ግንኙነቶች ይመሰርታል፡፡

11. በአገር ዉስጥም ከሚገኙ ድርጅቶች ቴክኒካዊ አቅም ለማጎልበት ድጋፍ ለማድረግ ፍቃደኝነቱ ካላቸው ድርጅቶች ጋር በክልሉና በአገሪቱ ፖሊሲዎችና ህጎች መሠረት አብሮ ይሠራል፡፡

12. የክልሉ የብዙሃን መገናኛዎች ስለሚስፋፉበትና በተስማሚ ቴክኖሎጂ ስለሚደራጁበት፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ስለሚሰጡበት ሁኔታ በማጥናት ሐሳብ ያቀርባል ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያዉላል፤

13. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ዉል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ይከሰሳል፤

14. ዓላማዉን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ህጋዊ ተግባራትን ያከናዉናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ኤጀንሲው አወቃቀርና ሥልጣን

### 6. የኤጀንሲው አካላት

ኤጀንሲው የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡፡

1. የሥራ አመራር ቦርድ፤
2. የኤዲቶሪያል ኮንፈረንስ፤
3. ዋና ሥራ አስኪያጅ፤
4. አስፈላጊ የሆኑ የሥራ ክፍሎችና ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

### 7. የሥራ አመራር ቦርድ መቋቋም

1. ኤጀንሲውን በበላይነት የሚመራ የስራ አመራር ቦርድ ይኖረዋል ፡፡ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል ፡፡

### 8. ተጠሪነት

የስራ አመራር ቦርዱ ተጠሪነት ለክልል ም/ቤት ይሆናል፡፡

### 9. የሥራ አመራር ቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የስራ አመራር ቦርዱ ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
2. ኤጀንሲው የብዙሃን መገናኛዎችን የሚመለከት ፖሊሲዎችን፣ ህጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረጉን ያረጋግጣል፤
3. በህዝብ ሊታወቁ የሚገባቸው የመንግሥት ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በድርጅቱ ልዩ ልዩ የብዙሃን መገናኛዎች አማካኝነት በወቅቱ መተላለፋቸዉን ይከታተላል፤
4. ኤጀንሲው በሚሰጣቸው አገልግሎቶች የክልሉ ሕዝብ ምን ያህል ተጠቃሚ እንደሆነ ይገመግማል፣ ይበልጥ ተጠቃሚ የሚሆንባቸዉን መንገዶችም በየጊዜው እየፈተሸ ተግባራዊ እንዲሆኑ ለድርጅቱ አቅጣጫዎችንና መመሪያዎችን ይሰጣል፤
5. ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ መሠረት የሚፈጽማቸዉን ተግባራት በተመለከተ ከህዝብ በሚነሱ ስሞታዎችና በሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ ተገቢ ማብራሪያዎችን እንዲሰጥ ያደርጋል እንደአስፈላጊነቱም ስሞታዎችንና ቅሬታዎችን መርምሮ ያፀድቃል በሥራ ላይ እንዲዉል ያዛል፤
6. ኤጀንሲው በብሔር በጾታ፣ በሃይማኖት እና በፖለቲካ አመለካከቶች መካከል ልዩነት ሳያደርግ ለሁሉም ወገኖች ሚዛናዊ የመረጃ ሽፋን መስጠቱንም ይቆጣጠራል፤ ማንኛዉም ተዘጋጅቶ እንዲቀርብለት በማድረግ መርምሮ ያፀድቃል በሥራ ላይ እንዲዉል ያዛል፤
7. የኤጀንሲውን መዋቅር ገምግሞ ያፀድቃል ሥራ ላይ እንዲዉልም ያዛል፤

www.chilot.me

8. የኤጀንሲው የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር መመሪያና ማኑዋል ተዘጋጅቶ እንዲቀርብለት በማድረግ ያፀድቃል፣ ሥራ ላይ እንዲውልም ያዛል፣
9. የኤጀንሲው የአጭር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እንዲሁም ዓመታዊ የካፒታልና መደበኛ በጀት ዕቅድና ሪፖርት ያፀድቃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣
10. ኤጀንሲው ከመንግሥትና ከዉስጥ ገቢ የተመደበለትን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋሉን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣
11. ኤጀንሲዉ የሚጠናከርበትንና አሠራሩ የሚሻሻልበትን መንገድ ይቀይሳል፣
12. ኤጀንሲዉን በሚመለከት ሌሎች የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ይወስናል፣
13. ለክልሉ ካቢኔ የሥራ ሪፖርትን ያቀርባል።

## 10. የኤዲቶሪያል ኮንፈረንስ አደረጃጀት

በድርጅቱ የሚገኙ ዋና አዘጋጆች እንዲሁም የዘርፍ አስተባባሪዎችና በዚህ ደረጃ የሚታዩ የዝግጅት ክፍሎች በአባልነት የሚሳተፉበት የአመራር አካል ነው።

ኤዲቶሪያል ኮንፈረንሱ የሚመራው በዋና አዘጋጆች ነው። ኮንፈረንሱ የድርጅቱ የከፍተኛ የሙያ የአመራር አካል ነው።

ኤዲቶሪያል ኮንፈረንስ መደበኛ በሆነ መንገድ በየቀኑ አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል። አስቸኳይ ሥራዎች ከመጡ ከመደበኛ ስብሰባ ዉጪ ሊሰበሰብ ይችላል።

## 11. የኤዲቶሪያል ኮንፈረንስ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. ኮንፈረንሱ በዝግጅት ክፍሎች ወይም በማስተባበሪያዎች ስር ላሉ ጋዜጠኞች የዕለት ተዕለት የሥራ አመራር ይሰጣል፣

ለ. የዜና፣ የፕሮግራምና የአምድ ስምሪቶች በኤዲቶሪያል መመሪያው መሠረት ያከናውናል። በዕቅድ የተያዘም ሆነ ድንገተኛ አስቸኳይ ሥራ እንደ ክብደቱ እየወሰነ ጋዜጠኞችን ይመድባል ። ለጋዜጠኛው ኦሬንቴሽን መስጠቱን ያረጋግጣል፣

ሐ. ተከታታይ ዜናዎች፣ ሐተታዎች ዜና ትንታኔ፣ ወቅታዊ ዘገባዎች እንዲሠሩ ይመክራል፤

መ. የዓመት፣ የግማሽና የሩብ ዓመት ዕቅዶች በመቅረጽ ከዕለት ተዕለት ሥራዎቹ ጋር በማጣጣም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ሠ. እለታዊ የዜና የአምድ፣ ፕሮግራም ስርጭትና ህትመት ጊዜዉን ጠብቆ የሚካሄድ መሆኑን ያጋጠሙ ችግሮች ካሉ መፍትሄ ይሻል።

ረ. ካለፈው የእወጃ ሰዓትና የህትመት ዉጤት በመነሳት ሥራዎችን ይገመግማል። ደካማና ጠንካራ ጎኑን በመለየት ለድክመቶቹ መፍትሄ ይፈልጋል፤

ሰ. የኤዲቶሪያል ኮንፈረንሱን ዉሣኔ የሚጠይቁ አስተዳደራዊና ሙያነክ የሆኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ እየተነጋገረ ይወስናል፤

ሸ. ለህብረተሰቡ የሚቀርቡት ዝግጅቶች፣ ጽሁፎች፣ ሥራዎች አዝናኝ፣ አስተማሪና አሳዋቂ በሆነ መልኩ የቀረቡ መሆናቸዉን ይቆጣጠራል።

ቀ. በፕሮጀክት፣ በተነሳሽነት ወይም በተለየ አሳይመንት ተጠናክረው ሊሠሩ የተያዙ ወይም በመስራት ላይ ያሉትን ዜናዎች፣ የፕሮግራሞች፣የአምዶች ጭብጦች በዝርዝር ይመለከታል፤

በ. ኤዲቶሪያል ኮንፈረንሱ ዝግጅት ክፍሎች ወይም ማስተባበሪያዎች በሚወስኑት ቀን ከክፍሉ ጋዜጠኞች ጋር ሥራዉን ይገመግማል። መሥሪያ ቤቱ በሚያወጣው የማበረታቻ ስርዓት መሠረት ጥሩ የሠራዉን እንዲበረታታ፣ ጥሩ ያልሠራው ደግሞ እንዲወገዝ ካልሆነም እንዲቀጣ ለመሥሪያ ቤቱ ያሳዉቃል፤

ተ. ኤዲቶሪያል ኮንፈረንሱ ለፕሮግራምና ለአምድ ባክሎግ እንዲዘጋጁ ያደርጋል። ተግባራዊ መሆኑንም ይቆጣጠራል።

ቸ. በሀገር ዉስጥ የሚካሄዱ ስምሪቶችን ይወስናል። ለስራው የሚመጥኑ ጋዜጠኞችን ይመድባል። የዉጭ ሀገር ጉዞ በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ሃላፊ ይወሰናል።

ነ. ኤጀንሲው በሚወስነው የጊዜ ሰሌዳ የኤዲቶሪያል ኮንፈረንሱ ለሚመለከተው የበላይ አካል በጽሑፍ የሥራ ሪፖርት ያቀርባል።

www.chilot.me

ኘ. በኤዲቶሪያል ኮንፈረንሱ የሚነሱ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ የሚሰጠው ዋና አዘጋጁ ነው፡፡

## 12. የዋናዉ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

1. የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስኪያጅ በቦርዱ አቅራቢነት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሾማል፡፡ ዋናው ሥራ አስኪያጅ ድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የሥራ አመራሩ ቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የድርጅቱን ሥራዎች ይመራል፣ያስተዳድራል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ1 የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስኪያጁ፡-
   ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 የተመለከቱትን የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያዉላል፤
   ለ. የሥራ አመራር ቦርዱ ባጸደቀው የሠራተኞች አስተዳደር መመሪያ መሠረት የድርጅቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ባለሙያዎችንና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
   ሐ. የድርጅቱን የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ እንዲሁም ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና የበጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ ለቦርዱ በማቅረብ ሲወስንለት ተግባራዊ ያደርጋል፤
   መ. ለድርጅቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፤
   ሠ. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጉ ግንኙነቶች ሁሉ ድርጅቱን ይወክላል፤
   ረ. የድረጅቱን ሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት ወቅታዊ ሪፖርቶችን ለቦርዱና ለካቢኔ ያቀርባል፤
3. ዋና ሥራ አስኪያጁ ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለበታች የኤጀንሲው የሥራ ሃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች ዉክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡
   ነገር ግን እሱን ተክቶ የሚሠራው ሰው ከ30 ቀናት በላይ ለሚሆን ጊዜ የሚወክል ከሆነ ዉክልናውን አስቀድሞ ለቦርዱ አቅርቦ መፈቀድ አለበት፡፡

# ክፍል አምስት

## 13. የኤጀንሲው በጀት

1. የኤጅንሲው በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፡፡
   ሀ. ክልሉ ከሚመደብለት በጀት፤
   ለ. በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚሰበሰበው አገልግሎት ክፍያ እና
   ሐ. ከሌሎች ምንጮች፡፡
2. በዚህ አንቀጽ 1 ሥር ከ/ሀ/ እስከ /ሐ/ ከተዘረዘሩት ምንጮች የሚሆነው ገቢ በኤጀንሲው ስም በሚከፈት የባንክ ሂሣብ ተቀማጭ ሆኖ የኤጀንሲውን ሥራዎች ለማከናወን በየጊዜው ወጪ ያደርጋል፡፡
3. የኤጀንሲው የገቢ እንዲሁም የንብረት አስተዳደርና አጠቃቀም በድርጅቱ የገንዘብና የንብረት አስተዳደር መመሪያና ማኑዋል መሠረት የሚፈጸም ሆኖ ማኑዋሉን የማሻሻልና የመቀየር ሥልጣን የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ይሆናል፡፡

## 14. የሂሳብ መዛግብት

1. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤
2. የኤጅንሲው ሂሣብ መዛግብትና የገንዘብ ሰነዶች በየዓመቱ በክልሉ ዋና ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራሉ፡፡

## 15. ደንብ የማውጣት ስልጣን

የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ የማውጣት ስልጣን ተሰጥቶታል ፡፡

## 15. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሐረር ነሐሴ 17 ቀን 1999

ሙራድ አብዱልሃዲ

የሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት

ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

12ኛ ዓመት ቁጥር 6
12th Year No 6

ሐረር ነሐሴ 17 ቀን 1999
HARAR, Aug. 23/2007

ያንዱ ዋጋ ብር 9.80
Unit price Br. 9.80

በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት
ጠባቂነት የወጣ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር 952
P.O. Box 952

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 73/1999
የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ለ2000 በጀት ዓመት ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ ........................................ ገጽ 556

## አዋጅ ቁጥር 73/1999
## ለሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት በ2000 በጀት አመት ለሚሰሩ ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ

ለ2000 ዓ.ም በጀት ዓመት ለሚከናወኑ ስራዎችና አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን በጀት በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ አጽድቆ ስራ ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ፤

ከፌደራል መንግስት ለክልሎች የሚሰጠውን ድጎማና ከክልሉ ከተለያዩ ገቢዎች ከሚሰበሰበው ገቢ የሚገኘውን ገንዘብ መሰረት አድርጎ የክልሉን መንግስት የ2000 አመት በጀት መወሰን በማስፈለጉ፣ በክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 51(2) (ነ) ላይ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለውን አውጇል::

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ «የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የ2000 በጀት ዓመት የበጀት አዋጅ ቁጥር 73 /1999 » ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**2. የክልሉ አጠቃላይ ገቢ በጀት**

በፌደራል መንግስት ከሚደረገው ድጎማና ክልሉ ከሚሰበስበው ገቢ በ2000 በጀት ዓመት የክልሉ አጠቃላይ ገቢ የሚከተለው ይሆናል::

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. መደበኛ ገቢ | ብር | 36,361,500 |
| ለ. ከፌደራል መንግስት ድጎማ | ብር | 135,720,000 |
| ጠቅላላ ድምር | ብር | 172,081,500 |

**3. ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ለማዋል የተፈቀደ ጠቅላላ በጀት**

ከሐምሌ 1 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2000 ዓ.ም በሚፈጸመው በአንድ የበጀት ዓመት ጊዜ ውስጥ በክልሉና በፌደራል መንግስት ከሚደረገው ድጎማ የሚገኝ ገቢ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ በተዘረዘረው መሰረት ቀጥሎ እንደሚከተለው ወጪ ሆኖ እንዲከፍል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል::

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. መደበኛ ወጪዎች | ብር | 90,707,700 |
| ለ. ከፒታል ወጪዎች | ብር | 72,113,800 |
| ሐ. መጠባበቂያ በጀት | ብር | 9,260,000 |
| ጠቅላላ ድምር | ብር | 172,081,500 |

4. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 2 እና 3 ላይ የተገለጸው የገቢና የወጪ ዝርዝር ከዚህ አዋጅ ጋር ተያይዟል::

5. ይህ የወጪ በጀት በክልሉ ለሚገኙ ቋሚ የመንግስት ሠራተኞች ለልዩ ልዩ ጉዳዮች ማስፈጸሚያ የደሞዝ ብድር በየወሩ ሳይቋረጥ እየተከፈለ የሚያልቅ ሆኖ የክፍያውን ጊዜ ለመወሰን እና በዚህ አኳሃን በሚሰጠው ብድር ላይ የሚከፈለው የወለድ መጠን የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

### ክፍል ሁለት
### በጀት አስተዳደር

6. የክልሉ የበጀት አስተዳደር የሚመራው አግባብ ባላቸው የክልሉ አዋጅ እና የፋይናንስ ደንብ፤ መመሪያዎችና የአሰራር ስርዓቶች መሠረት ነው::

www.chilot.me

7. ክልሉ ስለሚኖረው በጀት የማስተዳደር ስልጣን በዚህ አዋጅ ላይ ላልተመለከቱ ለአዲስ ወይም በበጀት ዓመቱ ለተፈቀዱ ለካፒታልም ይሁን ለመደበኛ ሥራዎች ከውጭ ብድር ከእርዳታ ወይም ከሀገር ውስጥ ብድር፣ ዕርዳታ ወይም ከሌላ ምንጭ ተጨማሪ ገቢ ሲገኝ በክልሉ እየተወሰነ በስራ ላይ እንዲውል ሆኖ ለበጀት አመቱ በተጨማሪ በጀትነት በክልሉ ም/ቤት እንዲጸድቅ ይደረጋል።

8. የክልሉ አስፈጻሚ አካላት ስልጣን

1. የሐረሪ ክልል አስፈጻሚ መ/ቤቶች እና የቀበሌ መስተዳድር የበላይ ኃላፊዎች በየስራ ክፍሎቻቸውና ፕሮጀክቶቻቸው አገልግሎት በዚህ አዋጅ መሠረት የተፈቀደላቸውን በጀት የማስተዳደር ስልጣን አላቸው።
2. በየደረጃው የሚገኙ አስፈጻሚ አካላት ለየመስሪያ ቤታቸው ስራና አግልግሎት በዚህ አዋጅ ከተፈቀደ ላቸው በጀት ክፍያ እንዲፈጸምላቸው በሚጠይቁ ጊዜ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ከክልሉ ገቢና ከሌላ ምንጭ እንዲከፍል በዚህ አዋጅ መሠረት ታዟል።
3. መንግስት መ/ቤቶች በዚህ አዋጅ ላይ ላልተ መለከተ ለካፒታልም ሆነ ለመደበኛ ተጨማሪ ስራዎች ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሀገር በአይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ የሚያገኙትን ዕርዳታ በስራ ላይ ማዋል እና ይህንኑ ሂሳብ በመስሪያ ቤቱ አርዕስት ንዑስ አርዕስት ፕሮግራም ፕሮጀክት ስር መዝግቦ በመያዝ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለገ/ኢ/ልማት ቢሮ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።
4. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ መሠረት የደረሰውን ሪፖርት በማጠቃለል መዝግቦ በተጨማሪ በ ጀትነት ይይዛል። ይህንን ተጨማሪ በጀት የሚያሳይ ሪፖርት ለክልሉ መንግስት ያቀርባል።

## ክፍል ሶስት

## የበጀት ዝውውር

9. በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 9/91 በአንቀጽ 17 የተ ደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በታች ለተመለከቱት አካላት በዚህ አዋጅ መሠረት የበጀት ዝውውር ስልጣን ሙሉልና ተሰጥቷቸዋል።

1. **የክልሉ ካቢኔ**

ሀ. ከአንድ የመንግስት መ/ቤት ከተፈቀደ የካፒታል በጀት ወደ ሌላ መ/ቤት ካፒታል በጀት ማዛወር፤

ለ. በበጀት ዓመቱ በጀት ላልተፈቀደለ ፕሮጀክት የካፒታል በጀት መመደብ ።

2. **የሐረሪ ክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ**

ሀ. በክልል ደረጃ ያለ የመንግስት መ/ቤት ሲጠይቅ በአንድ የመንግስት መ/ቤት ስር ከአንድ ፕሮግራም/ስራ ክልፍ ወይም ፕሮጀክት ወደ ሌላ የስራ ክፍል ወይም ፕሮጀክት የማዛወር፤

ለ. በክልል ደረጃ ያለ የመንግስት መ/ቤት ሲጠይቅ ለመደበኛና ካፒታል በጀት ከተፈቀደው ደመወዝና አበል ወደ ስራ ማስኬጃ ማዛወር፤

ሐ. በቀበሌ የተያዘን መደበኛና ካፒታል በጀት በጀቱ በተፈቀደለት ቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት የጹሁፍ ስምምነት መሰረት ወደ አስተዳደር ወይም ወደ ሌላ ቀበሌ የማዛወር፤

3. **ለሴክተር መ/ቤቶችና ቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤት**

ሀ. ከዋና ዋና ርዕሶች ከተያዘውና ከደሞዝና አበል በስተቀር በመደበኛ በጀት በተያዘው በአንድ የስራ ክፍል ባሉት የሂሳብ መደቦች በአንድ ሂሳብ መደብ ውስጥ ከአንድ ንዑስ ሂሳብ መደብ ወደ ሌላ ንዑስ ሂሳብ መደብ የማዛወር ስልጣን ተሰጥቶታል።

ለ. በተፈቀደ የካፒታል በጀት ውስጥ በአንድ የስራ ክፍል ፕሮጀክት ስር በአንድ ሂሳብ መድብ ውስጥ ከአንድ ንዑስ ሂሳብ መደብ ወደ ሌላ ንዑስ ሂሳብ መደብ የማዛወር ስልጣን ተሰጥቶታል።

## ክፍል አራት

10. የቤቶች ልማት ፕሮጀክት

ለተቀናጀ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ግንባታ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ2000 በጀት ዓመት ከቦንድ ሽያጭ በብድር የተገኘ ብር 143,348,984 ( አንድ መቶ አርባ ሶስት ሚሊዩን ሶስት መቶ አርባ ስምንት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አራት ብር ) ለበጀት ዘመኑ ለ1100 ቤቶች ማጠናቀቂያና ለ1540 አዳዲስ ቤቶች ግንባታ ስራ ላይ እንዲውል ጸድቋል።

11. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሐምሌ 1 ቀን 1999 ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር ነሐሴ 17 ቀን 1999 ዓ.ም

ሙራድ አብዱልሀዲ

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

## የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የ2000 በጀት ዓመት ገቢና ወጭ በጀት ድልድል

| | | | ብር |
|---|---|---|---|
| 1. የገቢ በጀት | | | |
| 1.1 በክልሉ መንግስት የሚሰበሰብ ገቢ | | | 28,361,500 |
| 1.2 ካለፉት አመታት ተካባች በጀት | | | 8,000,000 |
| 1.3 ከፌደራል መንግስት ድጎማ | | | 135,720,000 |
| 1.3.1 ከመንግስት ግ/ቤት | 126,000,000 | | |
| 1.3.2 ከውጭ አገር ብድር | 4,310,000 | | |
| 1.3.3 ከውጭ አገር አርዳታ | 5,410,000 | | |
| **ጠቅላላ የገቢ በጀት ድምር** | | | **172 ,081,500** |
| 2. የወጪ በጀት | | | |
| **2.1 ለመደበኛ በጀት** | | | **90,707,700** |
| 2.1.1 ለሴክተር መ/ቤት | | 63,956,500 | |
| ሀ/ ለደሞዝ | 42,915,600 | | |
| ለ/ ስራ ማስኬጃ | 21,000,900 | | |
| 2.1.2 ለቀበሌ መስተዳድር | | 26,751,200 | |
| ሀ/ ለደሞዝ | 22,737,400 | | |
| ለ/ ስራ ማስኬጃ | 4,013,800 | | |
| 2.2 መጠባበቂያ በጀት | | | 9,260,000 |
| **2.3 ካፒታል በጀት** | | | **72,113,800** |
| 2.2.1 ለሴክተር መ/ቤቶች | | | |
| ሀ/ ለኢኮኖሚ ልማት አገ. | | 48,090,100 | |
| ለ/ ለማህበራዊ ልማት አገ. | | 10,203,700 | |
| ሐ/ ጠቅላላ ልማት አገ. | | 4,820,000 | |
| 2.2.2 ለቀበሌ መስተዳድሮች ጠቅላላ ልማት | | 9,000,000 | |
| **ጠቅላላ መደበኛና ካፒታል በጀት ወጪ ድምር** | | | **172,081,500** |

www.chilot.me

# የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት
# የ2000 በጀት ዓመት የክልሉ ገቢ
# ከፌደራል መንግስት ድጎማ ከውጭ ብድርና እርዳታ ከአገር ውስጥ ብድር
# ማጠቃለያ

1. መደበኛ ገቢ

| | |
|---|---|
| ሀ. ከቀጥታ ታክስ | 21,314,500 |
| ለ. ቀጥታ ካልሆኑ ታክስ | 1,816,200 |
| ሐ. ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች | 5,230,800 |
| መ. ልዩ ልዩ ገቢዎች | 8,000,000 |
| (ካለፉት አመታት ተካባች በጀት) | |
| መደበኛ ገቢ ድምር | 36,361,500 |

2. ከፌደራል መንግስት ድጎማ

| | |
|---|---|
| ሀ. ከመንግስት ግ/ቤት | 126,000,000 |
| ለ. ከውጭ ሀገር ብድር | 4,310,000 |
| ሐ. ከውጭ ሀገር እርዳታ | 5,410,000 |
| ጠቅላላ የድጎማ ድምር | 135,720,000 |
| ጠቅላላ መደበኛ ገቢ, ድጎማና እርዳታና ብድር | 172,081,500 |

www.chilot.me

| | | የአመቱ ዕቅድ<br>በብር |
|---|---|---|
| | **ጠቅላላ ድምር** | **28,361,500** |
| | **ድምር** | **28,361,500** |
| **1100-1300** | **ቀጥታ ታክሲ** | **21,314,500** |
| **1101-1110** | **ከገቢ ከትርፍና ዋጋ እድገት ገቢ ግብር** | **21,314,500** |
| 1101 | ምንዳና ደመወዝ | 9,005,600 |
| 1102 | ከኪራይ ገቢ ግብር | 191,300 |
| 1103 | የግለሰቦች የንግድ ስራ ትርፍ ግብር | 1,439,100 |
| 1104 | የንግድ ድርጅቶች ትርፍ | 329,600 |
| 1106 | የካፒታል ገቢ | 2,500 |
| 1107 | ከግብርና ስራ ገቢ ግብር | 104,200 |
| 1109 | ከገቢ እቃዎች የቅድሚያ ገቢ ግብር | 1,643,300 |
| 1111 | የወለድ ገቢ ግብር | 39,800 |
| 1112 | የጫት ገቢ | 8,559,100 |
| | **ቀጥታ ያልሆነ ታክስ** | **1,816,200** |
| **11-20-1190** | **የተጨማሪ እሴት ታክስ** | **8,400** |
| **1120-1160** | **የአገር ውስጥ ሽያጭ ታክስ** | |
| 1169 | ሌሎች እቃዎች | |
| 1170-90 | የአገልግሎት ተጨማሪ እሴት ታክስ | 8,400 |
| 1176 | ስራ ተቋራጭ | 8,400 |
| | አገር ውስጥ የሚመረቱ የእቃዎች | |
| 1220-40 | ተርን ኦቨር ታክስ | **710,000** |
| 1224 | ከምግብ | 20,400 |
| 1225 | ከለስላሳ መጠጥ | 22,500 |
| 1227 | ከአልኮልና የአልኮል መጠጥ | 19,300 |
| 1228 | ከቢራ | 26,700 |
| 1231 | ጥጥ ድርና ማግ ጨርቃጨርቅ ልብሶች | 83,600 |
| 1232 | ከቆዳና የቆዳ ውጤቶች | 9,400 |
| 1234 | ብረትና ቆርቆሮ | 19,400 |
| 1235 | የጽህፈት መሳሪያ | 4,100 |
| 1237 | እርሻና የእርሻ ውጤቶች | 34,600 |
| 1238 | እንጨትና የእንጨት ውጤቶች | 11,500 |
| 1249 | ከሌሎች | 458,500 |
| **1250-70** | **የአገልግሎት ተጨማተሪ እሴት ታክስ** | **254,100** |
| 1251 | | |
| 1252 | ከጋራዥ | 14,900 |
| 1253 | ከልብስ ንፅህና | 1,800 |

www.chilot.me

| | | |
|---|---|---|
| 1254 | ከልብስ ስፌት | 9,700 |
| 1255 | ጥብቅና | 8,500 |
| 1256 | ከፎቶ ግራፍ ኖና ደራ ጅላኘሮም | 11,600 |
| 1258 | ከስራ ተቋራጭ | 1,700 |
| 1259 | ከመኝታ ቤት | 50,800 |
| 1263 | ከህዝብ መዝናኛ | 18,700 |
| 1264 | ከፀጉር ማስተካከልና ቁንጅና ሳሎን | 15,500 |
| 1265 | ቱሪዝም | 35,600 |
| 1279 | ከሌሎች አገልግሎቶች | 85,300 |
| **1290** | **ቴምብር ሽያጭ ቀረጥ** | **843,700** |
| 1291 | ከቴምብር ሽያጭ | 39,300 |
| 1292 | ከቴምብር ቀረጥ | 804,400 |
| 1400 | ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች | 5,230,800 |
| **1410-1420** | **ከፍቃድና ከሌሎች ክፍያዎች** | **808,600** |
| 1413 | የስራ ፍቃድ | 16,800 |
| 1414 | የፍርድ ቤት መቀጫ | 173,000 |
| 1415 | የፍ/ቤት ዳኝነት | 255,900 |
| 1417 | የንግድ ድርጅቶች የባለሞያዎች ምዝገባና ፍቃድ | 195,700 |
| 1418 | የመጋዘን ኪራዮች | 0 |
| 1429 | ለሌሎች ፍቃደችና ክፍያዎች | 167,200 |
| **1430-50** | **ከመንግስት እቃዎችና የአገልግሎት ሽያጭ** | **1,090,400** |
| 1431 | ከመንግስት ጋዜጣዎች መፅሄቶችና ህትመቶች ሽያጭ | 5,200 |
| 1433 | የማስታወቂያ ገቢ | 37,400 |
| 1435 | ህክምና አገልግሎት | 0 |
| 1436 | የመድሃኒትና የህክምና ዕቃዎች ሽያጭ | 68,700 |
| 1437 | የጤና ምርመራ ህክምና እቃዎች | 759,000 |
| 1439 | የታተሙ ቅጾች | 89,300 |
| 1441 | የወህኒ ቤቶች አስተዳደር ገቢ | 83,500 |
| 1451 | የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት | |
| 1457 | የወጪ መጋራት | 23,300 |
| 1456 | የደን ውጤቶች | 7,400 |
| 1459 | ሌሎች እቃዎችና አገልግሎቶች | 16,600 |
| **1460-70** | **የመንግስት ኢንቨስትመንት ገቢ** | **159,200** |
| 1465 | ለመንግስት ሰራተኞች ከተሰጡ ብድር የሚገኝ ወለድ | 62,800 |
| 1468 | የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ | 96,400 |
| 1480 | **መደበኛ ያልሆኑ እና ልዩ ልዩ ገቢዎች** | **3,172,600** |
| **1489** | **ሌሎች ልዩ ልዩ ገቢዎች** | **3,172,600** |

www.chilot.me

# የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት
# የ2000 ዓመት መደበኛ በጀት

መደበኛ በጀት

**አገልግሎት**
**ዘርፍ**
**አርዕስት**
**ን/አርዕስት**

| | | |
|---|---|---|
| 09 | የሐረሪ ህ/ብ/ክ/መንግስት | |
| 100 | አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት | 23,740,000 |
| 110 | የመንግስት ልዩ ልዩ ክፍሎች | |
| 111 | የክልል ም/ቤት ጽ/ቤት | 1,904,500 |
| 01 | አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት | 1,621,800 |
| 02 | ሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ | 282,700 |
| 113 | ዋና ኦዲት መ/ቤት | 911,200 |
| 115 | የመስተዳድር ም/ቤት ጽ/ቤት | 2,055,900 |
| 119 | ሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት | 299,000 |
| 121 | ፍትህና ጸጥታ ጉዳይ ቢሮ | 1,403,000 |
| 122 | ጠቅላይ ፍርድ ቤት | 3,837,700 |
| 127 | ፖሊስ ኮሚሽን | 5,563,400 |
| 129 | ማረሚያ ቤት | 3,138,900 |
| 134 | የሚሊሺያ ጉዳይ ጽ/ቤት | 778,900 |
| 152 | ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ | 2,175,800 |
| 01 | አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት | 2,132,200 |
| 04 | ግብር ይግባኝ | 37,800 |
| 156 | የገቢዎች ባለስለጣን | 686,400 |
| 155 | ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | 991,300 |
| 200 | ኢኮኖሚ አገልግሎት | 9,117,600 |
| 210 | ግብርና የተፈጥሮ ሀብት | |
| 211 | ግብርና ገጠር ልማት ቢሮ | 3,745,900 |
| 219 | የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን | 152,300 |
| 231 | ንግድ ኢንዱስትሪ ከተማ ልማት ቢሮ | 1,925,300 |
| 232 | አነስተኛና ጥቃቅን ንግድ ስራዎች ማ/ጽ/ቤት | 445,000 |
| 235 | የኢንቬስትመንት ጽ/ቤት | 171,900 |
| 273 | የመንገድ ስራ ባለስልጣን | 806,800 |
| 275 | ቤቶች ልማት ፕሮጀክት | 1,870,400 |
| 300 | ማህበራዊ አገልግሎት | 31,098,900 |
| 310 | አጠቃላይ ትምህርት | |
| 311 | ትምህርት ቢሮ | 12,036,700 |
| 01/01 | አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት | 4,478,000 |
| 03/01 | ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች | 3,108,800 |
| 05/01 | ቴክኒክና ሙያ | 2,381,600 |

www.chilot.me

| | | |
|---|---|---|
| 06/01 | የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም | 1,220,600 |
| 318/01/01 | አቅም ግንባታ | **847,700** |
| **340** | **ጤና** | **14,395,500** |
| **341** | **ጤና ጥበቃ ቢሮ** | |
| 01/01 | አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት | 2,033,800 |
| 04/01 | የሐረር ጤና ሳይንስ ኮሌጅ | 1,763,200 |
| **03/03** | **ሆስፒታሎች** | **10,598,500** |
| 03./01 | ህይወት ፋና ሆስፒታል | 5,404,000 |
| 03/02 | ጀጎል ሆስፒታል | 3,804,500 |
| 03/03 | ሳንባ ነቀርሳ ሆስፒታል | 1,390,000 |
| **350** | **ዕርዳታና መልስ ማቋቋም** | |
| 351 | ባህልና ቱሪዝም ማስታወቂያ ቢሮ | **4,666,700** |
| 1 | አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት | |
| | ድምር | **63,956,500** |
| **400** | **ልዩ ልዩ ወጪዎች** | |
| 460 | መጠባበቂያ | 9,260,000 |
| 461 | የልዩ ልዩ ወጪዎች መጠበቂያ | |
| **09/00/000/** | **ቀበሌ መስተዳደር ጽ/ቤት ድምር** | **26,751,200** |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **99,967,700** |

| የሂሳብ መደብ | መስሪያ ቤት | ብር |
|---|---|---|
| **001** | **አሚር ኑር ቀበሌ መስተዳድር** | **1,754,600** |
| 111 | አሚር ኑር ቀበሌ መስተዳደር | 528,000 |
| 127 | አሚር ኑር ቀበሌ ፖሊስ | 420,800 |
| 311/02/01 | ትምህርት አንደኛ ሳይክል | 450,900 |
| 02/02 | ሁለተኛ ሳይክል | 242,600 |
| 341/02/01 | አሚር ኑር ጤና ክሊኒክ | 112,300 |
| **002** | **አባድር ቀበሌ መስተዳድር** | **1,784,600** |
| 111 | አባድር ቀበሌ መስተዳደር | 552,700 |
| 127 | አባደር ቀበሌ ፖሊስ | 434,900 |
| 311/02/01 | ትምህርት አንደኛ ሳይክል | 132,300 |
| 02/02 | ሁለተኛ ሳይክል | 573,200 |
| 341/02/01 | አባድር ጤና ክሊኒክ | 91,500 |
| **003** | **ሸንኮር ቀበሌ መስተዳድር** | **4,516,600** |
| 111 | ሸንኮር ቀበሌ መስተዳደር | 574,100 |
| 127 | ሸንኮር ቀበሌ ፖሊስ | 377,700 |
| 311/02/01 | ትምህርት አንደኛ ሳይክል | 2,134,200 |
| 02/02 | ሁለተኛ ሳይክል | 1,359,400 |
| 341/02/01 | ሸንኮር ጤና ክሊኒክ | 71,200 |
| **004** | **አቦከር ቀበሌ መስተዳድር** | **3,251,800** |
| 111 | አቦከር ቀበሌ መስተዳደር | 518,800 |
| 127 | አቦከር ቀበሌ ፖሊስ | 348,000 |
| 311/02/01 | ትምህርት አንደኛ ሳይክል | 1,169,300 |
| 02/02 | ሁለተኛ ሳይክል | 1,123,300 |
| 341/02/01 | አቦከር ጤና ክሊኒክ | 92,400 |
| **005** | **ጅኒኤላ ቀበሌ መስተዳድር** | **2,615,400** |
| 111 | ጂኒኤላ ቀበሌ መስተዳደር | 557,400 |
| 127 | ጂኒኤላ ቀበሌ ፖሊስ | 504,400 |
| **311/02/01** | ትምህርት አንደኛ ሳይክል | 649,700 |
| **02/02** | ሁለተኛ ሳይክል | 828,800 |
| **341/02/01** | ጂኒኤላ ጤና ክሊኒክ | 75,100 |
| **006** | **ሐኪም ቀበሌ መስተዳድር** | **3,324,400** |
| **111** | ሐኪም ቀበሌ መስተዳደር | 552,500 |
| **127** | ሐኪም ቀበሌ ፖሊስ | 455,600 |
| **311/02/01** | ትምህርት አንደኛ ሳይክል | 1,418,200 |

www.chilot.me

| | | | |
|---|---|---|---|
| 02/02 | ሁለተኛ ሳይክል | | 823,000 |
| 341/02/01 | ሐኪም ጤና ክሊኒክ | | 75,100 |
| **007** | **ድሬ ጠያራ ቀበሌ መስተዳድር** | **3,966,900** | |
| 111 | ድሬጠያራ ቀበሌ መስተዳደር | | 586,100 |
| 127 | ድሬጠያራ ቀበሌ ፖሊስ | | 380,900 |
| 211-01-01 | ድሬጠያራ ቀበሌ መ/ግብርና ገ/ል/ቢሮ | | 368,000 |
| 311/02/01 | ትምህርት አንደኛ ሳይክል | | 1,189,900 |
| 02/02 | ሁለተኛ ሳይክል | | 903,900 |
| 341/02/01 | ድሬጠያራ ጤና ክሊኒክ | | 138,400 |
| 341/02/02 | ድሬጠያራ ጤና ጣቢያ | | 399,700 |
| **008** | **ኤረር ቀበሌ መስተዳድር** | **2,416,500** | |
| 111 | ኤረር ቀበሌ መስተዳደር | | 542,500 |
| 127 | ኤረር ቀበሌ ፖሊስ | | 375,900 |
| 211/01/01 | ኤረር ቀበሌ ግብርና ገ/ልማት ቢሮ | | 382,900 |
| 311/02/01 | ትምህርት አንደኛ ሳይክል | | 414,300 |
| 02/02 | ሁለተኛ ሳይክል | | 230,600 |
| 341/02/01 | ኤረር ጤና ክሊኒክ | | 179,700 |
| 341/02/02 | ኤረር ጤና ጣቢያ | | 290,600 |
| **009** | **ሶፊ ቀበሌ መስተዳድር** | **3,120,400** | |
| 111 | ሶፊ ቀበሌ መስተዳደር | | 588,800 |
| 127 | ሶፊ ቀበሌ ፖሊስ | | 326,100 |
| 211/01/01 | ሶፊ ቀበሌ ግብርና ገ/ልማት ቢሮ | | 481,700 |
| 311/02/01 | ትምህርት አንደኛ ሳይክል | | 929,100 |
| 02/02 | ሁለተኛ ሳይክል | | 492,500 |
| 341/02/01 | ሶፊ ጤና ክሊኒክ | | 302,200 |
| | **ድምር** | | **26,751,200** |

www.chilot.me

## የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ለ2000 የካፒታል በጀት

| አስፈፃሚ መ/ቤት | ንዑስ ፕሮግራም | ፕሮጀክት | የፕሮጀክቶች ዝርዝር | የፀደቀ በጀት | የፋይናንስ ምንጭ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ከመንግስት | ከዕርዳታ | መለያ | ብድር | መለያ |
| 100 | | | ጠቅላላ ድምር | 72,113,800 | 62,393,800 | 5,410,000 | | 4,310,000 | |
| | | | ጠቅላላ ልማት | 4,820,000 | 4,820,000 | | | | |
| 115 ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት | | | ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት | 520,000 | 520,000 | | | | |
| 000/115/01/01 | 01 | 002 | የመስተዳድር ህንፃና ገስት ሃውስ ጀንሬተር ግዥና ተከላ | 520,000 | 520,000 | | | | |
| 122 ጠቅላይ ፍ/ቤት | | | ጠቅላይ ፍ/ቤት | 300,000 | 300,000 | | | | |
| | 01 | 003 | የገጠር ችሎት ጽቤቶች ዕቃ ግዢ | 300,000 | 300,000 | | | | |
| 121 ፍ/ፀ/ጉዳይ ቢሮ | | | ፍ/ፀ/ጉዳይ ቢሮ | 500,000 | 500,000 | | | | |
| | 01 | 001 | የቢሮ እድሳትና ጥገና | 500,000 | 500,000 | | | | |
| 111 አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት | | | አፈ-ጉባኤ ጽቤት | 3,500,000 | 3,500,000 | | | | |
| | | | የክልል ምክር ቤት ህንፃ ዲዛይን ጥናት ግንባታ | 3,500,000 | 3,500,000 | | | | |
| | | | ኢኮኖሚ ልማት | 48,090,100 | 40,280,100 | 4,310,000 | | 3,500,000 | |
| 211 ግብርናና ገ/ል/ቢሮ | | | ግብርናና ገ/ል/ቢሮ | 9,564,000 | 1,754,000 | 4,310,000 | | 3,500,000 | |
| 008/211 01-01 | 01 | 003 | የገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከል ግንባታና ቁሳቁስ ማሟያ ግዢ | 381,200 | 381,200 | | | | |
| 007/211 01-01 | 01 | 004 | የድሬ ጠያራ አይሮፕላን ማረፊያ ግንባታ አጥር ግንባታ | 153,800 | 153,800 | | | | |
| 000/211/01/03 | 01 | 014 | መጠጥ ውሃና ሣኒቴሽን የመንግስት መቀናጀና ከዓለም ባንክ ብድርና እርዳታ | 2,597,000 | 487,000 | 510,000 | | 1,600,000 | |
| | 01 | 015 | ግብርና እርሻ ስራ | 3,140,000 | | 1,240,000 | | 1,900,000 | |
| | 01 | 013 | የገጠር መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን የመንግስት፣ መቀናጀና ከአፍሪካ ልማት ባንክ ብድር/ | 2,799,000 | 239,000 | 2,560,000 | | | |
| 000/211/01/03 | 0 | 016 | ድርብ ተግባር ያለው የእርሻ ትራክተር ግዢ | 493,000 | 493,000 | | | | |
| 418 የሐረር ው/ፍ/ ማሻሻያ | | | የሐረር ወሃ ፍሳሽ ማሻሻያ | 2,129,900 | 2,129,900 | | | | |
| | 01 | 004 | የሐረር ከተማ መጠጥ ውሃ ማሻሻያ | 2,129,900 | 2,129,900 | | | | |
| 232 ጥ/አ/ንግ/ ጽ/ ቤት | | | ጥ/አ/ንግድ ማስፋፊያ ጽ/ቤት | 764,500 | 764,500 | | | | |

www.chilot.me

| አስፈፃሚ መ/ቤት | ንዑስ ፕሮግራም | ፕሮጀክት | የፕሮጀክቶች ዝርዝር | የፀደቀ በጀት | የፋይናንስ ምንጭ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ከመንግስት | ከዕርዳታ | መለያ | ብድር | መለያ |
| 000/232/01/01 | 01 | 002 | ክላስተር ዴቬሎፕመንት ግንባታ ፕሮጀክት | 376,300 | 376,300 | | | | |
| | 01 | 003 | የሌይ አውት ማዕከል አገልግሎ ግንባታ | 388,200 | 388,200 | | | | |
| **231/ን/ኢ/ከ/ል/ቢሮ** | | | **ንግድ ኢንዱስትሪ ከተማ ልማት** | **3,631,700** | **3,631,700** | | | | |
| 000/231/01/01 | 01 | 004 | የሐረር ከተማ የተቀናጀ ልማት ጥናት ፕሮጀክት (IDP) | 774,600 | 774,600 | | | | |
| | | 010 | የሐረር ከተማ መልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፓኬጅ | 1,712,700 | 1,712,700 | | | | |
| **275 የቤቶች ል/ፕ/ጽ/ቤት** | | | **የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት** | **1,144,400** | **1,144,400** | | | | |
| 000/275/01/01 | 01 | 001 | የቤቶች ልማት ግንባታ | 1,144,400 | 1,144,400 | | | | |
| **416 ሐረር ማዘጋጃ ቤት** | | | **ሐረር ማዘጋጃ ቤት** | **2,000,000** | **2,000,000** | | | | |
| 000/01/01 | 01 | 002 | የመሬት ዝግጅትና ካሳ ክፍያ | 2,000,000 | 2,000,000 | | | | |
| **273መንገድ ስራ ባለስልጣን** | | | **መንገድ ስራ ባለስልጣን** | **30,000,000** | **30,000,000** | | | | |
| 000/273/01/01 | 01 | 002 | የአስፋልት መንገድ ግንባታ | 30,000,000 | 30,000,000 | | | | |
| | | | **ማህበራዊ ልማት** | **10,203,700** | **8,293,700** | **1,100,000** | | **810,000** | |
| **000/311 ትምህርት ቢሮ** | | | **ትምህርት ቢሮ** | **2,846,100** | **2,036,100** | | | **810,000** | |
| 01-01 | 01 | 005 | መድሃኒያ ዓለም ት/ቤት ቴክኒክና ሞያ ማስፋፊያ ግንባታ | 1,426,100 | 1,426,100 | | | | |
| 01-01 | 01 | 006 | ሐረር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማስፋፊያ ግንባታ /አፈር እቀባ/ | 20,000 | 20,000 | | | | |
| | 01 | 003 | የትምህርት እና አቅም ግንባታ ቢሮ ጣሪያ እድሳትና ጥገና | 15,000 | 15,000 | | | | |
| 007/311 02-01 | 01 | 010 | የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች /ገልመሽራ ስግቻ/ ፈርኒቸር የት/መሳሪያና ኢኩመንት ግዢ | 175,000 | 175,000 | | | | |
| 002/311 02-01 | 02 | 006 | የጀጎል እካባቢ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ግንባታ | 180,000 | 180,000 | | | | |
| 000/311 01-01 | 01 | 010 | በአፍሪካ ልማት ባንክ ለተሰሩ የሁለት 1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ፈርሂቸር የት/መሳሪያ ኢኩመንት ግዢ | 850,000 | 40,000 | | | 810,000 | |
| 000/311 01-01 | 02 | 001 | አርበኞች 1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ማስፋፋት ግንባታ | 180,000 | 180,000 | | | | |

www.chilot.me

| አስፈፃሚ መ/ቤት | ንዑስ ፕሮግራም | ፕሮጀክት | የፕሮጀክቶች ዝርዝር | የፀደቀ በጀት | የፋይናንስ ምንጭ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ከመንግስት | ከዕርዳታ | መለያ | ብድር | መለያ |
| 318 አቅም ግንባታቢሮ | | | አቅም ግንባታ ቢሮ | 1,100,.000 | | 1,100,.000 | | | |
| 000/318/01/01 | 01 | 001 | ለአቅም ግንባታ | 1,100,000 | | 1,100,000 | | | |
| 341 ጤና ጥበቃ ቢሮ | | | ጤና ጥበቃ ቢሮ | 3,679,200 | 3,679,200 | | | | |
| 000/341/01/01 | 02 | 006 | የሀ/ፋ/ሆ/ልና ሳንባ ነቀርሳ ሆስፒታልን ለማዋሐድ የላስትራ ንጣፍና በረንዳ ግንባታ | 385,200 | 385,200 | | | | |
| | 02 | 005 | የጤና ጥበቃ ቢሮ ግንባታ | 694,000 | 694,000 | | | | |
| | 02 | 002 | የሐረር ነርስ ት/ቤት ማስፋፋት | 2,600,000 | 2,600,000 | | | | |
| 000/351 | | | ባህል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ | 2,578,400 | 2,578,400 | | | | |
| 01/01 | 02 | 002 | የግል ሙዚየም ግንባታ/አብደላ ሸሪፍ | 239,600 | 239,600 | | | | |
| 01/01 | 01 | 002 | የሐረሪ ሙዚየም አዳራሽ ክፍል ጥገና | 69,300 | 69,300 | | | | |
| 01/01 | 01 | 003 | የሐረሪ ባህል ማዕከል ግንባታ | 1,269,500 | 1,269,500 | | | | |
| 01/01 | 01 | 004 | ወጣት ፓኬጅ | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| | | | የአካባቢ ቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤቶች | 9,000,000 | 9,000,000 | | | | |
| 001-111-01/01 | 01 | 001 | አሚር ኑር አ/ቀበሌ ልማት ፕሮጀክት | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| 002-111-01/01 | 01 | 001 | አባድር አ/ቀበሌ ልማት ፕሮጀክት | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| 003-111-01/01 | 01 | 001 | ሸንኮር አ/ቀበሌ ልማት ፕሮጀክት | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| 004-111-01/01 | 01 | 001 | አቦከር አ/ቀበሌ ልማት ፕሮጀክት | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| 005-111-01/01 | 01 | 001 | ጀኔላ አ/ቀበሌ ልማት ፕሮጀክት | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| 006-111-01/01 | 01 | 001 | ሃኪም አ/ቀበሌ ልማት ፕሮጀክት | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| 007-111-01/01 | 01 | 001 | ድሬ ጠያራ አ/ቀበሌ ልማት ፕሮጀክት | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| 008-111-01/01 | 01 | 001 | ኤረር አ/ቀበሌ ልማት ፕሮጀክት | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| 009-111-01/01 | 01 | 001 | ሶፊ አ/ቀበሌ ልማት ፕሮጀክት | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ ብሔራዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

12 ኛ ዓመት ቁጥር 7
12th Year No 7

ሐረር ጥር ጥር 29 ቀን 2000 ዓ/ም
HARAR, JAN /2008

| | | |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ ብር 4.50<br>Unit Price Bir. 4.50 | በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 952<br>P.o .Box 952 |

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር 74/2000**
የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የቀበሌዎችን አስተዳደር አከላለል አደረጃጀትና ስልጣንና ተግባራቸዉን ለማሻሻልና እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ______ ገጽ 569

## አዋጅ ቁጥር 74/2000

## በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቀበሌዎችን አስተዳደር አከላለል አደረጃጀትና ስልጣንና ተግባራችውን ለማሻሻል እና እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተጀመረው ምቹ የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ለማጠናከር ህዝቡን በልማቱ እንቅስቃሴ በቀጥታ በማሳተፍ ፈጣን ልማት ለማምጣት ፣ ሰላምና የተሻለ የፍትህ ስርዓት እንዲሁም መልካም አስተዳደር እንዲጎለብት ለማድረግ የቀበሌ አስተዳደር የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ፣

የቀበሌ አስተዳደር ለህዝቡ በሚሰጠዉ አገልግሎት ቀልጣፋ ዉጤታማ አሰራር ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው የልማት አጋዥ እንዲሆን ለማስቻል በአግባቡ ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

በክልሉ ህገ-መንግስት መሰረት ያልተማከለ አስተዳደር ስርዓትን እውን ለማድረግ የህዝቡ ሉአላዊነትና ውሳኔ ሰጪነትን ለማረጋገጥ፣ የክልሉን ህገ መንግስትና ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ልዩ አወቃቀርና አደረጃጀት አስፈላጊ መሆኑን በማመን፤

ለዚህም ምቹ ሁኔታዎችን ከወዲሁ ለማመቻቸት እንዲያስችል የቀበሌ አስተዳደርን አከላለል ፣አደረጃጀትና በተሻሻለው የሐረሪ ህዝብ ክልል ህገ መንግስት ቁጥር46/97 አንቀጽ 75(3) እና 51(2)(ሀ) መሰረት የሚከተለው ታውጇል ፡፡

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “ የቀበሌን አስተዳደር አከላለል፣ አደረጃጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለማሻሻል እና እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 74/2000” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፣

1. “ ህገ-መንግስት” ማለት የተሻሻለው የሐረሪ ህዝብ ክልል ህገ-መንግስት ቁጥር 46/97 ማለት ነው ፡፡

2. “ ቀበሌ ” ማለት በክልሉ በታችኛው እርከን ደረጃ ያለውና በዚህ አዋጅ መሰረት የተቋቋመ የከተማና የገጠረ ቀበሌ አስተዳደር ማለት ነው፡፡

3. “ ነዑስ ቀበሌ” ማለት ለዚህ አዋጅ አላማ በአዋጅ ቁጥር 44/96 መሰረት ተቋቁመው

www.chilot.me

የነበሩ 36 የከተማና የገጠር ቀበሌ አስተዳደር ማለት ነው፡፡

4. "ማህበራዊ ሽምግልና ጉባኤ "ማለት በተሻሻለዉ የክልል ህገ መንግስት አንቀጽ 75/2/ሐ ላይ የተመለከተዉን ማህበራዊ ፍርድ ቤት ማለት ነው፡፡

5. "የቀበሌ መስተዳደር ምክር ቤት " ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የተቋቋመ የከተማና የገጠር ቀበሌ የህግ አስፈፃሚ አካል ነው ፡፡

6. "መስተዳደር ምክር ቤት " ማለት በሐረሪ ህዝብ ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ 46(2) የተመለከተው የክልሉ መንግስት ከፍተኛው የህግ አስፈፃሚ አካል ነው ፡፡

## 3. ስለ ቀበሌ አስተዳደር መቋቋም

1. በክልሉ ህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ የተፋጠነ ልማት ለማስመዝገብ እንዲያስችል የነዋሪውን የህዝብ ቁጥር ባማከለ ዝቅተኛውን መንግስታዊ የአስተዳደር እርከን ማቋቋም ይቻል ዘንድ በክልሉ ያሉትን የቀድሞ ሠላሳ ስድስት የከተማና የገጠር ቀበሌዎች ዘጠኝ ቀበሌዎች ሆነው ስድስት የከተማና ሦስት የገጠር ቀበሌዎች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ን.አንቀጽ 1. በተመለከተው መሰረት የዘጠኝ የቀበሌ አስተዳደሮች ስያሜና ቀበሌውን ያደራጁ የንዑስ ቀበሌዎች እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ሀ. አሚር ኑር ቀበሌ አስተዳደር
- I. ንዑስ ቀበሌ . 01
- II. ንዑስ ቀበሌ . 02
- III. ንዑስ ቀበሌ . 07

ለ. አባዲር ቀበሌ አስተዳደር
- I. ንዑስ ቀበሌ . 03
- II. ንዑስ ቀበሌ . 04
- III. ንዑስ ቀበሌ . 05
- IV. ንዑስ ቀበሌ . 06

ሐ. ሸንኮር ቀበሌ አስተዳደር
- I. ንዑስ ቀበሌ . 08
- II. ንዑስ ቀበሌ . 09
- III. ንዑስ ቀበሌ . 10

መ. አቦከር ቀበሌ አስተዳደር
- I. ንዑስ ቀበሌ .11
- II. ንዑስ ቀበሌ .12
- III. ንዑስ ቀበሌ 13

ሠ. ጂንኤላ ቀበሌ አስተዳደር
- I. ንዑስ ቀበሌ . 14 ቀበሌ
- II. ንዑስ ቀበሌ . 15
- III. ንዑስ ቀበሌ . 16

ረ. ሐኪም ቀበሌ አስተዳደር
- I. ንዑስ ቀበሌ . 17
- II. ንዑስ ቀበሌ . 18
- III. ንዑስ ቀበሌ . 19

ሰ. ኤረር ቀበሌ አስተዳደር
- I. ንዑስ ቀበሌ . ኤረር ወልዲያ
- II. ንዑስ ቀበሌ . ኡላንኡላ
- III. ንዑስ ቀበሌ . ሐዋዬ
- IV. ንዑስ ቀበሌ. ኤረር ዶዶታ

ሸ. ድሬጠያራ ቀበሌ አስተዳደር
- I. ንዑስ ቀበሌ . ደሬጠያራ
- II. ንዑስ ቀበሌ ሱቁል
- III. ንዑስ ቀበሌ . ሲግቻ
- IV. ንዑስ ቀበሌ ሐሰን ጌይ
- V. ንዑስቀበሌ . ሚያይ
- VI.ንዑስ ቀበሌ .አቦክሪ ሙጤ

ቀ. ሶፊ ቀበሌ አስተዳደር
- I. ንዑስ ቀበሌ . አው ኡመር
- II. ንዑስ ቀበሌ ገልመ ሺራ
- III. ንዑስ ቀበሌ . ሶፊ
- IV. ንዑስ ቀበሌ አው በርኸደሌ
- V. ንዑስ ቀበሌ.. ሐረዌ
- VI. ንዑስ ቀበሌ ቂሌ
- VII. ንዑስ ቀበሌ ቡርቃ

## 4. የአዋጁ ተፈፃሚነት

ይህ አዋጅ በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ውስጥ ባሉት የከተማና የገጠር ቀበሌዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል ፡፡

www.chilot.me

5. የጾታ አገላለፅ

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴት ጾታን ያጠቃልላል ፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## የቀበሌ አስተዳደር የስልጣን አካላት አደረጃጀት አወካከል እና ስልጣንና ተግባር

### ክፍል አንድ

6. የቀበሌ አስተዳደር የስልጣን አካላት

የቀበሌዎች አስተዳደር የሚከተሉት የስልጣን አካላት ይኖራቸዋል ፡፡

1. በዚህ አዋጅ መሰረት የቀበሌ አስተዳደር ከፍተኛ ስልጣን የቀበሌው ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱ ለወከለው ህዝብ እና ለክልሉ ም/ቤት ነው ፡፡
2. የቀበሌ አስተዳደሩ የአስፈፃሚነት ስልጣን የተሰጠው ለቀበሌው መስተዳድር ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለቀበሌው ምክር ቤትና ለክልሉ ፕሬዚዳንት ነው ፡፡
3. በእያንዳንዱ የገጠሩማና የገጠረ ቀበሌዎች ዉስጥ የቀበሌ ማህበራዊ ሽምግልና ጉባኤ የዳኝነት ስልጣንና ተግባር አግባብ ባለዉ ህግ መሰረት ይወሰናል፡፡

7. የቀበሌ አስተዳደር ስልጣንና ተግባር

1. የፌደራልና የክልሉን መንግስት ህጎች ፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል ፤
2. በክልሉ መንግስት በሚሰጥ አቅጣጫ መሰረት የተለያዩ የአካባቢ ልማት ስራዎችን ይሰራል ፤
3. በቀበሌ አስተዳደር ባለቤትነት ስር ያሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶችን ያከራያል ፣ የቤት አበል ለሚከፈላቸው በመንግስት መመሪያ መሰረት እንዲከፈል ያደርጋል ፤
4. በክልሉ መስተዳደር ም/ቤት እና ገቢዎች ባለስልጣን በሚሰጠው ውክልና የገቢ ግብሮችን ያሰባስባል ፣ ለክልሉ ገቢዎች ባለስልጣን ያስተላልፋል ፤
5. በመንግስት መመሪያ መሰረት የውስጥ ገቢውን ይሰበስባል፣ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል ፤
6. የቀበሌዉን ፀጥታ ከክልሉ መንግስት የፀጥታ ጉዳይ ተቋማት ጋር በመሆን እና ህዝቡን በማስተባበር እንዲጠበቅ ያደርጋል ፤
7. በቀበሌ ውስጥ የመልካም አስተዳደርና የዲሞክራሲ ስርዓት እንዲከበር ያደርጋል ፣
8. የቀበሌ ነዋሪ ህዝብ በአካባቢው የልማት ስራዎች እንዲሳተፍ ያነሳሳል ፣ ያደረጃል ፣ ይመራል፣ ድጋፍ ይሰጣል ፤
9. በቀበሌው ውስጥ ለልማት ሞዴል ሊሆኑ የሚችሉ ነዋሪዎችን ይለያል ፣ ያበረታታል ፤
10. ስለ ቀበሌ ነዋሪዎች መሰረታዊ መረጃዎችን በአግባቡ ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ወቅታዊ ያደርጋል ፤
11. መንግስታዊ አገልግሎቶችን ለቀበሌው ህዝብ የልማት፣ የማህበራዊና የፍትህ አገልግሎቶች በጥራትና በፍጥነት እንዲያገኙ ያደርጋል ፤
12. በቀበሌው ነዋሪዎች መካከል መግባባትን በሠላም አብሮ የመኖር የዲሞክራሲ ባህል እንዲጎለብት ያደርጋል ፤
13. በቀበሌ ህዝብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማትን ለማፋጠን ሠላማዊና ዲሞክራዊያዊ ባህል እንዲጎለብት መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆነ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይሰራል ፤
14. በቀበሌው የሚገኘውን የመንግስትና የህዝብ ንብረት እንዲጠበቅ ያደርጋል ፤
15. በቀበሌ ክልል ውስጥ ህገ-ወጥ ንግድና ግንባታን ከጅምሩ ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል ፤
16. በቀበሌ ክልል ውስጥ የሚገኙትን ታሪካዊ ቦታና ቅርሶችን በህጉ መሰረት እንዲጠበቁ ያደርጋል፡፡
17. ሌሎች በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት የሚሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

### ክፍል ሁለት
### የቀበሌ ም/ቤት አወካከል ፣አወቃቀር እና ስልጣንና ተግባር

8. የቀበሌ ም/ቤት አወካከልና አወቃቀር

1. የቀበሌ ም/ቤቶች የቀበሌዎችን የህዝብ ብዛት እና የምርጫ ክልሎችን መሰረት በማድረግ ከአንድ መቶ ሃምሣ እስከ ሁለት መቶ አባላት በቀጥታ ምርጫ የሚወከሉበት ም/ቤት ነው ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ የተደነገገዉ ቢኖርም የከተማ ቀበሌ ም/ቤቶች በሁለት ጉባኤዎች የተዋቀረ የቀበሌ ምክር ቤት ነዉ ፡፡

www.chilot.me

9. **የከተማ የቀበሌ ም/ቤቶቹ ጉባኤዎች እናአወካከል**

1. የቀበሌ ም/ቤቶች ጉባኤዎች ፡-
   ሀ. የቀበሌ የህዝብ ተወካዮች ጉባኤና ፣
   ለ. የቀበሌ የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ናቸው ፡፡
2. የቀበሌ የህዝብ ተወካዮች ጉባኤ በእያንዳንዱ ቀበሌ ም/ቤት 70 % የሚወከሉበት ጉባኤ ሆኖ ፡-
   ሀ. 55 % ቀበሌዉን ባደራጁት ነዑስ ቀበሌዎች የሚመረጡ ተወካዮች የሚወከሉበት ሲሆን ፣
   ለ. 15 % ከከተማዉ ቀበሌ ምክር ቤት አጎራባች በሆኑ የገጠር ቀበሌዎች የሚመረጡ ተወካዮች የሚወከሉበት ይሆናል ፡፡
3. የቀበሌ የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በእያንዳንዱ ከተማ ቀበሌ ም/ቤት የሐረሪ ብሔረሰብ 30 % የሚወከ ሉበት ጉባኤ ነው ፡፡
4. የጉባኤዎች አባላት ምርጫ ነፃና ቀጥተኛ በሆነ ድምጽ በሚስጥር በሚሰጥበት ሥርዓት ይፈፅማል፡፡ የቀበሌ ም/ቤት አባላት ብዛት የጉባኤዎቹ አወካከል የምርጫ ሁኔታ አግባብ ባለዉ የምርጫ ህግ ይወሰናል ፡፡

10. **የቀበሌ የህዝብ ተወካዮች ጉባኤ ስልጣንና ተግባራት**

የቀበሌ የህዝብ ተወካዮች ጉባኤ በቀበሌ ምክር ቤቱ ከሚኖረው ስልጣንና ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል ፡፡

1. የቀበሌ ም/ቤት አባላት መካከል ለቀበሌው ም/ቤት አፈ-ጉባኤነት አንድ አባል ይጠቀማል፡፡

11. **የቀበሌ የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር**

የቀበሌ የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በቀበሌ ምክር ቤቱ ከሚኖረው ስልጣንና ተግባር በተጨማሪ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፡፡

1. የቀበሌውን ዋና አስተዳዳሪ ከምክር ቤት አባላት መካከል ይጠቁማል ፡፡
2. የቀበሌ ም/ቤት ም/አፈ-ጉባኤውን ከምክር ቤት አባላት መካከል ይጠቁማል ፡፡

12. **የቀበሌ ም/ቤት ስልጣንና ተግባር**

የቀበሌ ም/ቤት በዚህ አዋጅ በሚሰጠዉ ስልጣን መሰረት የቀበሌው አስተዳደር ከፍተኛ የስልጣን አካል ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

1. የፌደራልና የክልሉ ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል ፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 (1) እና አንቀጽ 20 መሰረት የሚቀርበዉን እጩ 50+1 ድምፅ መርምሮ ያፀድቃል ፡፡
3. የቀበሌውን የአካባቢ ልማት እቅድና በጀት ያፅድቃል ፡፡
4. በቀበሌው ውስጥ መልካም አስተዳደርና የዲሞክራሲ ስርዓት መከበሩን ያረጋግጣል ፡፡
5. በቀበሌው የኢኮኖሚና የማህበራዊ እቅዶች አፈፃፀምና የተገኙ ውጤቶችን ይገመግማል ፡፡
6. በቀበሌው በሚካሄዱ የአካባቢ ልማት እንቅስቃሴዎች የህዝብ ተሳትፎ እንዲረጋገጥ ያደርጋል ፡፡
7. ከሚመለከታው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር የቀበሌውን ፀጥታ እንዲከበር ያደርጋል ፡፡
8. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ን.አንቀጽ 4 እና 5 የቀበሌውን የውስጥ ገቢና በውክልና የሚሰጠውን የክልሉ ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡን ያረጋግጣል፡፡
9. ለከተማ ቀበሌ ም/ቤት አፈ-ጉባኤነት ከቀበሌው የህዝብ ተወካዮች ጉባኤ ጠቋሚነት የሚቀርበውን እጩ እና ለም/አፈ-ጉባኤነት ከሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ የሚቀርበውን እጩ እንዲሁም ለገጠር ቀበሌ ም/ቤት የሚቀርቡትን አፈ-ጉባኤና ም/አፈ-ጉባኤዎችን 50+1 ድምፅ መርምሮ ያፀድቃል፡፡

13. **የቀበሌ ም/ቤት አመራር**

1. ም/ቤቱ የራሱ አፈ-ጉባኤና ምክትል አፈ-ጉባኤዎች ይኖሩታል ፡፡
2. እንደአስፈላጊነቱ የተለያዩ ኮሚቴዎችን በስሩ ሊያደራጅ ይችላል ፡፡

14. **የአፈ-ጉባኤዉ ስልጣንና ተግባር**

1. የምክር ቤቱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል ፡፡
2. የም/ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል ፡፡
3. በም/ቤቱ የሚደራጁትን የተለያዩ ኮሚቴዎች ያስተባብራል፡፡

www.chilot.me

3. በም/ቤቱ የሚደራጁትን የተለያዩ ኮሚቴዎች ያስተባብራል።

4. በም/ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል ።

5. የአፈ-ጉባኤው ሌሎች ተግባራት በቀበሌ ም/ቤቱ በሚወጣው መመሪያ ይወስናል ።

## 15. የምክትል አፈ-ጉባኤዉ ስልጣን ተግባር

1. በአፈ-ጉባኤው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል ።

2. አፈ-ጉባኤው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።

## ክፍል ሦስት

## ስለ ቀበሌ መስተዳደር ም/ቤት

## 16. ስለ ቀበሌ መስተዳደር ም/ቤት መቋቋም

1. የቀበሌ መስተዳደር ም/ቤት የቀበሌው ዋና አስተ ዳዳሪ እና ም/አስተዳዳሪና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑትን የክልል መስተዳደር ምክር ቤት የሚሰየም የቀበሌ አስተዳደር ዋና ኦስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ መሰረት ተቋቋሚል ።

2. የቀበሌ መስተዳደር ም/ቤቱ በዚህ ህግና በሌሎች ህጎች የተጣሉበትን ኃላፊነቶች ለመወጣት ይቻለው ዘንድ የራሱ ጽ/ቤት እና አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞች ይኖሩታል ።

3. የቀበሌው ጽ/ቤት በበላይነት የሚመራው በቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ ይሆናል ።

## 17. የቀበሌ መስተዳደር ም/ቤት ተጠሪነት ኃላፊነት እና የሥራ ዘመን

1. የቀበሌ መስተዳደር ም/ቤት ተጠሪነቱ ለቀበሌ ም/ቤቱና ለቀበሌው አስተዳዳሪ ይሆናል ።

2. የቀበሌ መስተዳደር ም/ቤት አባላት በምክር ቤት እባልነታቸው ለሚሰጡት ውሳኔና ለሚፈጽሙት ተግባራት የጋራ ኃላፊነትና ተጠያቂነት አለባቸው።

3. በሌላ አኳኃን ካልተወሰነ በስተቀር የቀበሌ መስተዳደር ም/ቤት የስራ ዘመን የቀበሌው ም/ቤት የስራ ዘመን ነው ።

## 18. የቀበሌ መስተዳድር ም/ቤት አደረጃጀት

የቀበሌው መስተዳደር ም/ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል ።

1. ዋና አስተዳዳሪ፤

2. ምክትል አስተዳዳሪ እና

3. እንደአስፈላጊነቱ የክልል መስተዳደር ምክር ቤት የተለያዩ የስራ ዘርፎች ያዋቅራል ።

## 19. የቀበሌ መስተዳደር ም/ቤት ስልጣንና ተግባር

የቀበሌ መስተዳድር ም/ቤት የቀበሌው አስተዳደር ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ አካል ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. የፌደራልና የክልሉን መንግስት ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል ።

2. የቀበሌውን ዓመትዊ እቅድና በጀት ያዘጋጃል ለቀበሌው ም/ቤት ያቀርባል፣ ሲፀዲቅም ተግባራዊ ያደረጋል ።

3. የቀበሌውን ህዝብ ለልማት ሥራ ያነሳሳል፤ ያደራጃል።

4. የቀበሌውን የዉስጥ ገቢ በማሰባሰብ በመንግስት መመሪያ መሰረት በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

5. የቀበሌውን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ስራዎች አገል ግሎቶች አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይገመግማል።

6. ከመስተዳደር ም/ቤትና ከክልሉ ገቢዎች ባለ ስልጣን በሚሰጠው ውክልና ግብር ይሰበስባል ለክልሉ ገቢዎች ባለስልጣን ያስተላልፋል ።

7. የቀበሌ ም/ቤትና የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተግባራዊ ያደርጋል ።

8. በቀበሌው ዉስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎችን አስመልክቶ መሰረታዊ መረጃዎች በአግባቡ ተመዝግበው እንዲ ያዙና ወቅታዊ እንዲሆኑ ያደርጋል ፤

9. በቀበሌው ውስጥ በህዝብ ተሳትፎ ፀጥታ እንዲጠበቅ ነዋሪውን ያስተባብራል ፤

10. ሌሎች በክልሉ መስተዳደር ም/ቤት እና አስፈፃሚ አካላት በውክልና የሚሰጡትን ተግባራት ያከናዉናል።

## 20. ስለ ቀበሌዉ ዋና አስተዳዳሪ አሰያየም

ለከተማ ም/ቤት በዚህ አዋጅ አንቀፅ 11(1) ላይ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በገጠር የቀበሌ ም/ቤት ዋና አስተዳዳሪ ከቀበሌዉ ም/ቤት መካከል አብላጫ ድምፅ ባገኘ ወይም ባገኙት የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ድርጅቶች አቅራቢነት በቀበሌው ም/ቤት ይሰየማል ።

www.chilot.me

21. **የቀበሌ መስተዳደር ም/ቤት አባላት ስልጣንና ተግባር**

1. **የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር፦**
የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለቀበሌ ም/ቤትና ለክልሉ ፕሬዚዳንት ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል ።
ሀ. የቀበሌ መስተዳደር ኃላፊና ተጠሪ ሆኖ የቀበሌ መስተዳደሩ ሥራ መሪ ነው ።
ለ. የቀበሌ መስተዳደር ም/ቤቱን ስብሰባዎች ይጠራል፣ ይመራል ።
ሐ. ም/አስተዳዳሪውን ሸምክር ቤቱ በማቅረብ ያሾማል።
መ. የቀበሌውን ፀጥታና ሁላም ጉዳዮችን ከክልሉ መንግስት ፀጥታ ተቋማትና ኃላፊዎች ጋር በመሆን በትብብር ይሰራል ።
ሠ. የመንግስት ህጎች ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች ደንቦችና መመሪያዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል ።
ረ. በክልሉ የፋይናንስ ደንብና መመሪያ የቀበሌውን በጀት ያስተዳድራል ።
ሰ. በቀበሌው የሚከናወን ፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴን ይመራል።
ሸ. የቀበሌውን አመታዊ የሥራ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለቀበሌ ም/ቤት በማቅረብ ያፀድቃል። የፀደቀውንም በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።
ቀ. ለክልሉ ፕሬዚዳንት እና ለቀበሌው ም/ቤት ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል ።
በ. ከክልሉ ፕሬዚዳንት፣ ከቀበሌው ም/ቤት እና ከክልሉ መስተዳደር ም/ቤት የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

2. **የቀበሌው ምክትል አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር**
የቀበሌ ም/አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል ።
ሀ. በቀበሌው ዋና አስተዳደሪ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል ።
ለ. የቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።

## ክፍል አራት
## ስለ ማህበራዊ ሸምግልና ጉባኤ

22. **ስለ ማህበራዊ ሸምግልና ጉባኤ መቋቋም ተጠሪነት አሰራር እና የሥራ ዘመን**

1. በእያንዳንዱ የከተማና የገጠር ቀበሌዎች ዉስጥ የቀበሌ ማህበራዊ ሸምግልና ጉባኤ በዚህ አዋጅ መሰረት ተቋቁመዋል ።
2. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 22(1) የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በቀበሌዉ አስተዳደር ክልል ዉስጥ ለቀበሌ ነዋሪ አመቺ በሆኑ አካባቢዎች ከአንድ በላይ የቀበሌ ማህበራዊ ሸምግልና ጉባኤዎች ሊሰየሙ ይችላሉ ።
3. የቀበሌ ማህበራዊ ሸምግልና ጉባኤዎች ተጠሪነት ለቀበሌዉ ም/ቤት ይሆናል ።
4. የጉባኤ አደረጃጀት ስልጣንና ተግባር፣ አሰራሩን የአባላቱን ብዛትና አሰያየም አግባብ ባለው ህግ ይወሰናል።
5. የቀበሌ ማህበራዊ ሸምግልና ጉባኤ የስራ ዘመን የቀበሌ ም/ቤቱ የስራ ዘመን ነዉ ።

## ክፍል አምስት
## የቀበሌ ምክር ቤት የስብሰባ ጊዜ፣ የስራ ዘመን የዉሳኔ አሰጣጥና ምልዐተ ጉባኤ

23. **የቀበሌ ም/ቤት የስብሰባ ጊዜና የስራ ዘመን**

1. የቀበሌ ም/ቤቱ በየሩብ ዓመቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል።
2. የቀበሌ ም/ቤት አባላት የስራ ዘመን ለአምስት ዓመት ነው ። የስራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል ።
3. በዚህ አንቀጽ ን. አንቀጽ 2. የተደነገገው ቢኖርም የቀበሌ ም/ቤቱ የምርጫ ዘመኑ ከማለቁ በፊት ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱንና የክልሉን ህልውና የሚነኩ ተግባራት መፈፀሙን የክልሉ ፕሬዚዳንት ሲረዳ ወዲያውኑ የክልሉ ም/ቤት በማስፈቀድ ሊበተን ይችላል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ በተደነገገው መሰረት የቀበሌ ም/ቤቱ ከተበተነ ፕሬዚዳንቱ ይህንኑ ለክልል ም/ቤት ሪፖርት ያቀርባል ።

www.chilot.me

5. ፕሬዚዳንቱ ወዲያውኑ ጊዜያዊ የቀበሌ አስፈፃሚ አካላትን በመሰየም በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ አዲስ የቀበሌ ም/ቤት ምርጫ እንዲደረግ ያደርጋል ፡፡

6. የቀበሌ ም/ቤት መደበኛ ስብሰባ በማይኖርብት ወቅት የቀበሌው አስተዳደሪ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ይጠይቃል ፡፡ ከቀበሌ ም/ቤተ አባላት መካከል 1/3 በላይ የሚሆኑ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ-ጉባኤው ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት ፡፡

## 24. የቀበሌ ም/ቤት የውሳኔ አሰጣጥና የምልዐተ ጉባኤ

1. በከተማ ቀበሌ ም/ቤት ከሁለቱ ጉባኤዎች ከእያንዳንዳቸው 50+1 በላይ የሚሆኑ የቀበሌ ም/ቤት አባላት ከተገኙ እንዲሁም በገጠር ቀበሌ ከም/ቤቱ አባላት መካከል 50+1 በላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

2. ማንኛውም ዉሳኔ የሚተላለፈው በዚህ አዋጅ በልዩ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በም/ቤቱ አባላት አብላጫ ድምፅ ይሆናል ፡፡

3. የቀበሌ ም/ቤቱ አሰራሩን አስመልከቶ የክልሉ መስተ ዳደር ምክር ቤት ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 25. ስለ ቀበሌ አስተዳደር ም/ቤት ማዕከላት አመራረጥ እና የአገልገሎቶች ተደራሽነት ፡፡

1. በአዲስ መልክ የተደራጁ የቀበሌ መስተዳደር ም/ቤት ማዕከላት አመራረጥ በክልሉ መስተዳደር ም/ቤት መመሪያ መሰረት ይወስናል ፡፡

2. ከቀበሌ ማዕከላት ርቀት የተነሳ ነዋሪዉ በቅርበት አገልግሎት እንዲያገኝ በመስተዳደር ም/ቤቱ አስፈላጊ ናቸዉ ተብሎ የሚታመንባቸዉን ተቋማት ከቀበሌ ማዕከላት በታች ልያደራጅ ይችላል ፡፡

## 26. ስለቀበሌ መስተዳደር ም/ቤት የበጀት ምንጭ

ሀ. ከመንግስት በቀመር የሚመደብ ፤

ለ. ከቀበለው የውስጥ ገቢ እና

ሐ. ከሌሎች አግባብ ካላቸው የፋይናንስ ምንጮች ይሆናል፡፡ ዝርዝሩ በክልል መስተዳደር ም/ቤት መመሪያ ይወስናል፡፡

## 27. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸወ ህጎች

1. በሐረሪ ብ/ክ/መንግስት የቀበሌዎችን አስተዳደር ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 44/96 በዚህ አዋጅ ተሽሯል ፡፡

2. የቀበሌ መስተዳደር ምክር ቤት አካላት ማቋቋሚያ የመስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 8/97 በዚህ አዋጅ ተሽሯል ፡፡

3. የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም የክልል ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 11/98 አንቀጽ 20 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

4. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚጋጩ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በዚህ አዋጅ ውስጥ ለተደነገጉት ጉዳዮች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም ፡፡

## 28. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በአዋጅ ቁጥር 44/96 መሰረት ተቋቋመው የነበሩ ንዑስ የቀበሌ አስተዳደር እና በደንብ ቁጥር 8/97 ተቋቋመው የነበሩ የአካባቢ ቀበሌ መስተዳደር ምክር ቤቶች ሥልጣንና ተግባር አግባብ ባለዉ የምርጫ ህግ መሰረት የቀበሌ ም/ቤት ምርጫ ተካሂዶና የቀበሌ ም/ቤትና መስተዳደር ም/ቤቶች ስራ እስኪጀምሩ ድረስ ባሉበት ይቀጥላሉ፡፡

2. በዚህ አዋጅ መሰረት የተቋቋሙት ቀበሌዎች እስኪደራጁ ድረስ በስራ ላይ ያሉ ደንቦችና መመሪያዎች ተፈፃሚነት ይቀጥላል ፡፡

3. በቀድሞዉ ቀበሌዎች አስተዳደር እና በደንብ ቁጥር 8/97 ተቋቁሞ የነበሩ የቀበሌ መስተዳድር ም/ቤቶች የተጀመሩ ስራዎች በዚህ አዋጅ መሰረት በተቋቋሙት አካላት እንደተጀመሩ ተቆጥረው አፈፃፀማቸዉ ይቀጥላል ፡፡

## 29. ደንብና መመሪያ ስለማዉጣት

የክልሉ መስተዳደር ም/ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የተለያዩ ደንቦችና መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 30. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከታህሳስ 18 ቀን 2000 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል ፡፡

ሐረር ጥር 29 ቀን 2000 ዓ/ም

ሙራድ አብዲልሃዲ

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ፕሬዚዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| 12ኛ ዓመት ቁጥር 8<br>12 th Year No 8 | | ሐረር ጥር 30 ቀን 2000 ዓ.ም<br>HARAR, Feb. 8 /2008 |
| ያንዱ ዋጋ ብር 1:40<br>Unit Price Bir. 1:40 | በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 952<br>P o Box 952 |

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 75/2000
የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ምርጫን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ....................ገጽ 576

## አዋጅ ቁጥር 75/2000

## በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቀበሌ ም/ቤት አባላት ምርጫን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት መሰረት ያልተማከለ የአስተዳደር ስርዓትን እውን ለማድረግና ምቹ ሁኔታዎችን ከወዲሁ ለማመቻቸት እንዲያስችል እና የቀበሌ አስተዳደርን እንደገና ለማደራጀትና ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2000 መሰረት የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ምርጫ ማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

የተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 20(6) እና 29(1)(2)(3) መሰረት ለአካባቢ ምክር ቤት ለየም/ቤቶቹ የሚመረጡትን አባላት እና የመራጩን ብዛት መሰረት ያደረገ ተመጣጣኝ የምርጫ ክልሎችን ማቋቋምና መወሰን የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ስልጣን መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ ፤

በዚህም መሰረት የቀበሌ ም/ቤት አባላት ብዛት የምርጫ ክልል ብዛትና አወካከሉን እንዲሁም የክልሉን ህግ መንግስትና ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ልዩ አወቃቀርና አደረጃጀት አስፈላጊ መሆኑንን በመገንዘብ፤ በተሻሻለው የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ህገ-መንግስት አንቀጽ 51(2)(ሀ) መሰረት የሚከተለው ታውጇል ።

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ምርጫን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 75/2000 " ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

### 2. ትርጓሜ

1. "**ቀበሌ**" ማለት በአዋጅ ቁጥር 74/2000 መሰረት የተቋቋመ ዘጠኝ የከተማና የገጠር ቀበሌ አስተዳደር ማለት ነው።
2. "**የከተማ ቀበሌ ምክር ቤት**" ማለት በአዋጅ ቁጥር 74/2000 መሰረት የተቋቋመው ስድስቱ የከተማ ቀበሌ ምክር ቤት ነው።
3. "**የገጠር ቀበሌ ምክር ቤት** " ማለት በአዋጅ ቁጥር 74/2000 መሰረት የተቋቋመው ሶስቱ የገጠር ቀበሌ ምክር ቤት ነው።
4. "**የቀበሌ ምርጫ ክልል**" ማለት በእያንዳንዱ የቀድሞ ቀበሌዎች ዉስጥ የሚቋቋመዉ የምርጫ ጣቢያዎች ነዉ ።

www.chilot.me

### 3. የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ምርጫና ብዛት

1. የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ምርጫ የሚካሄደው የቀበሌው ነዋሪዎችን ብዛት መሰረት በማድረግ ይሆናል።
2. አንድ የቀበሌ ምክር ቤት አባል የተመረጠበትን የምርጫ ክልልና የቀበሌውን ነዋሪዎች ይወክላል።
3. አንድ የቀበሌ ምክር ቤት ዝቅተኛዉ 150 አባላት፣ ከፍተኛው 200 አባላት ይኖሩታል ።
4. አንድ የቀበሌ ምክር ቤት አባል ቢያንስ 100 ቢበዛ 150 የሚሆኑ የቀበሌ ነዋሪዎችን ይወክላል።
5. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 4 የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ ከ20,000 ህዝብ በላይ በሚኖሩበት ቀበሌ እያንዳንዱ ተጨማሪ 600 የቀበሌ ነዋሪ አንድ ተወካይ እየጨመረ የሚታሰብ ይሆናል።
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገዉ ቢኖርም ከፍተኛው የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ብዛት ከ200 መብለጥ የለበትም ።

### 4. ስለ ቀበሌ ም/ቤት አወቃቀር፣ አወካከልና አመራረጥ

1. የከተማ የቀበሌ ም/ቤት በቀበሌ የህዝብ ተወካዮች ጉባኤና በቀበሌ የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ የተዋቀረ ም/ቤት ነው ።
2. ከላይ በአንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 3 ስለ ቀበሌ ምክር ቤት የመቀመጫ ብዛት የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ በከተማ ቀበሌ ምክር ቤት 30 % የሐረሪ ብሔረሰብ ብቻ ዕጩ የሚቀርብበትና የሚወዳደርበት ይሆናል ። ለዚህ ጉባኤ የሚቀርቡትን እጩዎች ማንኛዉም የቀበሌ ነዋሪ ሊመርጣቸዉ ይችላል ።
3. ከላይ በአንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው እንዳለ ሆኖ የከተማ የቀበሌ የህዝብ ተወካዮች ጉባኤ ከምክር ቤቱ ጠቅላላ መቀመጫ 55 % በመቶው ማንኛውም የቀበሌ ነዋሪ የሆኑ ዜጎች ሁሉ በግልና በፓርቲ የሚወዳደሩበት እና የሚወከሉበት ይሆናል ።
4. ከላይ በአንቀጽ 3(3)(6) እና 4(2)(3) የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በሐረር ከተማ ዙሪያ አዋሳኝ የገጠር ቀበሌ ነዋሪዎች 15 % በከተማ ቀበሌ የገጠር አዋሳኝ በሆኑ የቀበሌ ም/ቤት ቀጥታ የተሳትፎ ውክልና ይኖራቸዋል ። ዝርዝር አወካከልና አፈፃፀሙ በመስተዳደር ም/ቤት ደንብ የሚወሰን ይሆናል ።
5. ከላይ በአንቀጽ 3 እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ የቀበሌ ምክር ቤት ተወካዮች ብዛትና አወካከል የቀበሌ አስተዳደሩን ባደራጁት የቀድሞ ቀበሌዎች የህዝብ ብዛትን ባመጣጠነ መልኩ ከእያንዳንዱ የምርጫ ክልሎች የሚወከሉ አባላትን ያቀፈ ይሆናል ። ሆኖም ግን በከተማ ቀበሌ ም/ቤት ለሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ የሚመረጡት የቀበሌ አስተዳደሩን የሚወክሉ አባላትን ያቀፈ ይሆናል ።

### 5. የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ብዛት ለውጥ

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 3 እና 4 የተደነገገው ቢኖርም የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ብዛትን መለወጥ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት መስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ በመወሰን ከ6 ወራት አስቀድሞ ለብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ማሳወቅ ይቻላል ።

### 6. ደንብ የማውጣት ስልጣን

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት መስተዳደር ም/ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል ።

### 7. ተፈፃሚነት የሌላቸዉ ህጎች

ከዚህ አዋጅ የሚፃረር ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ ለተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈፃሚነት አይኖረውም ።

### 8. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥር 30 ቀን 2000 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

ሐረር ጥር 30 ቀን 2000 ዓ/ም

ሙራድ አብዱልሃዲ

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዚዳንት

www.chilot.me